የአብርሃምን በረከት መውረስ

Possessing The Blessings Of Abraham



ኢዮብ ማሞ

የአብርሃምን በረከት መውረስ

2001 ዓ. ም.

Possessing The Blessings Of Abraham

2009

ይህንን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉም ሆነ በከፊል ያለ ደራሲው ፈቃድ ማባዛት በሕግ የተከለከለ ነው::

Copyright © 2009, by Eyob Mamo

All right reserved.

Reproduction of text in whole or in part without the written consent by the author is unlawful

የክርስቲያኖች መቅደስ ቤተ ክርስቲያን

(ክሩሴደርስ)

Christian Temple Church

(Crusaders)

P.O.BOX 2080 CODE 1110

Addis Ababa

Ethiopia

impact@ethionet.et

ይህንን መጽሐፍ

ውድ ለሆኑ ለክርቲያኖች መቅደስ (ክሩሴደርስ) ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና አባሎች ከታላቅ ፍቅር ጋር አበረክታለሁ:: የእነሱ የማይለወጥ ፍቅርና ድጋፍ አገልግሎቴን በጊዜው እንዳከናውን ብርታት ሆኖኛል::

This book is dedicated to the most precious people on earth, the members of Christian Temple Church (Crusaders). Their unwavering love and support has been a source of strength for me to do the works of the ministry.

በኢዮብ ማሞ የተጻፉ መጻሕፍት

1) ለአእምሮ የሚመች አገልግሎት
2) የመንፈስ አንድነት:- የጠፋብን እንቁ
3) የመክሊት መቃብር
4) ተፈትኖ-ተቀብቶ የሚወጣ ማንነት
5) ከጥሪ ወደ ተልዕኮ
6) አዲስ ሕይወት
7) የአብርሃምን በረከት መውረስ
8) The Making Of Apostolic People (English)

ማውጫ

መግቢያ

ምዕራፍ አንድ

የአብርሃም ጥሪና በረከቶች.....7

ምዕራፍ ሁለት

የአብርሃም ጥሪ ባህሪያት.....12

ምዕራፍ ሶስት

የአብርሃምን ጥሪ መንከባከብ.....21

ምዕራፍ አራት

የአብርሃም በረከት እንቅፋቶች.....29

ምዕራፍ አምስት

የአብርሃም የጥሪ መንገድ.....37

ምዕራፍ ስድስት

የአብርሃም ጥሪና መለኮታዊ ጉብኝት.....45

ምዕራፍ ሰባት

የአብርሃም ጥሪና የጠሪው ስጦታ.....54

ምዕራፍ ስምንት

በአብርሃም ጥሪ መብሰል 63

ምዕራፍ ዘጠኝ

የአብርሃም ነህ ወይስ የሎጥ? 72

ምዕራፍ አስር

የባሪያ ልጅ ነህ ወይስ የጨዋ? 84

መግቢያ

ይህ ትውልድ፣ «ውረስ . . . ትወርሳለህ . . . ተነሳ . . .» በሚሉና በመሳሰሉት መልካም መልእክቶችና ዝማሬዎች የተሞላ ትውልድ ነው። ስለዚህም ምናልባት ለመውረስ የተጠራው ምን እንደሆነና በእንዴት አይነት መልኩ ሊወርስ እንደሚገባው የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚያሳየው ክሌለ የተሳሳተን ነገር በተበላሸ አካሄድ ለመውረስ ይነሳሳል ብዬ እሰጋለሁ። ይህ ጉዳይ እጅግ ሊያሳስበንና ትኩረት ልንሰጠው ይገባል፣ ምክንያቱም መርህ በጎደለው መንገድ ውርስን መፈለግ፣ የኋላ ኋላ በወረስነው ነገር ወደ መወረስ ስለሚያመጣን ነው።

የአብርሃም ጥሪና ሕይወት ውርስን አስመልክቶ ለዘመኑ አማኝና አገልጋይ እጅግ አስፈላጊ የሆኑ እውነታዎችን አዝሏል። እነዚህ እውነታዎች በቃሉ የተጻፉና ልንክዳቸው የማንችላቸው ከመሆናቸውም ባሻገር ብንክተላቸውና ብንተገብራቸው የአብርሃምን በረከት ሊያመጡልን የሚችሉ መርሆች ናቸው። በአጭሩ፣ የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የአብርሃምን መንገድ መከተል አስፈላጊ ነው።

በክርስቶስ በማመኑ ምክንያት የአብርሃም ልጅና ወራሽ የሆነ ይህ ትውልድ ምን ለመውረስ ነው የተጠራው? ይህንንስ ውረስ የተባለውን ውርስ በእንዴት አይነት መልኩ ነው የሚወርሰው? የውርስ እንቅፋቶች ምንድን ናቸው? አብርሃም ውረስ የተባለውን ለመውረስ የተከተላቸው መንገዶች ምንድን ናቸው?

ለመሆኑ የአብርሃም የጥሪ ሕይወት ምን ይመስል ነበር? እግዚአብሔር በእንዴት አይነት ሁኔታ ነበር የጠራው? ከየትስ ተነስቶ ወደ የት ነበር የሄደው? እንደ አብርሃም ልጆችስ በእኛ ሕይወት ምን ይጠበቃል? ይህ «የአብርሃም የጥሪ ሕይወት» የተሰኘ መጽሐፍ የአብርሃምን ሕይወት በማስታከክ በእኛም በዘመኑ አማኞችና አገልጋዮች ሕይወት መለኮታዊው አሰራር በምን መልኩ እንደሚከናወን ያመላክተናል።

አንድን ነገር በማሰብ ወደ ጥናታችን እንሂድ። የአብርሃምን በረከት የምንወርሰው እንደ አገልጋዮች ሳይሆን እንደ አማኞች ነው። የአብርሃም ጥሪና

በረከት «ለታላላቆች» እና «ለልዩ» ነገር ለተለዩ ሰዎች ብቻ የተገለጠ ጉዳይ እንደሆነ አስበን ራሳችንን ማግለል ከቃሉ የራቀ አመለካከት እንደሆነ ማወቅ አለብን። በክርስቶስ ላመንን ሁሉ የአብርሃም ጥሪና በረከት ተለ�ቀልናና። አምኖ መራመድና መባረክ የእኛ ፋንታ ነው።

በሕይወቱ ጥሪ የሌለው ሰው በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ተፈልጎ አይገኝም። አንዳንዶች ጥሪያቸውን ባለማወቅ ሲመላለሱ፣ ሌሎች ደግሞ ጥሪያቸውን አውቀው በዚያ ጥሪ ለመቆም ግን የተሳናቸው አሉ - አዚም ተጫኖአቸው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ግን ጥሪያችንን አውቀን በዚያም የጥሪ መላት እንድንመላለስ ነው።

አንባቢዬ ሆይ፣ እግዚአብሔር በልጁ በክርስቶስ በማመንህ ብቻ ምን አይነት ጥሪ እንደሰጠህ አስተውለሃል? ወደ መንግስቱ ሲጠራህና ልጁ ሲያደርግህ ከጌታህ በአዋጅ የጸደቀልህን በረከት ታውቀዋለህ? ለዚህ ከሰማይ ለሰማኸው ጥሪ እሺ ብለህ ለመታዘዝ ዝግጁ ነህ? በክርስቶስ ካመንህ የአብርሃም ልጅ ነህ። የአብርሃም ልጅ ከሆንክ ደግሞ የአብርሃምን በረከት ለመውረስ ተጠርተሃል። ስለዚህ፣ የዚህን ጥሪ ባህሪያት የማወቅህ ጉዳይ እጅግ አንገብጋቢ ነው።

በዚህ ጽሑፌ ከላይ የተጠቀሱትን ጥያቄዎች ለወገኖቼ ለመመለስ የቃሉን እውነት አስፍሬአለሁ። አንባቢዬ የተከፈተ ልቦናና ለቃሉ የሚታዘዝን ማንነት ይዞ እንዲያነብ ጸሎቴ ነው።

ኢዮብ ማሞ

ምዕራፍ አንድ

የአብርሃም ጥሪና በረከቶች

«ታላቅ ሀዝብም አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህን እባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድርም ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ» (ዘፍ. 12:2-3)።

እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው ሊባርከው፣ ሊያበዛውና ሊያስወርሰው ነው። ይህ እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራበት የበረከት ጥሪ ብዙ እውነታዎችን ያካትታል። ለምሳሌ፣ «በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ» (የሐዋ. 3:25) የሚለው ቃል እንደሚያመለክተን የተጠራው ለብዙዎች በረከት ለመሆን ነው። ከዚህም በተጨማሪ፣ የአብርሃም በረከት ካለበት ከራሱ ትውልድ አልፎ ለተተኪው ትውልድ የሚተርፍ በረከት እንደሆነ እናስተውላለን። «በዚችም የእግር ጫማ ስንኳ የሚያህል ርስት አልሰጠውም፤ ነገር ግን ልጅ ሳይኖረው ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጎ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ ሰጠው» (የሐዋ. 7:5)። እግዚአብሔር ለአብርሃም ከገባለት የተስፋ ቃል ውስጥ የሚመነጨው በረከት ብዙዎችን ስለሚያፈራ። «ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ» (ሮሜ 4:17) ተብሎለታል።

ይህ ሁሉ በረከት ለእኛ በእምነት የአብርሃም ልጆች ለሆንን አማኞች ተሰጥቶናል። ስለሆነም እነዚህንና የመሳሰሉትን በረከቶች እንደሌሉ አድርጎ መኖር የክስረት ሁሉ ክስረት ነው። በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን ምክንያት ሁላችን የአብርሃም ልጆች ነን። «እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ ይህንን እወቁ (ገላ. 3:7)። እንደ አብርሃም ልጆች ደግሞ

ለአብርሃም የተለቀቀ በረከት ሁሉ ተወስኖልናል፦ «እንደዚህ ከአምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ» (ገላ. 3:9)።

እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ለአብርሃም ጥሪውን ሲያስተላልፍለት እንደምንመለከተው፣ በክርስቶስ በማመናችን ምክንያት እንድንወርሳቸው የተሰጡን የአብርሃም በረከቶች የሚከተሉትን እውነታዎች ያካትታሉ።

1. «ታላቅ ህዝብም አደርግሃለሁ»

- ዘፍጥረት 12:2

እግዚአብሔር ትንሽ ጥሪ የለውም! እግዚአብሔር ማንንም ሰው ለትንሽና ለአናሳ ጥሪ አይጠራም። በክርስቶስ የሰጠን የአብርሃምን በረከት የመውረስ ጥሪ ታላቅና ሰፊ ነው። እንድንበዛ፣ እንድንስፋና ታላቅ ህዝብ እንድንሆን ተጠርተናል እንጂ ጠላት በላያችን ላይ አይሉ እንዲበዛና እንዲነግስብን በፍጹም አልተጠራንም።

ይህ በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን ምክንያት የተሰጠን የታላቅነት ጥሪ ዋነኛ ዓላማው ታላቅ ያደረገንን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማሳየት ነው። የእርሱን ታላቅነት ሳይሸሙና የትህትናን መንፈስ ሳይለቁ ለመብዛትና ለመትረፍረፍ፣ በዚያም ውስጥ የእርሱን በጎነትና ታላቅነት ለማሳየት ተጠርተናል። ይህ ደግሞ እጅግ የከበረና ታላቅ እድል ነው።

«ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው» (ዕብ. 7:7)። ስለሆነም፣ ጌታ የሰጠን ታላቅ የመሆን ጥሪ እጅግ ወሳኝ ከመሆኑም ባሻገር፣ በውስጣችን ያለውን ጸጋ ጠቅልሎ የያዘ መንፈስ አለው። ስለዚህ፣ «በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን እፈጥናለሁ (ፊል. 3:14) በማለት ወደፊት ልንዘረጋ ይገባል።

2. «እባርክሃለሁ»

- ዘፍጥረት 12:2

እግዚአብሔር እርግማን የለውም! በክርስቶስ ኢየሱስ በማመናችን ምክንያት የአብርሃም በረከት ወራሾች እንድንሆን የተጠራን ቅዱሳን የተጠራነው ለበረከት ነው እንጂ ለመርገም አይደለም። ስለዚህ፣ ምንጩ ምንም ይሁን

ምንም፣ በሕይወታችን ምንም አይነት እርግማን እንዲሰለጥንብን የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም። መርገም ተሽሮ በረከት ታውጇልናልና!

እግዚአብሔር እኛን ለመባረክ የወሰነበት ዋነኛ ምክንያቱ እኛን መባረክ ስለሚወድ መሆኑ ባያከራክረንም፣ የባረከን እርሱ የበረከት አምላክ መሆኑን ለማስመስከርና የእርሱን በጎነት እንድናስመሰክርም ጭምር ነው። እግዚአብሔር የበረከት አምላክ እንደሆነና ወደ እርሱ የተጠጋና ስሙን የሚፈራ ሰው ከበረከቱ እንደሚካፈል በእኛ እንዲታይ ይህ የጌታ ሃሳብ ነው።

ቃሉ፣ «በአንተ ለሚያምኑ በሰው ልጆች ፊት ያዘጋጀሃት ለሚፈሩህም የሰወርሃት ቸርነትህ እንደምን በዛች» (መዝ. 31:19) እንደሚል፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ላመኑትና ስሙን ለሚፈሩ ሁሉ የአብርሃም በረከት ተወስኖላቸዋል። ይህም በረከት በሰው ልጆች ፊት ሊገለጥ በእግዚአብሔር ግምጃ ቤት ውስጥ ተሰውሮ ተቀምጦአል።

3. «ስምህንም አከብረዋለሁ»

- ዘፍጥረት 12:2

እግዚአብሔር የውርደት ጥሪ የለውም! እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ መንግስቱ የጠራቸውን ልጆቹን ሊያከብር፣ ከፍ ሊያደርግና ወደ እርሱ ክብር ሊያስጠጋ እንጂ ሊያዋርድ አልጠራቸውም። እግዚአብሔር ልጆቹን በማክበሩ ምክንያት የእርሱ ክብር እንደማይነካበት ያውቃል። ስለዚህም፣ በስሙ የሚያምኑትን ከክብር ወደ ክብር ይወስዳል።

እግዚአብሔር ልጆቹን በማክበር ይደሰታል ምክንያቱም በዚያ ውስጥ ለስሙ ክብር እንደሚመጣ ስለሚያውቅ ነው። እግዚአብሔር የእኛን ስም በማክበሩና በማስጠራቱ ውስጥ የእርሱን ስም የማግነን፣ የማስጠራትና የማስከበር ዓላማችን ግን በፍጹም ሊጠፋብን አይገባም። ክብራችን እሱ እንደሆነና ከነበርንበት ስፍራ ወጥተን አሁን ያለንበት የክብር ቦታ የመግባታችን ምንጩ እሱ መሆኑን ስንዘነጋ መዝቀጥ እንጀምራለን።

«የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል» (ዮሐ. 12:26) የሚለው ቃሉ እውነተኛና የታመነ ነው። ከዚያም ጋር፣ «የጠራቸውንም . . . አከበራቸው» (ሮሜ 8:30) የሚለውም ቃል የማይናወጥና የጸና ነው። ስለዚህም፣ በክርስቶስ ኢየሱስ የደረሰን እግዚአብሔርን የመከተልና የማገልገል ጥሪ አጥብቀን ስንይዝ፣ የእርሱም ክብር በእኛ ላይ በጸና ሁኔታ እንደሚፈስስ ልናስታውስ ይገባናል።

4. «ለበረከትም ሁን...የምድርም ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ»

- ዘፍጥረት 12:2-3

እግዚአብሔር የመርገም መልእክተኛ የለውም! በእግዚአብሔር የተጠራና የእርሱን መልእክት ይዞ የተላከ ሰው ለሌሎች የበረከትን እንጂ የመርገምን ነገር አያስተላልፍም። በእግዚአብሔር መልእክተኛ ውስጥ ያደረው መንፈስ ለተጠንቶና ለሰሙት ሁሉ በረከትን የሚያመጣ፣ ከአበሳ የሚያወጣና ለተሻለ ህይወት ልቦናን የሚያነቃ መንፈስ ነው።

እግዚአብሔር በጠራቸው ባሪያዎቹ ውስጥ አድሮና የበረከትን መልእክት ሞልቶ የሚልከው እሱን የታመነና የታዘዘ ለሌላው የሚተርፍን በረከት እንደሚላበስ ለትውልድ ሁሉ ለማሳየት ነው። በዚህም ሁኔታ ውስጥ፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ጥሪ እንዲያከብሩና መጠራትን እንዲናፍቁ ታላቅ የሆነን መለኮታዊ ተጽእኖ ያመጣል። የተጠራ ሰው ተባርኮ ሌሎችን ለመባረክ የተመረጠ ሰው ነው።

«ከነገድ ሁሉ ከቋንቋም ሁሉ ከወገንም ሁሉ ሰዎችን ዋጅተሃል ለአምላካችን መንግስትና ካህናት ይሆኑ ዘንድ አደረግሃቸው» (ራእ. 5:9-10) የሚለው የእግዚአብሔር ቃል አዋጅ የሚፈጸመው፣ «ለበረከት ሁን» ተብሎ በተጠራ ሰው አማካኝነት ነው። ነገድ፣ ቋንቋና ወገን የማይለየው ይህ ጥሪ ባሰፋንለት መጠን ሰፍቶ የሚሄድና ለብዙዎች በረከት የሚሆን ጥሪ ነው።

5. «የሚባርክህን እባርካለሁ፣ የሚረግመህንም አረግማለሁ»

- ዘፍጥረት 12:3

እግዚአብሔር ጠርቶ መተው የሚባል ወረት የለውም! እንደ አብርሃም ካለበት የተደላደለ ሁኔታ ወጥቶ የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል የወሰነን ሰው የሚጋፉ በርካታ የክፉ ኃይሎች እንዳሉ እሙን ነው። በዚያው መጠን ደግሞ የእግዚአብሔር ሃሳብ የጸናች ነች፡- ቢባርኩን ሊባረኩ፣ ቢረግሙን ደግሞ ሊረገሙ ትእዛዝን አስተላልፏል።

እግዚአብሔር የጠራን ጥሪ መለኮታዊ ጥበቃን በላያችን ላይ የሚያስቀምጥ ጥሪ ነው። ጌታ ወደ እርሱ ሃሳብ የጠራውን ሰው ለመባረክ ብቻ ሳይሆን በዚያ ሰው ላይ ከየአቅጣጫውም በሚነሳበት ክፉ ላይ ለመፍረድም

ጭምር ይህ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው። እርሱን ብሎ የወጣን ሰው የሚጠብቅ የእስራኤል አምላክ አይተኛም፣ አያንቀላፋምም።

እግዚአብሔር በፍጹም ለጠላት አሳልፎ አይሰጠንም። ይልቁንም፣ «በእርሱም ከጠላቶቻችን እጅ ድነን በዘመናችን ሁሉ ያለፍርሃት በቅድስናና በጽድቅ በፊቱ እንድናገለግለው ሰጠን» (ሉቃ. 1:74-75)። ስለዚህም በክፋት በተያዘች በዚህች ዓለም ውስጥ ታላቁንና የተከበረውን ጌታ እንወክል የእሱ ሕልውና ለጥበቃ በእኛ ላይ እንዳለ በማመንና በማወቅ እንድንመላለስ ያስፈልጋል።

ምስጢሩ ግን ያለው እዚህ ላይ ነው፡- የአብርሃምን በረከት ለመውረስ በክርስቶስ በማመን የአብርሃም ልጅ መሆን ብቻ ሳይሆን የአብርሃምን ጎዳና መከተል አስፈላጊ ነው። ጥሪያችን የአብርሃምን በረከት የመውረስ ብቻ ሳይሆን የአብርሃምን መንገድ የመከተልም ጥሪ ነው። እርሱ የወረሰውን በረከት ለመውረስ፣ እርሱ ባመነው አምላክ ማመን፣ እርሱ የከፈላቸውን ዋጋዎች መክፈልና፣ የተከተላቸውን መርሆች መከተል አስፈላጊ ነው።

ወደ ጥናታችን ጠልቀን ስንገባ፣ ከሁሉ በፊት የአብርሃምን የጥሪ ባህሪያት በሚቀጥለው ምእራፋችን ውስጥ በሰፊው እንመለከታለን።

ምዕራፍ ሁለት

የአብርሃም ጥሪ ባህሪያት
(ዘፍጥረት 12)

«ሀንድሞች ሆይ፣ መጠራታችሁን ተመልከቱ» (1ቆሮ. 1:26)።

አብርሃም ለመጀመሪያ ጊዜ በተጠቀሰበት በዘፍጥረት ምእራፍ 12 ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ጥሪ ባህሪያት ብዙ እውነታዎችን እንማራለን። እግዚአብሔር አብርሃምን ለሚያስገርም የበረከት ሕይወት ሲጠራው የሰጠውን ትእዛዝ፣ የተናገረውን ነገርና አብርሃምም የመለሰውን ምላሽ ስናጠና ስለ እግዚአብሔር ጥሪ ባህሪያት ብዙ ተግባራዊ ትምህርቶችን እንቀስማለን።

አብርሃም የኖረበት ዘመን የሰዎች ቋንቋ የተደባለቀበት፣ ጌታም በሰው ዘር ክፋት ልቡ ያዘነበት ዘመን ነበር። ሰዎች ረኃድም እድሜ እየኖሩ ነገር ግን ተጽእኖን ማምጣት በተሳናቸው ዘመን ነበር አብርሃም ወደዚህ ጥሪ የመጣው። ሰዎች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ብዙ ዘመን የመኖር እድል ባለመጠቀም ምንም ታሪክ ሳያስመዘግቡና ከመብላትና ከመጠጣት ሳያልፉ በኖሩበት በዚያ ዘመን ነበር እግዚአብሔርም አንድ ሰው ለማግኘትና የምድርን ታሪክ ለመለወጥ ወስኖ የተነሳው። አብርሃም ተገኘ!

እግዚአብሔር ወደ አብርሃም መጥቶ በህይወቱ የነበረውን አላማ ሲገልጥለት አመጣጡን፣ የጥሪውን አገላለጥና የጥሪውን አቅጣጫ ስንመለከት የአብርሃምን በረከት ለመውረስ ለተጠራን የዚህ ዘመን ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ጥሪ ባህሪያት ብዙ መገለጦችን ያበራልናል።

የእግዚአብሔርን የጥሪ ባህሪያት ማወቅ ጥሪ እንዳለን የማወቅን ያህል አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም ጥሪ እንዳለን አውቀን ያወቅነው ጥሪ በምን መልኩ

እንደሚሰራ ካላስተዋልን ከጌታ ጋር ልንተላለፍና ለብዙ ግራ የመጋባት መንፈስ ልንጋለጥ ስለምንችል ነው። የእግዚአብሔር የመውረስ ጥሪ እንዴት ነው የሚመጣው?

1. በሁኔታዎች መናጋት ውስጥ የሚገለጥ ጥሪ

«ታራም በካራን ሞተ . . . እግዚአብሔርም አብራምን አለው»

- ዘፍጥረት 11:32 - 12:1

እግዚአብሔር ጥሪውን ለማስተዋወቅ የሁኔታዎችን ለውጥ ይጠቀማል። አብርሃም በደመቀና በሞቀ የቤተሰብ ትስስር ውስጥ ያደገ ሰው ለመሆኑ ዘፍጥረት ምእራፍ አስራ አንድን ማንበብ በቂ ነው። አባት፣ አያትና ቅድመ አያት የተከማቸበት ቤት ውስጥ ያደገው አብርሃም በድንገት አባቱን አጣ። በዚያን ጊዜ ይመስላል እግዚአብሔር ለአብርሃም የነበረውን ጥሪ ለማስተዋወቅ የአድል መስኮት ያገኘው። ምናልባት አባቱ በሕይወት ቢኖር ኖሮ አብርሃም የእግዚአብሔርን የመውጣት ጥሪ ማስተናገድ ይከብደው ይሆን? መልሱን በእርግጠኝነት ባናውቅም፣ በአጋጣሚ የማይሰራው እግዚአብሔር ግን በትክክለኛው ጊዜ ወደ አብርሃም እንደመጣ እርግጠኞች ነን።

አንድን እውነት እርግጠኞች መሆን እንችላለን፣ አለልን የምንለው የምንመካበት ሁኔታና ሰው የጌታን ጥሪ በቅጡ እንዳንሰማ ጥላን ሊያጠላብን ይችላል። ምናልባት የሚደርሰን ጥሪ ከእነዚህ ከምናደንቃቸውና በሕይወታችን ትልቅ ስፍራ ከያዙ ሰዎች ወይም ሁኔታዎች የመለየትን ትእዛዝ ይዞ ከመጣ ምላሽ የመስጠታችን ጉዳይ አጠራጣሪ ሊሆን ይችላል።

በአንጻሩ፣ ጌታ መስራት ቢፈልግ እነሱ እያሉለት ወደ እኔ አልፎ ሊመጣ አይችልም የምንላቸው ታላላቅ ሰዎች ጥሪውን እንዳንሰማ ሊያደርጉንም ይችላሉ። ከእኔ የሚበልጥ ሰው እያለ እግዚአብሔር እንዴት ወደ እኔ እንዲህ አይነት ታላቅ ጥሪ ይዞ ሊመጣ ይችላል የሚል ስሜት በቀላሉ ሊያጠቃን ይችላል። ስለዚህም ድምጹን እንድንሰማ ሃሳባችንን ለመሳብ ጌታ ዙሪያችንን ሊያናጋ ይችላል። አለልን፣ አለኝ፣ ተመችቶኛል፣ ደስ ይላል፣ እና ባልተለየኝ የምንላቸውን ነገሮች ከፊታችን ለጊዜው ወይም በቋሚነት ሊወስዳቸው ለድምጹ ክፍት ሆነን ያገኘንና ጥሪውን ያስተላልፋል።

እግዚአብሔርን ለሚወዱና እንደ ሃሳቡም ለተጠሩ የሁኔታዎች መናጋትና መወሰድ ለበጎ እንደሚሆን እናምናለን። ጊዜ ስንሰጠውና ሲገባን

በማጣታችን ምክንያት ለጥሪው ምላሽ እንድንሰጥ ከእኛ ስለተወሰደው ነገር ጌታን ወደማመስገን መንገድ እንመጣለን። ሊናወጥ የሚገባው ነገር ሁሉ ተናውጦና ፈርሶ የማይናወጠው ፍጻሜአችን ላይ እንድንገባ ጌታ ነገሮችን ሊያናጋ የመቻሉ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው (ዕብ. 12:27)።

2. ከተመቸን ስፍራ የመውጣት ጥሪ

«ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ . . . ውጣ»

- ዘፍጥረት 12:1

የእግዚአብሔር ጥሪ ከተመቸን ስፍራ የመውጣት ጥሪ ነው። አብርሃም የእግዚአብሔርን ጥሪ በሙላት ለመፈጸም ከሚኖርበት ስፍራ መውጣት ነበረበት። የነበረበት ስፍራ የሚመቸው፣ የለመደውና በተቻለው መጠን ሊለቅቀው የማይፈልገው ስፍራ ነው። ጥሪው ግን ያንን ስፍራ የመልቀቅ ጥያቄ ይዞ መጣ። ለአብርሃም የሚቀለው ሁኔታ ባለበት ስፍራ በመሆን የለመደውን ነገር ማከናወን መሆኑ እሙን ነው። የለመደው ስፍራ፣ የለመደው ቤት፣ የለመዳቸው ወዳጆችና የተለመደ የኑሮ ሂደት ለአብርሃም ተመችቶታል። የእግዚአብሔር እጅንዳ ግን ለየት ያለ ነበር።

የእግዚአብሔር ጥሪ ከምንወዳቸው ወገኖቻችን ሊለየን ይችላል። ይህ ጥሪ ሰዎችን የመጥላት ጥሪ ሳይሆን ከእነሱ የመለየት ጥሪ ነው። ጥሪው ከምንወደው ስፍራም እንድንለይ ሊያደርገን ይችላል። ከዚያም አልፎ ማድረግ ከምንወደው ተግባር እንድንለይ ጥያቄ ሊያቀርብልን ይችላል። የተለመደን ተግባር እያደረግን ያልተለመደን መለኮታዊ አሰራር ለማስተናገድ በማይቻልበት ጊዜ እግዚአብሔር ከተመቸን ስፍራ የመውጣትን ጥሪ ያመጣል።

የእግዚአብሔር ጥሪ ከተመቻችንበት ስፍራ ሊለየን የሚመጣበት ምክንያቱ በዚያ በተመቻችንበት ስፍራ ጥሪውን የማሟላታችን ሁኔታ እውን እንደማይሆን ስለሚያውቅ ነው። ጥሪው ከተደላደልንበት ሁኔታ እንድንወጣ ቢያዘንም ከሕይወታችን ግን በፍጹም አያፈናቅለንም። ጥሪው የመቅበዝበዝና የመንከራተት ጥሪ ሳይሆን ለእኛ ተመችቶ ለጌታ ግን ከማይመች ሁኔታ የመውጣት ጥሪ ነው።

የእግዚአብሔር ጥሪ የምንወደውን ነገር፣ ኃጢአት እንኳን ባይሆን፣ እንድንተው ሊያዘን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ሌሎች አማኞች ሲያደርጉት ያልተወቀሰበትን ጉዳይ የእኛ የጥሪ ጥልቀት ግን ሊከለክለን ይችላል። የከበረ

ጥሪ የከበረን ኑሮንና ውሎን ስለሚጠይቅ ላነሰ ፍጻሜ ራሳቸውን የሰጡ ሰዎች ያልተከለከሉትን እኛ ግን ልንከለከል እንችላለን። ምርጫው ግን የእኛው ነው።

እኛ ላይመቸን እግዚአብሔር ግን ለመስራት እንዲመቸው ስናደርግለት ሕይወት ይሰምራል። እግዚአብሔርም በሕይወታችን ሊሰራ ያቀደው ነገር ወደመከናወን ይመጣል። በዘመኑ ተጽእኖን ለማምጣት የተጠራ ሰው የሚሄድበት ጎዳና የብቸኝነት ሊሆን እንደሚችል አውቆ ልቦናውን ማዘጋጀት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

3. ሁሉን ነገር በአንድ ጊዜ ግልጽ አድርጎ የማይመጣ ጥሪ።

«እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ»

- ዘፍጥረት 12:1

የእግዚአብሔር ጥሪ ሁሉን ነገር በአንድ ጊዜ ግልጽ አድርጎ አይመጣም። አብርሃም ከእግዚአብሔር ጥሪን ሲቀበል፣ ወዴት እንደሚሄድና እንዴት እንደሚሄድ፣ እንዲሁም ደግሞ የት ምን እንደሚገጥመው ሁሉን መረጃ የያዘ ንግግር መስማትን እንደሚመኝ መገመት አያስቸግርም። ጌታ ሲናገረው ግን እነዚህን የተለመዱ ነጥቦች ይዞ አልመጣም። «እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ» ነበር የተባለው። የተለመደውን ማንኛውም ሰው ሊያገኝ የሚፈልገውን የእርግጠኝነት መልእክት ስላላገኘ በልቡ ጥያቄ ላይፈጠርበት የቀረ አይመስልም። አብርሃም ግን ለጥሪው ምላሽ ከመስጠት አልተመለሰም።

እግዚአብሔር ጥሪውን ሲያስተዋውቀን የፍጻሜአችንን መልካምነትና ታላቅነት በማሳየት እንጂ እያንዳንዷን እርምጃ በማሳየት አይመራንም። የጠራን የታመነ እንደሆነ በማመን በእሺታ መንፈስ መታዘዝ ከእኛ ይጠበቃል። እግዚአብሔር በመንገዳችን ላይ የሚገጥመንን ተግዳሮት ሁሉ ተንትኖና አስረድቶ ቢያስጀምረን ኖሮ ጎዳናችንን መጀመራችን አጠራጣሪ ይሆናል።

ውጡ ወደተባልንበትን ስፍራ ለመሄድም ሆነ አድርጉ የተባልነውን ተግባር ለመተግበር የመጀመሪያዋን እርምጃ ስንወስድ መግለጥ የሚፈልገውን የሚቀጥለውን ደረጃ እርሱ ራሱ ይገለጥልናል። የእኛ ሃላፊነት አድርጉ የተባልነውንና በጊዜው የተገለጠልንን በማድረግ መታዘዝ ሲሆን የቀረውን ማከናወንና መቆጣጠር ደግሞ የጠሪያችን የጌታ ሃላፊነት ነው።

በየቀኑ በጌታ ላይ የመደገፍ እርምጃ የእውነተኛ ጥሪ ምልክቱ ነው። ሁኔታዎች ሲጠሩን ምቹ ነገር ያላዩናል። ምላሻችንንም የሚያነሳሳው የምናየው

የተመቻቸ ሁኔታ ነው። በእንጻሩም፣ የተጠራነው በሰው ሲሆን ከጠራን ሰው ጋር ተግባብተንና ምን እንደምንጠብቅ ተነግሮን፣ ከተስማማን ልንወስደው ካልተስማማን ልንተወው ጥሪ ይቀርብልናል። የሁኔታዎችና የሰዎች ጥሪ ግን ምንም እንኳን ከመጀመሪያው የወደፊቱን አስረግጦ ነግሮን ቢያስጀምረንም ዘላቂነቱ አስተማማኝ ያልሆነ ጥሪ ነው። ሁሉን ቻይና በሕይወታችን ላይ ሙሉ ስልጣን ያለው ጌታ ግን ጥሪን ሲያመጣ ለሚናገረው ሁሉ «አሜን» ብለን እንድንታዘዘው ይመጣል። የሚበጀን ይህ አይነቱ መታዘዝ ነውና።

4. የብዙዎችን ፍጻሜ የሚነካ ጥሪ

«ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፣ አባርክሃለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ፣ ለበረከትም ሁን፣ የሚባርኩህንም አባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም አረግማለሁ፣ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ»

- ዘፍጥረት 12:2-3

ለእግዚአብሔር ጥሪ የምንሰጠው ምላሽ ክፉ ወይም መልካም ውጤት አለው። አብርሃም ከጌታ የተቀበለው ጥሪ ዋጋ የመክፈልና ከለመደውና ከተመቸው ስፍራ የመውጣት ብቻ ሳይሆን ዋጋ የሚከፍልና የሚመችን ስፍራ የሚሰጥም ጭምር ነው። ነገር ግን ምስጢሩ እዚህ ላይ ነው። ዋጋ እንዲከፈለው በቅድሚያ እሱ ዋጋ መክፈል ነበረበት። ስፍራ እንዲሰጠው በቅድሚያ እሱ ስፍራውን መልቀቅ ነበረበት። የብዙዎች አባት እንዲያደርገው እሱ የአባቱን ቤት ትቶ መሄድ ነበረበት። እንዲያከብረው እሱ በቅድሚያ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሊመጣ የሚችለውን ጊዜአዊ መዋረድ ለመቅመስ ራሱን መስጠት ነበረበት። ይህ ጥሪ የአብርሃም ጥሪ ይባላል።

እግዚአብሔር ተራ ጥሪ የለውም፤ የታላቅነት፣ የመባረክና የመክበር እንጂ። አንድ በክርስቶስ አምኖ ዳግም የተወለደ ሰው በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ያለውን ስፍራ አውቆና ለዚያም ምላሽ ሰጥቶ ሲመላለስ የሚገባበትን የክብር ሕይወት የሚመስል ክብር የትም አይገኝም። አይን ያላየውና ጆሮ ያልሰማው፣ በማንም ሕይወት ተከናውኖ የማያውቅ ልዩ ነገር ለአያንዳንዱ ልጆቹ ጌታ አለው። ይህንን እውነት ግን አምኖና በመንፈስ መርምሮ ወደ መታዘዝ ጎዳና መግባት የእኛ ድርሻ ነው። ሆኖም በስጋ አይን የማይታይና በብዙዎችም ሲታይ ዝናን ያተረፈ ጎዳና ስላልሆነ ከሚታዘዙት የማይታዘዙት በልጠው ሲገኙ ይታያል።

እግዚአብሔር በሕይወታችን ለሚመጣው ጥሪ ምላሽ መስጠትም ሆነ አለመስጠት ምርጫው የእኛ ነው። እግዚአብሔር ጥሪን ካስተላለፈ በኋላ ምላሽ እስክንሰጠው ድረስ ይጠብቃል። ለዚህ ጥሪ መታዘዛችንም ሆነ አለመታዘዛችን የእኛን ብቻ ሳይሆን የብዙዎችን ሰዎች የሕይወት ፍጻሜ የሚወስን ጉዳይ ነው። ቀድሞውኑ እግዚአብሔር በራስ ተጀምሮ ራስ ላይ የሚያልቅ ጥሪም በረከትም የለውም። የሚሰጠን ጥሪም ሆነ በረከት የእኛን ጽዋ እንዲሞላና እንዲትረፈረፍ አድርጎ ወደ ሌሎች ዘልቆ የሚገባና ለትውልድ የሚደርስ ጥሪ ነው።

ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ የሚሰጥና በሙሉ ልቡ የሚታዘዝ ሰው የጥሪውና የመታዘዙ ጥልቀት ከማንኛውም እርግማን ይከልለዋል። ጥሪና ውድቀት፣ ጥሪና እርግማን፣ ጥሪና ውርደት፣ ጥሪና መቅበዝበዝ አብረው የማይሄዱ ጉዳዮች ናቸው። ጥሪው የበረከት ጥሪ ነው። ይህም በረከት ከእኛ አልፎ ለሌሎች ሊደርስ ስለሚገባው የእኛ አለመታዘዝ ብዙዎችን ከበረከት እንደሚከለክል ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው። የእኛ መታዘዝ በብዙዎች ላይ ለውጥን፣ እንደውም ዘላለማዊ የሆነ ለውጥን እንደሚያስከትል ሲገባን ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ የመስጠታችንን ጉዳይ በቁም ነገር መውሰድ እንጀምራለን።

5. ያለንን ፈልገው የሚጣበቁ ሰዎች የሚሳቡበት ጥሪ

«አብራምም እግዚአብሔር እንደነገረው ሄደ፣ ሎጥም ከእርሱ ጋር ሄደ»

- ዘፍጥረት 12:4

የእግዚአብሔር ጥሪ ሲመጣ ተጣብቆን ሊሄድ የሚፈልግ ሰው ወይም ነገር አይጠፋም። አብርሃም የጌታን ጥሪ ታዝዞ መራመድ ሲጀምር ሎጥ የተሰኘው ወንኑ ከእርሱ ጋር ጉዞ ጀመረ። ሁኔታውም ከዘመዶችህ ተለይ የሚለውን ትእዛዝ በቀጥታ የሚጻረር ነበር። አብርሃም ምናልባት ሁኔታው ለክፉ አይሰጥም ብሎ አስቦ ሊሆን ይችላል። ሎጥ ግን ብዙም ሳይቆይ የስቃይና ወደ ኋላ የመጎተት ምክንያት ሲሆንበት እናስተውላለን። ሎጥ ካለማቋረጥ ከአብርሃም ጋር ያለመስማማቱን ሁኔታ ስናጤን ምናልባት ሎጥ የፈለገው አብርሃምን ሳይሆን የአብርሃምን በረከት ብቻ ይሆናል የሚል ግምት ውስጥ ይከተናል።

እግዚአብሔር ወደ አንድ ደረጃ ሊያሻግረን ሲፈልግ ወደዚያ ከፍታ እንዳንደርስ ከሚጋፉን የተለመዱ እንቅፋቶች አንዱ ከማይመች ሰው ጋር በወዳጅነት ቀንበር መጠመድ ነው። ጌታ ወደ መንግስቱ ሲጠራንና ለእኛ ወዳሰበው ፈቃዱ ሊያስገባን ሲጀምር ከሁሉ አስቀድመን መመለስ የሚገባን ጥያቄ በአካባቢያችን ያሉ ሰዎች ለዚያ ጥሪ እንትፋት የመሆናቸውንና ያለመሆናቸውን ጉዳይ ነው። ለጥሪያችንና ጌታ ሁኑ ላለን ነገር የማይመችን ሰውና ሁኔታ የማስወገዱን ጉዳይ ጌታ በእኛ ላይ ነው የሚጥለው።

በዙሪያችን ያሉት ሰዎች እነማን እንደሆኑ የሚለይን መንፈስ ከእግዚአብሔር በመጠየቅ በማስተዋል ካልተመላለስን ጌታ ወዳሰበልን ሃሳብ እንዳንገባ ዘመኑን ያራዝምብናል። ከማን መለየት እንደሚገባንና ከማን ጋር አብረን ልንቆይ እንደሚገባን ለመለየት ከእግዚአብሔር መንፈስ ጋር እጅግ የተቆራኘ ህይወት ያስፈልገናል። የእግዚአብሔር መንፈስ ካመላከተን ሰው እስክንለይ ድረስ ወደጌታ ሃሳብ የመግባታችን ሁኔታ ይራዘማል እንጂ አለማምደንና አታልለን ለማለፍ በፍጹም አንችልም። በሕይወታችን የሚከብቡን ሰዎች ገሚሶቹ ወደ ፍጻሜአችን የሚገፉን ሲሆኑ ገሚሶቹ ደግሞ ከፍጻሜአችን ሊያወጡን የሚጋፉን ሊሆኑ ይችላሉ። ይህንንም ጉዳይ የሚለየው በእኛ ውስጥ ያለው መናፍስትን በትኖ የሚያውቀው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። ይህንን መንፈስ ብንፈቅድለትና በሙላት በውስጣችን ቢሰራ ከወደፊት ችግርና ከፍጻሜ ከመጉደል እንጠበቃለን።

6. ከለመድነው ተራ መንገድ የመውጣት ጥሪ

«እንግዲህ በአንቺ ምክንያት መልካም ይሆንልኝ ዘንድ፣ ስለአንቺም ነፍሴ ትድን ዘንድ፡- እኅቴ ነኝ በይ»

- ዘፍጥረት 12:13

የእግዚአብሔር ጥሪ ሲመጣ በለመድነው መንገድ ለችግር መፍትሄ መፈለግና ማግኘት አንችልም። አብርሃም ለጥሪው ምላሽ ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንደጀመረ አንድ ስጋት ገጠመው። በሚስቱ በሳራ ምክንያት ሕይወቱ በአደጋ ላይ የሚወድቅ መሰለው። በእግዚአብሔር ጥሪ ያልበሰለውና ለጋ የሆነው አብርሃም ይህንን ችግር ለመፍታት የተጠቀመበት መንገድ ምናልባት ቀድሞ «በዓለም» ላለ የሚያውቀው መንገድ ይሆናል። ሳራን ገንዘባቸው ለማድረግ እሱን መግደል ካለባቸው እንኳ እንደሚገድሉት መስሎታል። ስለዚህም ከሳራ

ጋር ያላቸውን የትዳር ትስስር በመደበቅና እሷን አሳልፎ መስጠት ካለበትም ያንን አድርጎ ነፍሱን ማትረፍን ፈለገ። መጨረሻውን ያሳመረለት ይህ የውሸት ጎዳናው ሳይሆን እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባቱ ምክንያት መሆኑን ከታሪኩ እንገነዘባለን።

አንድ ሰው ወደ እግዚአብሔር ሃሳብ ከመግባቱ በፊት ብዙ የኑሮና የዓላማ መሰናክሎችን አልፎ እንደመጣ እሙን ነው። ሆኖም ቀድሞ ለችግሮች ይሰጥ የነበረውን የምላሽ ዘይቤ ወደ እግዚአብሔር ሃሳብ ከገባ በኋላ ለተጠራበት የጥሪ ክብር የማይመጥን ሆኖ ሊያገኘው ይችላል። የቀድሞው አመለካከት ለቀድሞው ጉዞ የሚመጥን ቢሆንም ወደ ተልእኮውና አምላኩን ወደ መታዘዝ ከገባ በኋላ ላያስኬደው ይችላል። ጥሪውና ተልእኮው ውስጥ የገባ ሰው አመለካከቱንም የለወጠ ሰው ነውና።

የእግዚአብሔር ሰው ቀድሞ እንደሚዋጋ መዋጋት፣ ቀድሞ እንደሚናገር መናገር፣ ቀድሞ እንደሚያስብ ማሰብ አይችልም። እግዚአብሔር ለሰጠው ጥሪ ምላሽ እንዲሰጥ ያደረገው መለኮታዊው ጉልበት ያንንም የቀደመውን አሮጌ አደራረግ ማስጣል የሚችል ጉልበት አለው። እያንዳንዱ እርምጃው በጠራው በእግዚአብሔር እንደሚመራ ስለሚያውቅ፣ ከአቅሙ በላይ ለሆነ ነገር ሊንበረከክ አይገባውም። ይልቁንስ ውጊያ ሲበዛ ሊንበረከክ የሚገባው በጠራው በጌታ ፊት ነው።

7. መለኮታዊ እርዳታ የማይለየው ጥሪ

«እግዚአብሔርም በአብራም ሚስት በሦራ ምክንያት ፈርዖንንና የቤቱን ሰዎች በታላቅ መቅሰፍት መታ»

- ዘፍጥረት 12:17

የሰጠንን ጥሪ እንድናከናውን እግዚአብሔር ማድረግ ያለበትን ነገር ያደርጋል። አብርሃም እግዚአብሔርን በመታዘዝ የጀመረው ጉዞ መሰናክል የሌለበት ጎዳና አልነበረም። ጠላት የአብርሃምን ሃሳብ እግዚአብሔር ካሳየው መንገድ ላይ ለማንሳት ምን ቢጠቀም እንደሚሳካለት ያወቀበት ይመስላል። ውብ የሆነችውንና የጥሪው ፍጻሜ የሚመለከታትን ሚስቱን ከእጁ ለማውጣትና በዛም ምክንያት እሱም ከጥሪ ጎዳና እንዲወጣ በቂ አቅድ ያወጣለት ይመስላል። አብርሃም እንደፈራው ሚስቱን ሳራን ከመነጠቅ

አላመለጠም። ያን ጊዜ ነበር የጠራው እግዚአብሔር ለባሪያው ጠበቃ ሆኖ የተነሳው። በአብርሃም መንገድ ላይ የቆመውን ፈርኦንን በቁጣው ቀሰፈ።

ከተከሰተው ሁኔታ እንደምናስተውለው፣ የእግዚአብሔርን ጥሪ ተከትለን በምንሄድበት ጎዳና ላይ ለሚገጥመን ተግዳሮት ሙሉ ሃላፊነቱን የሚወስደው የጠራን እግዚአብሔር እንደሆነ ነው። እሱ ያዘዘንን በሚገባ ስናደርግ እሱም በበኩሉ የሚገባውን ያደርግልናል። መወገድ ያለበትን ያስወግዳል፤ መንቀል ያለበትን ይነቅላል፤ መቀጣት ያለበትንም ደግሞ ይቀጣል። በአጭሩ፣ እግዚአብሔር በጠራቸው ባሪያዎቹ ሕይወት ዓላማውን ለመፈጸም ሲል በመንገድ የሚቆመውን ሁሉ ያስወግዳል።

እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም ሲል ለባሪያዎቹ በሰዎች ዘንድ ሞገስን ይሰጣል። ይህ ሊለወጥ የማይችልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ያለው እውነት ነው። የሚራሩልንን፣ የእግዚአብሔር እጅ በእኛ ላይ እንዳለ አውቀው መንገድ የሚለቁልንንና ስለእኛ ነገር ግድ የሚላቸውን ሰዎች የሚያዘጋጅ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ዓላማውን ለመፈጸም ሲል ሰዎችን ስለ እኛ ያዝዛቸዋል። እምቢተኞች እሺ እንዲሉ፣ ጠማሞች እንዲቀኑና ጨካኞች እንዲራሩ የሚሆነው እግዚአብሔር በእኛ ላይ ካስቀመጠው መልካም ነገር የተነሳ ነው።

እግዚአብሔር በቅዱሳን ሁሉ ላይ ያስቀመጠው ጥሪ አለ። ይህም ጥሪ የአብርሃምን ዘረክት የመውረስ ጥሪ ነው። በዚህ ምእራፍ ውስጥ ለመመልከት እንደሞከርነው ይህን የአብርሃምን ዘረክት ለመውረስ የአብርሃምን የጥሪ መንገድ መከተል አስፈላጊ ነው። ስለዚህም የዚህን ጥሪ ባህሪያት ተመለከትን። በሚቀጥለው ምእራፍ ከእኛ የሚጠበቀውም ጥሪአችንን የሚጠበቅንና የመንከባከብን ሁኔታ እናጠናለን።

ምዕራፍ ሶስት

የአብርሃምን ጥሪ መንከባከብ
(ዘፍጥረት 13-14)

«በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ አለምናችኋለሁ» (ኤፌ. 4:1)።

«ወደ መንግስቱ ወደ ክብሩም ለጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ» (1ተሰ. 2:12)።

ጌታ የገለጠልንን መለኮታዊ ጥሪና ዓላማ በአግባብ የመያዛችን ጉዳይ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በእጃችን የገባውን የእግዚአብሔር ሃሳብና በረከት አያያዛችን በሕይወታችን የመውደቃችንንና የመነሳታችንን ሁኔታ ይወስናል። የሕይወታችን ልምምድ፣ አመለካከታችንና ለሚመጣው ሁኔታ ሁሉ የምንሰጠው ምላሽ በጥሪያችን ላይ ቀጥተኛ የሆነ ተጽእኖ አለው። ከዚህም በተጨማሪ በቃሉ የተማርናቸውን እውነቶች የማመናችንንና የመለማመዳችን ሁኔታም በጥሪያችንና በፍጻሜአችን ላይ ታላቅ ስፍራ አለው።

ለአማኝ ሁሉ በክርስቶስ በኩል እንዲሁ የታደለው የአብርሃም በረከት በአብርሃም የጥሪ መንገድ ካልተጓዝን በቀር እንዲሁ አይመጣም። ልናስተውላቸው ከሚገቡን አስፈላጊ እውነታዎች አንዱ ሰዎች በእኛ ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ነው። ከዚያም ባሻገር በመንገዳችን ላይ የሚጠብቁንን ገጠመኞች በእንዴት መልኩ እንደምንይዛቸውና ምላሽ እንደምንሰጣቸው ማስተዋል አስፈላጊ ነው። ሰዎችና ሁኔታዎች፣ ድልድይ ወይም እንቅፋት ይሆኑብናል - እንዳያያዛችን።

ከአብርሃም የጥሪ ሕይወት ከምንማራቸው ታላላቅ እውነቶች መካከል ጥሪን የመንከባከብ ጉዳይ በግልጥነት ይታያል። አብርሃም በረከቱን ለመውረስ በሄደበት ጎዳና ውስጥ እግዚአብሔር የሰጠውን ጥሪ እንዴት ነው የተንከባከበው? እኛስ የአብርሃምን በረከት ለመውረስ በምን አይነት ሁኔታ ነው ጥሪያችንን መንከባከብ ያለብን? የሚከተሉትን እውነቶች እናስተውል።

1. መውጣት ካለብን ስፍራ መውጣት

«አብርሃምም ከግብጽ ወጣ»

- ዘፍጥረት 13:1

አብርሃም በምድሩ የነበረውን ረሃብ ሸሽት ወደ ግብጽ መሄዱ እሙን ነው። ግብጽ ግን የእግዚአብሔርን በረከት እንዲወርስ የተሰጠው ስፍራ አልነበረም። የጊዜውን ችግር ለማምለጥና ለመጠለል ወደዚያ መግባቱ እግዚአብሔርን እንዳስቆጣው ባናነብም፣ በረከቱን መውረስ ካስፈለገው ግን ከግብጽ መውጣት ነበረበት። በግብጽ ለአብርሃም በረከት አልነበረም። በግብጽ ያጋጠመው ስጋት፣ ድንጋጤ፣ የቤተሰብ መናጋት፣ በእሱ ምክንያት የሰዎች መቁሰልና የመሳሰሉት ችግሮች ናቸው። አብርሃም ከዚህ ስፍራ በአስቸኳይ መውጣት ነበረበት።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የተጠራ ወገን ሁሉ ይህን ሊያስተውል ይገባል። ስንገባ ጌታን ሳናማክር የገባንበት ስፍራ ካለ ያንን እንዳወቅን በፍጥነት መውጣት አለብን። ስንገባ ጌታ መርቶን ሳይሆን ችግርን ሸሽተን የገባንበት ሁኔታ ካለ በፍጥነት መውጣት አለብን። ስንገባ ለጊዜው መፍትሄ የሰጠን መስሎን በኋላ ግን በእንግድነትና በተንጠለጠለ ሁኔታ የሚያቆየን ስፍራ ውስጥ ራሳችንን ካገኘነው በፍጥነት እንድንወጣ እንመከራለን። ስንገባ መፍትሄ የምናገኝበት መስሎን ከገባን በኋላ መፍራትና መጨነቅ ከጀመርን ከዚያ ስፍራና ሁኔታ የመውጣታችንን ጉዳይ ልናስብበት ይገባል። ስንገባ የተሰበሰበና መልካም ቤተሰብ ይዘን ከገባን በኋላ ትዳራችንና ቤተሰባችን መናጋትና መፍረስ ከጀመረ ከዚያ ሁኔታ በፍጥነት መውጣት ይበጀናል። ስንገባ መልካምነት ከገጠመንና፣ የተደረገልን መልካምነት ግን ጌታ የሰጠንን ክብራችንን የሚነጥቅ ከሆነ በፍጥነት መውጣት ይበጀናል። ስንገባ ጎሽ ብለው የተቀበሉንና ያስተናገዱን ሰዎች በእኛ ምክንያት ስቃይና መከራ ከጀመራቸው በፍጥነት መውጣቱ ያዋጣናል።

2. መለየት ካለብን ሰው መለየት

«አብራምም በከብት በብርና በወርቅ እጅግ በለጠገ . . . ከአብራም ጋር የሄደው ሎጥ ደግሞ የላምና የበግ መንጋ ድንኳንም ነበረው . . . አብራምም ሎጥን አለው፦ . . . ከእኔ ተለይ ዘንድ እለምንሃለሁ»

- ዘፍጥረት 13:2-9

አብርሃም በረከቱን ለመውረስ ከሎጥ መለየት እንደነበረበት በሚገባ ተገንዝቦ ነበር። ለዚህም ነው ምንም እንኳ ወዳጅነቱ የጠበቀ ቢሆንም የእግዚአብሔርን መንገድ ለመከተል ሲል ከሎጥ ለመለየት የወሰነው። ሎጥ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠውን ጥሪ ተገንዝቦና ያንን በመደገፍ የበረከት ምንጭ ሆኖ አብሮ ለመባረክ የወጣ ሰው አይመስልም። ሎጥ የጸብ፣ የጭቅጭቅ፣ የኋላ ቀርነትና የመሳሰሉት ለአብርሃም ከተሰጡ በረከቶች የሚጎትቱ ሁኔታዎች ምንጭ ነው። አብርሃም የነበረው ምርጫ ከሎጥ መለየት ነበር።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የተጠራን ቅዱሳን ይህንን ለመናገር ቀላል፣ ለመተግበር ግን እጅግ ክባድ የሆነ እውነት እናስተውል። አንዳንድ ሰዎች ከእኛ ጋር የመቅረባቸው ዋነኛ ዓላማ ካለአግባብ የመበልጸግና ካለን መልካም ነገር ተጠቃሚ የመሆን ነው። ከእነዚህ ሰዎች ደግሞ መለየት የግድ ነው። ጥሪያችንን፣ በረከታችንንና ለእግዚአብሔር ለማደር ብለን የሰበሰብነውን ማንነታችንን ካለአግባብ ከሚጠቀሙ ሰዎች መለየት አስፈላጊ ነው። የእግዚአብሔርን ሽክም ሳይሆን የራሳቸውንና የሰውን ሽክም እንድንሸከም ከሚያስገድዱን ሰዎች መለየት ኃጢአት አይደለም።

በየእለቱ አዳዲስ የመጨቃጨቂያ ሁኔታዎችን እያመጡ ወደ ራእያችን ከመገስገስ ይልቅ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት በመጨነቅ ብቻ ዘመናችንን እንድንፈጅ ከሚያደርጉ ሰዎች መለየት ጤናማ እርምጃ ነው። አላማችንንና ማንነታችንን ሳይቀበል ያለንን በረከት ብቻ ከሚፈልግ ሰው መለየት አምላካዊ መንገድ ነው። ዘወትር ከመወቃቀስ፣ ከመንደር ጠብ፣ ከወሬና ከሃሜት እንዳንላቀቅ ከቆለፈብን ሰው መለየት ወደ አብርሃም በረከት የመግቢያው ጠባብ መንገድ ነው።

3. ከፍላጎታችን ይልቅ ሰላምን ማስቀደም

«አብራምም ሎጥን አለው፦ እኛ ወንድማማች ነንና በእኔና በአንተ በእረኞቼና በእረኞችህ መካከል ጠብ እንዳይሆን እለምንሃለሁ»

- ዘፍጥረት 13:8

አብርሃም በሎጥ ባህሪይ መቸገሩ ግልጽ የሆነ እውነት ቢሆንም ጉዳዩን ግን በጥንቃቄ የያዘ ሰው ነበር። ጥሪውን የሚከታተል፣ እግዚአብሔርን በረከትና ኪዳን ለመውረስ በትኩረት የሚራመድ ቢሆንም እንኳን፣ ያንን ለመውረስ ግን መንገዱ የሰላም መንገድ መሆኑንም ያስተዋለ ሰው ነበር። አብርሃም ለሎጥ ምንም አይነት መልካምነት ቢያሳየውም እንኳ ጉዳዩ ለሎጥ ብዙም ትርጉም የሰጠው አይመስልም። አብርሃም ግን በግሉ ያለውን ሰላምን የመፈለግ መርህ ለመልቀቅ አልፈለገም። ሰላምን ለመፈለግ ተጨማሪ ጎዳና መራመድና ዋጋም መክፈል ስለነበረበት ያንኑ አደረገ። ምርጫውን ለሎጥ በመስጠት ስፍራን ለቀቀ፣ ታገሰ፣ ለመነ፣ መብቱን ጣለ። የአብርሃም የበረከት መንገድ ይህንን ይመስላል።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የባህሪይ ጤንነት ያስፈልጋል። ይህንን የባህሪን ጤንነት ለመጠበቅ ስንል ደግሞ ለጊዜው ከሰዎች መለየት ጤናማ እርምጃ ነው። ከዚያም አልፎ የባህሪን ጤንነት ለመጠበቅ ስንል አሳልፈን የምንሰጣቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፤ ይህ ደግሞ ክስረት አይደለም። የባህሪያችንን ጤንነት ለመጠበቅ ስንል መብታችንን ስንሰዋ መለኮት ከእኛ ጋር ይቆማል። ይህንን እናስተውል፣ የባህሪን ጤንነት ለመጠበቅ ስንል በመተዋችን ምክንያት ሰዎች በብልጠት የወሰዱብን ነገር ለእነሱ አይበጅም።

የባህሪያችንን ጤንነት ለመጠበቅ፣ በሰዎቹ ባህሪይና ክፋት ተገፋፍቶ ምላሽ ከመስጠትና አጉል ውሳኔን ከመወሰን መገታት አለብን። የባህሪን ጤንነት ከወረስን፣ በአለም ላይ መውረስ የማንችለው ነገር እንደሌለ እናስተውል። የአብርሃምን በረከት የመውረሻው መንገድ ይህ ነው። ራሳችንን ከክፉ ባህሪይና ከሚነሱብን ክፉ ሁኔታዎችና ሰዎች ክፉ ምላሽ ከመስጠት ከተጠበቅን እግዚአብሔር በባህሪያችን ስለሚያምንብን ምንም በረከት ለእኛ ከማስወረስ አይከለከልም።

4. አይንን ወደ ላይ ከማንሳት አለማቋረጥ

«አይንህን አንሳና አንተ ካለህበት ሰፍራ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ወደ ምስራቅና ወደ ምእራብ አይ፤ የምታያትን ምድር ሁሉ ለአንተና ለዘርህ ለዘላለም እሰጥሃለሁ . . . ተነሳ በምድር በርዝመቷም በስፋትዋም ሂድ አርሷን ለአንተ እሰጣለሁና»

- ዘፍጥረት 13:14-18

አብርሃም ከላይ የተጻፈልንን ድምጽ ከእግዚአብሔር ሲሰማ፤ በሕይወቱ ብዙ ሁኔታዎች አልፈዋል። ምናልባትም «እግዚአብሔርን እሺ ብሎ መከተል እነዚህን ሁሉ መከራዎች ያመጣል እንዴ?» እስኪል ድረስ መሰናክሎች እንደገጠሙት መገመት አዳጋች አይደለም። በዚህ አደናጋጭ ሁኔታ ለነበረው ለአብርሃም የመጣው ድምጽ፤ «አይንህን አንሳ . . . እይ . . . ሂድ . . . እሰጥሃለሁ» የሚል ነው። አብርሃምም አይኑን አነሳ፤ አየ፤ ሄደ፤ በመጨረሻም ወረሰ!

የአብርሃም ልጆች ሆይ ስሙኝ፡- ከእኛ ተለይቶ ስለሚሄድ ሰው፤ ከዚህ በፊት ስላልሰራን አካሄድ፤ ስለወደቅንበትና ስለተነሳንበት ጎዳናና መልካም አይደሉም ስለምንላቸው ልምምዶች ከመጨነቅ ይልቅ አይናችንን ለራእይ እናንሳ። እግዚአብሔር፤ «አይንህን አንስተህ እይ» የሚላቸው እድለኞች ብዙዎች አይደሉምና ያንን ሲናገረን ማየት የምንችለውን ያህል ትልቅ ነገርን እንይ። ውስጣችን ማየት ከቻለ መውረስ የማንችለው ነገር እንደሌለ የሚያውቅ እግዚአብሔር ቀና ብለህ እይ ሲለን ጊዜአዊውን እንተውና ዘላለማዊውን እንይ።

በማየትና በራእይ የምንወርሰው ውርስ ለዘላለም የሚሰጠን እንጂ ለጊዜው ብቅ ብሎ የሚጠፋ አይደለምና ጌታ የሚያሳየን ላይ እናተኩር። ከሁኔታችን፤ ከችግራችንና በሰዎችም ሆነ በጠላት ከሚነሳብን ወጀብ የተነሳ አቀርቅረን ወደ መሬት አንመልከት። ይልቁንም ጌታ ዛሬ የሚለንን እንስማ፤ ቀና ብለን እንመልከት፤ ቀና ብለን እንሂድ፤ ቀና ብለን እንውረስ። እግዚአብሔር «ተነሳ» ይለናልና አንቀመጥ፤ እንንቀሳቀስ፤ እንውረስ። እግዚአብሔር የሚለንን እንስማ፡- «ተነሳ በምድር በርዝመቷም በስፋትዋም ሂድ አርሷን ለአንተ እሰጣለሁና»።

5. የጥሪንና የወዳጅነትን ልዩነት መገንዘብ

«አብራምም ወንድሙ እንደ ተማረከ በሰማ ጊዜ በቤቱ የተወለዱትን ሰለጠኑ መቶ አስራ ሰምንት ብላቴኖችን አሰለፈ፤ ፍለጋቸውንም ተከትሎ እስከ ዳን ድረስ ሄደ . . . ከብቱንም ሁሉ አስመለሰ፤ ደግሞም ወንድሙን ሎጥንና ከብቶቹን ሴቶችንና ሕዝቡን ደግሞ መለሰ»

- ዘፍጥረት 14:1-16

አብርሃም አብሮ ለመኖር ከተቸገረበት ከሎጥ ከተለየ ሰንበት ብሎ ነበር። ሎጥን እንደገና ማየት ብዙም የማይጓጓበት ሁኔታዎች ተከስተዋል። አንድ ቀን ግን የሰማው ነገር አስደነገጠው፤ ሎጥ ተማርኮ ነበር። አብርሃም ምንም እንኳ በሎጥ ምክንያት ተቸግሮ ከእሱ ቢለይም አሁን ግን ለችግሩ መድረስ እንዳለበት አምኖ ነበር። ምስጢሩ እዚህ ጋር ነው። አብርሃም ከሎጥ የተለየው እግዚአብሔር የሰጠውን ጥሪ ወደ መላት ለማምጣትና ሂድ ባለው ጎዳና ለመራመድ እንጂ ሎጥን በመጥላቱ ምክንያት አይደለም። ይህንንም የውስጡን ስሜት የሚሳይበት አጋጣሚው ሎጥ በተቸገረ ጊዜ መድረስ ነበር።

የጌታን መንገድ ለመከተል ሲባል ካለምንም ጥላቻ ከሰዎች መለየት ስህተት የሌለበት ጎዳና ቢሆንም፤ ለነገ መግቢያ የሚሆንን የሰላም በር ክፍት አድርጎ መለየት ግን እጅግ አስፈላጊ ነው። ዛሬ በፍጻሜ ምክንያት የምንለየው ሰው፤ አንድ ቀን ወይ እሱ ይፈልገናል፤ ወይም ደግሞ እኛ እንፈልገው ይሆናል። በጥሪ አብሮ አለመሰለፍ ማለት ጠላትነትን ማዳበር ማለት አይደለም። እውነተኛ ወዳጅ ለመሆን በአንድ ዓላማ መሰለፍ፤ በየቀኑ መገናኘ ትም ሆነ ሁል ጊዜ የማንለያይ መሆን የለብንም። ያ ሰው የእኛን ድጋፍ ሲፈልግ ግን አብረን የምንቆም ሰዎች እንድንሆን የጌታ ሃሳብ ነው።

ወንድምን ከምርኮና ከድካም ከመመለስ የሚከለክል ጥሪ የለም። ወንድማችንን እንውቀሰው፤ እንገስጸው፤ አስፈላጊም ከሆነ በአላማ ምክንያት እሱ ከሚሄድበት ጎዳና ተለይተን እንሂድ፤ ለጠላት ግን አሳልፈን አንስጠው። አብሮን በማይሄድ ወንድም መቅናት፤ በውድቀቱ መደሰት፤ የሚወድቅበትንና የሚማረክበትን መንገድ ማመቻቸት፤ የድካሙን ወሬ በመስማት መደሰትና የመሳሰሉት የክፉው መንገዶች ከውርስ ያጎድሉናል።

6. በረከት ለሆነን ሰውና አምላክ በስጦታ ምላሽን መስጠት

«የሳሌም ንጉስ መልከ ጼዴቅም እንጀራንና የወይን ጠጅን አወጣ፤ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበር። ባረከውም፦ አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፤ ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም። አብራምም ከሁሉ አስራትን ሰጠው»

- ዘፍጥረት 14:17-20

አብርሃም ለተደረገለት ነገር ምላሽ ለመስጠት የሚፈጥን ሰው ነበር። ጠላቶቹን በእጁ ለጣለለት ለእግዚአብሔር ምላሽን የሚሰጥበትን አጋጣሚ ሲፈልግ የሰነበተ ይመስላል። አብርሃም እግዚአብሔር ከባረከው በረከት አውጥቶ በፈቃዱ ስጦታን ሲሰጥ ይታያል። ይህ ለሰዎችም ሆነ ለእግዚአብሔር ስጦታን በመስጠት ውስጥ ያለው ምስጢር ለአብርሃም የገባው የበረከት ምስጢር ነው።

ለባረከን ለእግዚአብሔር ስጦታን መስጠት የአብረሃምን በረከት ለመውረስ የተጠራ ሰው ባህርይ ነው። ለእግዚአብሔር የምንሰጠው፣ ጌታ ገንዘብ ስላጠረው ወይም ከእኛ ስጦታ ውጪ ምንም ማድረግ ስለማይችል ሳይሆን በመስጠታችን ውስጥ ያለው መንፈሳዊ አሰራር የበረከታችን ምንጭ ስለሆነ ነው።

እንደ አብርሃም ልጆች ለእግዚአብሔር ብቻ ሳይሆን ለበረከት ለሆኑን ሰዎች የምንሰጠው ምላሽ ሊኖረን ይገባል። ያደረገልኝ ጌታ ብቻ ነው በሚል እንከን የሌለበት አመለካከት ተሸፍነን አሁን ያለንበት ደረጃ የመድረሻ ምክንያት የሆኑንን ሰዎች ችላ ማለት ከአብርሃም ጎዳና ያስወጣናል። ለሰዎች ስጦታን የምንሰጠውና የምንባርካቸው ሰዎቹ ስላላቸውም ሆነ ስለሌላቸው ሳይሆን መንፈሳዊ ምስጢር ስለሆነ ነው። ስለዚህም፣ ከእኛ በታች ላሉ ሰዎች፣ በእኛ ደረጃ ላሉ ሰዎችና፣ እንዲሁም፣ ከእኛ በላይ ላሉ ሰዎች በረከትን የማፍሰስ ምስጢር ያለጥርጥር ታላቅ ነው።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የተነሳ አማኝ በገንዘብ ላይ ያለው አመለካከት የጥሪውን ሁኔታ እንደሚወስን ሊያስታውስ ይገባዋል። በሕይወታችን ያለው ማንኛውም የተስፋ ቃል የሚለቀቀው በመስጠት ነው። በእጃችን ውስጥ ያለው ሁሉ የጌታ ነውና በመስጠትና ባለመስጠት የሰዎችን ሁኔታና የጌታን ስራ ለመቆጣጠር ከመሞከር ወጥተን በልግስና ወደ መስጠት ስንተላለፍ የእኛም በረከት በልግስና ይለቀቅልናል።

7. የጌታን ክብር ለሰዎች ከሚሰጥ ሁኔታ መጠበቅ

«አብራምም የሰዶምን ንጉስ አለው፦ ሰማይንና ምድርን ወደሚገዛ ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጄን ከፍ አድርጌአለሁ፤ አንተ፦ አብራምን ባለጠጋ አደረግሁት እንዳትል፣ ብላቴኖቹ ከበሉት በቀር ከእኔ ጋር ከሄዱትም ድርሻ በቀር፣ ፈትልም ቢሆን የጫማ ማዘቢያም ቢሆን፣ ለአንተ ከሆነው ሁሉ እንዳልወስድ፤ አውናን ኤስኮልም መምሪም እነርሱ ድርሻቸውን ይውሰዱ»

- ዘፍጥረት 14:21-24

አብርሃም ከሰዶም ንጉስ ለቀረበለትን ምርኮን ለራስ የማስቀረት ግብግር መልሱ፣ «አብራምን ባለጠጋ አደረግሁት እንዳትል» አልፈልገውም የሚል ነበር። አብርሃም የሰዶም ንጉስ የነበረውን አመለካከት ጠንቅቆ ያወቀ ይመስላል። የሰዶም ንጉስ ስጦታን ለአብርሃም በመስጠቱ ምክንያት የአብርሃም የመባረኩ ምክንያት እሱ እንደሆነ በማወጅ ክብሩን ሊወስድ አስቦ ይሆን?

ለሰዎች የሚገባቸውን ክብር መስጠቱ ጌታን የሚያስደስተው እንጂ የሚያሳዝነው እርምጃ አይደለም። ሆኖም፣ የጌታን ክብር መጋራት ከጠማቸው ሰዎች ክብሩን አሳልፎ ከመስጠት ለመጠበቅ ልንወስድ የምንችላቸው ብዙ እርምጃዎች አሉ። ለምሳሌ፣ ከእኛ ጥቅም ስላገኙ ብቻ ብቅ ከሚሉ ሰዎች መጠንቀቅ አንደኛው መንገድ ነው። እንዲሁም፣ ከሰውና ከወዳጅነት ይልቅ ገንዘብና ንብረት ላይ ከሚያተኩሩ ሰዎች መጠበቅ አስፈላጊ ነው። ምን ሊሰጡን እንደሚችሉ ሳይሆን ምን ልንሰጣቸው እንደምንችል በማሰላት ከሚቀርቡን ሰዎች መጠበቅና ዛሬ ሰጥተውን ነገ ክብሩን ለመውሰድ ወሬን ከሚያበዙ ሰዎች ገለል ማለት የጌታን ለጌታ እንድንለይ መንገዱን ይጠርግልናል።

የእግዚአብሔር አሰራርና መንገድ ያልገባቸው (እንዲገባቸውም የማይፈልጉ)፣ ከመንፈሳዊ ሰዎች አካባቢ የማይጠፉና በስጦታቸው ብቻ መታወቅን የሚፈልጉ ሰዎች ለብዙዎች የእስራት ምንጮች ሆነዋል። መጸለይ አይፈልጉም፣ ለሚጸልይ ግን ገንዘብን ይሰጣሉ። መጾም አይፈልጉም ለሚጾሙት ግን ምግብን ያበላሉ። በስጦታቸው ማስተዋል የጎደላቸውን አገልጋዮች በማጥመድ ከአካባቢያቸው እንዳይጠፉ ያደርጋሉ። መንፈሳዊውን ሰው እየፈለጉ መንፈሳዊውን ሕይወት ግን ከማይፈልጉ ሰዎች እጅ ለምንም ጠብ የማይል ስጦታ ይንጠባጠባል። ከእንደዚህ አይነት ሰዎች እጅ ስጦታን ከመቀበል እግዚአብሔርን በመጠበቅ መቸገር እጅግ ማትረፊያ ነው።

ምዕራፍ አራት

የአብርሃም በረከት እንቅፋቶች
(ዘፍጥረት 15-16)

«ከዚያ በኋላ እንኳ በረከቱን ሊወርስ በወደደ ጊዜ እንደ ተጣለ ታውቃላችሁና፤ በእንባ ተግቶ ምንም ቢፈልገው ለንስሃ ስፍራ አላገኘምና» (ዕብ. 12:17)።

የአብርሃምን በረከት የመውረስ ጉዞ የሰልፍ ጉዞ ነው። በህይወቱ ያለውን የአብርሃምን በረከት የመውረስ ጥሪ በሚገባ አውቆ የሚራመድ ሰው ከጠላቱ ይህ ነው የማይባልን ጽኑ ውጊያ ሊጠብቅ ይገባዋል። ይህን ወደ ፍጻሜው በመገስገስ ላይ ያለን ሰው የሚታገሉት ችግሮች መነሻቸው ሁል ጊዜ ከሰይጣን ላይሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ለአብርሃም ጥሪ ምላሽን የመስጠቱ ጉዞ በራሱ ለፈተና የማጋለጥ ባህሪይ አለው። ምክንያቱም የምንኖርባት አለምና የተሸከምነው ስጋ የመወረስን እንጂ የመውረስን መልእክት ስለማያስተጋቡ ነው።

የእምነት አባታችን አብርሃም በሕይወቱ ላይ ያለውን የአምላኩን ፈቃድ በሚገባ ካወቀና እርምጃን ከወሰደ በኋላ የተነገረለት ፍጻሜ ላይ እንዳይደርስ በፊቱ የተደነቀሩ ብዙ መሰናክሎች ነበሩ። እነዚህ መሰናክሎች ዛሬም ቢሆን ጌታ ኢየሱስን በመውደድና ለፈቃዱ ራሳቸውን በመስጠት በሚራመዱ የአብርሃም ልጆች ፊት ይቆማሉ። አብርሃምን የመሰለ በቃሉ የተመሰከረለትን የእምነት አባት እነዚህ ሁኔታዎች ተገዳድረውት ካለፉ የዘመኑን የእግዚአብሔር ሰውማ ምንኛ አይጋፉት!

ይህ ዘመን የፍጻሜው ፍልሚያ የሚከሰትበት ዘመን ነው። ጠላት በክፋትና በጭካኔ ተነስቷል። ይህ ዘመን የመጨረሻ ዘመን ስለሆነም ጌታ

የሚናገራቸውና ለመልካም ፍጻሜ የሚያዘጋጃቸውም ሰዎች የበዙበት ዘመን ነው። ከእግዚአብሔር ጥሪና ድምጽ የተነሳ ልቦናው የነቃ ወገን በዝቷል። በአንጻሩም፣ እሱን በአጭሩ ለመቅጨት የተነሳውም ጠላት ጨክኗል። ነገር ግን ደስ ይበለን፣ የጌታ ጸጋም ካለገደብ ተለቅቋል!!!

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ ጥሪን የተቀበሉ ብዙዎች ናቸው፣ ዘልቀው ውርስ ውስጥ የሚገቡ ግን ጥቂቶች ናቸው። ለመሆኑ አንድ ሰው ለእግዚአብሔር ሃሳብ ራሱን ሲሰጥና ለተሰጠው የአብርሃምን በረከት የመውረስ ጥሪ ሲታዘዝ በመንገዱ ላይ የሚገጥሙት የተለመዱ እንቅፋቶች ምንድን ናቸው? በእንዴትስ ሁኔታ ሊያልፋቸው ይችላል? ከአብርሃም ሕይወት እንቅፋቶቹን እናያለን፣ ተግባራዊ መፍትሄዎችን እንማራለን።

1. ፍርሃት

«አብርሃን ሆይ፣ አትፍራ፤ እኔ ለአንተ ጋሻህ ነኝ»

- ዘፍጥረት 15:1

አብርሃም እግዚአብሔር ወደ መራው ስፍራ ጉዞ ከጀመረ ሰንበትበት ብሎአል። አሁን ሎጥ በአጠገቡ የለም። እንደውም ሎጥን ከምርኮ መልሶአል። ለመጀመሪያ ጊዜ የተዋጋው አብርሃም በድል ተመልሶአል። ስለዚህም በውጪ ሲታይ ከተጎናጸፈው ድል የተነሳ ድፍረትንና እምነትን የተሞላ ይመስላል። ውስጡን የሚያውቅ እግዚአብሔር ግን «አትፍራ» የሚል መልእክት ይዞ መጣ። እግዚአብሔር አትፍራ ካለ አብርሃም ፈርቷል ማለት ነው። መልእክቱ በአጭሩ ሲተረጎም፡- «አየፈራህ እኔ ያሰብኩልህን በረከት መውረስ አትችልምና አይዞህ» ማለት ነው።

እግዚአብሔር ያሳየውን በረከት ለመውረስ የተንቀሳቀሰን ሰው በመዋጋት የታወቀ ቀንደኛ መንፈስ የፍርሃት አሰራር ነው። ጥሪውንና ተልእኮውን በቁም ነገር የወሰደን ሰው ጠላት ዘወትር ያስፈራራዋል። የአብርሃም በረከት የሚወረሰው በእምነት ስለሆነ ለፍርሃት መንፈስ የተጋለጠ ጉዞ ነው፤ የእምነት ተቃራኒ ፍርሃት ነውና።

ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው የተልእኮን ሰው «በወንዝ ፍርሃት፣ በወንበዴዎች ፍርሃት፣ በወገኔ በኩል ፍርሃት፣ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፣ በከተማ ፍርሃት፣ በምድረ በዳ ፍርሃት፣ በባህር ፍርሃት፣ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት» (2ቆሮ. 11:26) ይዋጋዋል። የፍርሃት መንፈስ

ለውጊያ መነሳቱ አዲስና የሚያስገርም ጉዳይ አይደለም። ትወርሳለህ ብሎ የጠራን እግዚአብሔር ግን እስከመጨረሻው «አትፍራ» እያለ ደግሮ ያቆማል። ስለዚህ «ክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ራብ፣ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሃት፣ ወይስ ሰይፍ ነውን» ሮሜ 8:35)? በማለት ወደፊት መገስገስ ብቸኛው መንገድ ነው።

2. በራስ ላይ ያለ ዝቅተኛ አመለካከት

«አብራም ሆይ . . . ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው»

- ዘፍጥረት 15:1

አብርሃምን የተዋጋው አሰራር ፍርሃት ብቻ እንዳልሆነ መገመት አያስቸግርም። እግዚአብሔርን የሚያክል ታላቅ አምላክና የሰማይና የምድር ፈጣሪ አንድን በብዙዎች ታላላቅ ሰዎች መካከል የተገኘን አብርሃም የተሰኘ ታናሽ ሰው ለታላቅ ስራ ፈለግሀህ ብሎ ሊናገረው፣ አብርሃም የራሱን ትንሽነት አይቶ ሳይረበሽ አይቀርም። ለዚህም ነው እግዚአብሔር «ዋጋህም እጅግ ታላቅ ነው» በሚል ቃል የአብርሃምን ልቦና ሊያነቃቃው የፈለገው።

የዝቅተኝነት መንፈስና ትልቁ እኔ ነኝ የሚለው በበዛበት በዚህ አለም ውስጥ እየኖሩ ለታላቅ ነገር በእግዚአብሔር መፈለግ በአንድ ሰው ውስጥ የሚያመጣው ያለመብቃት ስሜት ቀላል አይሆንም። እውነት ነው የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የተጠራን ሰው የዝቅተኝነት ስሜት እጅግ ያጠቃዋል። ይህም የሚሆንበት ምክንያት ራእዩ ሰፊና ታላቅ፣ በእጁ ያለው ነገር ግን እጅግ ጥቂት ስለሆነ ነው።

ነገር ግን አሁን ያለንበትን ሁኔታ ሳይሆን እግዚአብሔር ነገ ሊያደርገንና ሊያደርግልን የሚችለውን ታላቅ ነገር በእምነት አይቶና አምኖ ጌታን መከተል አማራጭ የሌለው መንገድ ነው። ያለፈው ታሪካችን፣ ዘራችን፣ እድሜያችን፣ ጾታችን፣ የኢኮኖሚያችን ሁኔታና ያለንበት ሁኔታ እግዚአብሔር ከሚናገረን ነገር ጋር ባይመጣጠንም እንኳ ጌታ ስለእኛ የከበረ ነገርን አይቷልና በእምነት እንገስግስ። እየሆነ ያለው ነገር ላይ ሳይሆን ሊሆን ያለው ነገር ላይ እናተኩር። አብርሃም እግዚአብሔርን ከባዶ ተነስቶ አመነ፣ «ስለዚህ ደግሞ በብዛታቸው እንደ ሰማይ ከከብ እንደማይቆጠርም በባህር ዳር እንዳለ አሸዋ የነበሩት የሞተን ሰው እንኳ ከመሰለው ከአንዱ ተወለዱ» (ዕብ. 11:12)። በእኛ

ም ሕይወት እንዲህ ሊሆን ተጠርተናልና እንመን፣ ራሳችንንም ጌታ ባየን አይታ ማየትን እንጀምር።

3. በሌለን ነገር ላይ ማተኮር

«አብራምም፦ አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፣ ምንን ትሰጠኛለህ? እኔም ያለልጅ እሄዳለሁ፣ የቤቴም መጋቢ የደማስቆ ሰው ይህ ኤሊዔዘር ነው። አብራምም፦ ለእኔ ዘር አልሰጠኸኝም፣ እነሆም፣ በቤቴ የተወለደ ሰው ይወርሰኛል አለ»

- ዘፍጥረት 15:3

አብርሃም ጌታን ከሰማ በኋላ የመብዛትና የመትረፍረፍ፣ ለበረከትም የመሆን ራእይ በውስጡ ገባ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ነበር በፊት ያላሳሰበው ነገር ሊያሳስበው የጀመረው። ገና የሚወረሰው በረከት በሙላት ሳይመጣ የሚወርሰው ሰው ማን እንደሆነ መጨነቅ ጀመረ። ይህም የሚያሳየን የመብዛቱ ራእይ ውስጡ እንደገባ ነው። የአብርሃም ችግር እግዚአብሔር በሰጠውና ባለው ነገር ላይ ሳይሆን በሌለው ነገር ላይ የማተኮር ችግር ነበር። ውብ ትዳር፣ ታማኝ ባሪያዎች፣ ብዙ ከብቶችና የሚያስገርም የተስፋ ቃል ከማይለወጠውና ሁሉን ቻይ ከሆነው ጌታ ተቀብሎ ሳለ የእሱን ልብ ያዛለው ግን ልጅ የለኝም የሚለው ሃሳብ ነው፣ ለዚያውም በጉዳዩ ላይ የተስፋ ቃል እያለው።

ይህ አይነቱ አመለካከት የአብርሃምን በረከት ለመውረስ ትልቅን እይታ ከጌታው የተቀበለን ሰው የሚዋጋበት ምክንያት አለ። ይህ ታላቅንና የመብዛትን ራእይ ያየ ሰው ዘወትር በደረሰበት ሁኔታ የማይረካና የሚቀጥለውን የተሻለ ነገር ለማግኘት የሚራመድ ሰው ስለሆነ የፍሬ ቢስነት ስሜት ሊዋጋው ይችላል። ይህ ስሜት በቅጡ ከተያዘ ችግር የሌለበት ስሜት ሆኖ ሳለ፣ በዚህ ስሜት ምክንያት ግን ተስፋ መቁረጥ ለአደጋና ለተስፋ መቁረጥ አሳልፎ የሚሰጥ ሁኔታ ሊሆን ይችላል።

እንደ አብርሃም ልጆች፣ ለመምጣት ጊዜው የደረሰውን በረከት በእምነትና በጸሎት የማምጣት፣ ጊዜው ያልደረሰውን ደግሞ በጽንአት የመጠበቅ፣ ከዚያም አልፎ ደግሞ ለእኛ ያልተሰጠንንና ያልሆነውን ነገር ደግሞ በጸጋው የመተው ማንነት ያስፈልገናል። ሐዋርያው «በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለው» (ፊል. 3:12-14) እንዳለ፣ በእኛችን ስለገባው

ነገር በምስጋና በመቅረብና በማሻሻል በፊታችን ያለውን ለመያዝ እንዘርጋ እንጂ በአጻችን ያልገባውን እየቆጠርን አናጉረምርም።

4. በምልክት መመላለስ

«አቤቱ እግዚአብሔር ሆይ፣ እንድወርሳት በምን አውቃለሁ? አለ»

- ዘፍጥረት 15:8

አብርሃም እግዚአብሔር የተናገረውን አምኖአል፤ ነገር ግን ምልክትን የፈለገ ይመስላል። ይህም የሚያሳየን አብርሃም እግዚአብሔርን መጠራጠሩን ሳይሆን የተሰጠውን የተስፋ ቃል ለማግኘት መጓጓቱን ነው። ምናልባትም ይህንን ልቡን ስላየ ይሆናል እግዚአብሔር ለምልክት ጥያቄው ምላሽን የሰጠው። ሆኖም፣ ምንም እንኳ በቅን ልቦና ቢያደርገውና ጌታም ምላሽን ቢሰጠው፣ ምልክትን ፍለጋ መሄዱ ለጠላት ወጥመድ ሊያጋልጠው ይችል ነበር።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የበራለት ሰው ከጌታ የሰማው በረከት ውስጥ ለመግባት እጅግ የሚጓጓ ሰው ስለሆነ ምልክት ለማየት እስኪፈልግ ድረስ ይፈተናል። ይህም ሁኔታ እግዚአብሔርን ከሚጠራጠር ማንነት እስካልመነጨ ድረስ ጌታን አያስዝነውም። ነገር ግን ጠላት ምልክትን በመጠየቅ የሚመላለስን ሰው በቀላሉ ከመስመር እንደሚያስወጣው እሙን ነው። ጠላታችን ሰይጣን የዚህ አለም አምላክ በመሆኑና ይህችን የምንኖርባትን አለም በቀላሉ ማንቀሳቀስና ለዓላማው ማሳተፍ ስለሚችል ሃሰተኛ ምልክትን የማሳየት አጀንዳው ሊሳካለት ይችላል።

ጌታ ምልክትን መስጠት መብቱና በፈለገውም ጊዜ ከመስጠት እንደማይከለከል በማመን ምልክትን ከሰጠን እንቀበለው፤ ምልክትን ካላየሁ አልንቀሳቀስም ማለት ግን ለመወረስ እንጂ ለመውረስ አያበቃንም። ምልክትን ስናይ ብቻ የማመን ዝንባሌ ካለን ለጠላት መጫወቻ እንሆናለን። መርሃችን ይህ ይሁን፦ «መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ የግሪክ ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፣ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን» (1ቆሮ. 1:22-23)።

5. በእኛ ላይ ስልጣን ላልተሰጣቸው ሰዎች ካለአግባብ መታዘዝ

«ሦራም አብራምን፦ እነሆ፣ እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ፤ ምናልባት ከእርሷ በልጅ እታነጽ እንደሆነ ወደ እርስዋ ግባ አለችው። አብራምም የሦራን ቃል ሰማ»

- ዘፍጥረት 16:2-3

ለአብርሃም ወደ አጋር የመግባትን ሃሳብ ያመጣችውም ሆነ ትእዛዙንም ያስተላለፈችው ሳራ ነች። ወደዚያ ከኪዳን ውጪ ወደሆነ ተግባር ላለመግባት አብርሃም ለሳራ ቃል እምቢ ማለት ሲገባው፣ መስማትንና መታዘዝን መረጠ። ቃል ኪዳንን በቀጥታ ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ ሰው የሰማውን ኪዳን አስኪቀበል ድረስ የመጠባበቅን ውሳኔ ማስተላለፍ ሲገባው የሳራን ቃል ሰምቶ አቋራጭ መንገድን መከተልን ወደደ።

ዘመኑ ሰዎች የተሰጣቸውን ስፍራ፣ ሃላፊነትና የስልጣን ገደብ የማይጠብቁበትና በሁሉ ሰው ሕይወት ጣልቃ እየገቡ የሚፈርዱበት ዘመን ነው። አዛዥ፣ ባለስልጣኑ፣ የበላይ ሆኖ ለመታየት የሚታገለው ሰውና ሃሳብ ሰጪው በበዛበት በዚህ ዓለም ውስጥ መስማት ያለብን ሰው ማን እንደሆነ ካላወቅን ውርስን የሚያስቀማው ህዝብ ብዙ ነው።

የተጠራ ሰው ጌታን ላለማሳዘን ካለው ዝንባሌ የተነሳ ሁሉንም የመስማት ችግር ውስጥ ሊወድቅ ይችላል። የመጠበቅ ዘመን ሲረዝም፣ ጌታ የተናገረን ነገር ከዕለቱ ኑሮአችን ጋር አልጣጣም ሲልና፣ ውጥረት ሲበዛ አቋራጭ መንገድን አመልካቹ ብዙ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ሃሳብ ሰጪዎች ሰዎች የቅርብ ወዳጆቻችን ሊሆኑ ይችላሉ። ስለዚህም እነሱ ከሚያዝኑብን ብንሰማቸው ይቀልለንና መዘዝ ውስጥ እንገኛለን።

በጌታ ስም የሚነገርንና ለጥሪያችን ተስማሚ የመሰለንን ሃሳብ ሁሉ ሳይመረምሩ ሰምቶ መተግበር ከውርስ ያስወጣናል። ሰዎችን ስለምናዝንላቸው፣ ስለምንወዳቸውና አገልጋይ ናቸው ብለን ስላሰብን ብቻ ለሁሉ ነገር እሺ ማለት የለብንም። ቃሉ «ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለስልጣኖች ይገዛ» (ሮሜ 13:1) እንደሚል መታዘዝና መስማት ያለብንን የበላይ ሰዎች ማወቅ ተገቢ ነው።

6. የጌታን ተስፋ ለመሙላት በስጋ መሞከር

«አርሱም ወደ አጋር ገባ፣ አረገዘችም»

- ዘፍጥረት 16:4

አብርሃም ወደ አጋር የገባበት ዋነኛ ምክንያት የልቡን ልጅ የማግኘት ምኞት ወደመሆን የሚያመጣ ሃሳብን ስላገኘና «መገለጡ» ስለተስማማው ነው። ወደ አጋር ገብቶ ጌታ የሰጠውን የተስፋ ቃል በዘጠኝ ወር ውስጥ በጉያው ሲያቅፍ ታየው። በመለኮታዊ መገለጥ የመጣለትን የተስፋ ቃል በስጋው ወደ መሆን ለማምጣት ሞከረ። ልጅ ስላገኘ ብቻ ወራሽ የሚያገኝ መሰለው።

ይህ እርምጃ ብዙዎችን ለበረከት የተጠሩ ሰዎችን የሚፈታተን ስህተት ነው። የአብርሃምን በረከት ለመውረስ እይታው የበራለት ሰው ሕይወቱን ሁሉ ለጌታ የሰጠና ለተጠራለትም ነገር የሚቀና ሰው ስለሆነ፣ ተስፋው እንዲሞላ የስጋ እርምጃ ውስጥ በቀላሉ ሊገባ ይችላል። ጠላትም ወደ እኛ ለማሳሳት ሲመጣ የሚጠጋን ልባችን በሚቀናለትና በሚንጓለት ጉዳይ ተከልሎ እንጂ ግድ በማይሰጠን ሁኔታ አይደለም። እግዚአብሔር ግን «ከእስማኤል» እንድንጠበቅ ያሳስበናል።

ተስፋውን ለማግኘት ጌታን ከመስማት፣ ከማመን፣ ከመታዘዝና ራስንም በቅድስና ከመጠበቅ ውጪ ልናደርገው የምንችለው አንድም ነገር እንደሌለን በሚገባ ልንረዳ ይገባል። እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር በራሱ ጊዜ፣ ስፍራና ሁኔታ ወደ መሆን ያመጣዋል። የእኛ ሃላፊነት ራስን ማቅረብ እንጂ ምርጫ ማቅረብ አይደለም።

ጌታን ለማስከበርና የተናገረውን እውን ለማድረግ ከምንከፍለው ማንኛውም አይነት መስዋእትነት ይልቅ ቀላል የሆነ መታዘዛችንን ይፈልገዋል። «በውኑ የእግዚአብሔርን ቃል በመስማት ደስ እንደሚለው እግዚአብሔር በሚቃጠልና በሚታረድ መስዋእት ደስ ይለዋልን? እነሆ፣ መታዘዝ፣ ከመስዋእት፣ ማዳመጥም አውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል» (1ሳሙ. 15:22)።

7. የጥሪንና የቤተሰብን ጉዳይ በሚዛናዊነት አለመያዝ

«አብራምም ሦራን፦ እነሆ ባሪያሽ በእጅሽ ናት፤ እንደወደድሽ አድርጊባት አላት»

- ዘፍጥረት 16:6

«ይህም ነገር በአብርሃም ዘንድ ስለ ልጁ እጅግ ችግር ሆነበት»

- ዘፍጥረት 21:11

አብርሃም የብዙ ዓመታት ልምድ እያለው እንኳ በቤተሰብ ውስጥ ያለውን ሁኔታ እግዚአብሔር ከተናገረው ነገር ጋር አስታርቆና ሚዛናዊ አድርጎ በሚገባ መያዝ አስቸግሮት ነበር። የሳራን ቃል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በሚዛናዊ ሁኔታ መያዝ የቸገረውን ያህል፣ አሁን ደግሞ የአጋርን ነገር ከሳራ ነገር ጋር፣ የይስሃቅን ነገር ከእስማኤል ነገር ጋር በምን መልኩ አስታርቆ እንደሚይዝ ግር አለው። ለዚህም ነው ጉዳዩን ለሚስቱ ለሳራ አሳልፎ በመስጠት እንደወደድሽ አድርጊ ያላት።

የበረከት ጥሪ የደረሰው ሰው ካላስተዋለ ጥሪውን ከቤተሰቡና ከሕብረተሰቡ ለይቶ በማየት ሕብረተሰባዊ አመለካከቱ እንጭጭ እንደሆነ ሊቀርበት ይችላል። ስለዚህ፣ የጥሪው ሁኔታ ቤተሰቡንና ሕብረተሰቡን እንደሚነካ በማወቅ በሚዛናዊነት መያዝ ይገባዋል። በአንጻሩም የቤተሰቡ ሁኔታም የጥሪውን ጎዳና ሊያስተጓጉልም እንደሚችል በመገንዘብ አስተውሎ ሊያደረግ ይገባል። እንደ አማኞች መላው ማንነታችንን ያዳበርንና ጥሪያችን ከቤተሰብ ህይወታችን ጋር የተያያዘ እንደሆነ ያወቅን ሰዎች እንድንሆን ያሻል።

እግዚአብሔር ያዘዘኝን እየፈጸምኩ ነው በሚል ሰበብ ቤተሰብን ችላ ማለት በዚህ መልኩ ያለመብሰል አንዱ ምልክት ነው። አንዳንድ ጊዜ ለጌታ ስራ የምናስበው ሃሳብ ከመብዛቱ የተነሳ ለቤተሰብ ማሰብን ስናቆምና ጌታ ይጠነቀቃል ብለን ችላ ስንለው ከፍጻሜአችን የሚያወጣ ስህተት ውስጥ እንደምንገባ አስቀድመን ልናውቅና ልንጠነቀቅ ያሻል። ቃሉም እንደሚለን፦ «ነገር ግን ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁኑ ስለቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፣ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው» (1ጢሞ. 5:8)።

ምዕራፍ አምስት

የአብርሃም የጥሪ መንገድ
(ዘፍጥረት 17)

. «ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፣ እንዲሁ መንገዴ ከመንገዳችሁ አሳቤ ከአሳባችሁ ከፍ ያለ ነው» (ኢሳ. 55:9)::

የአብርሃም አምላክ እግዚአብሔር የራሱ የሆነን አሰራርና መንገድ በመከተል የታወቀ አምላክ ነው:: እግዚአብሔር ዓለም ሳይፈጠር ለእኛ ያሰበውን ጥሪና በረከት ወደ እኛ ሲያመጣው አቀራረቡ ከሰው ለየት ያለ ነው:: ሰው ቢጠራን እንደሚቀርበን አይቀርበንም:: ሰው ቃል ከገባ በኋላ ድካም ቢያይብን እንደሚሆነው እግዚአብሔር አይሆንብንም::

በብዙ ድካም በተያዙ ቤተሰቦች መካከል መወለዳችንና ማደጋችን ይህ ነው የማይባል ተጽእኖ አሳድሮብናል:: ሲሳካልን አመስግነውን፣ ሳይሳካልን ደግሞ ፍርሃትን የሚለቅና አእምሮአችንን የሚመታ ሃሳብ ሰንዝረውብን በብዙ ተጎድተን ያለፍን ሰዎች ነን:: ወደ እግዚአብሔር መንግስት ስንመጣና ያንን አባታዊ የፍቅር ግብገር ሲሰጠንም፣ በለመድነው በሰው መንገድ ወደ እኛ የሚመጣ ይመስለንና ስጋት በውስጣችን ያድራል፤ ተፈትኖ መመላለስም ያዳግተናል:: አላወቅነውም እንጂ የብዙዎቻችን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ሆነን በነጻነት ያለመመላለሳችን መንስኤ ያለው እዚያ ጋር ነው::

በስጋዊና በተፈጥሮአዊ አሰራር ተወስኖ በሚርመሰመስ ህብረተሰብ መካከል መመላለሳችንም አስከፊ አመለካከት ቀርጾብናል:: የገባውን ቃል ኪዳን ላለመጠበቅ ምክንያት የማያጣ ትውልድ ውስጥ በመኖር ነፍሳችን ተጨንቃለች:: መጀመሪያ ሲያውቀን የወደደንንና የተቀበለንን ያህል፣ በቆየን መጠን ስለማናገኝበት ውስጣችን ይደማል:: ይህም ሁኔታ ለእግዚአብሔር ጥሪ የምንሰጠው ምላሽ ላይ ሳይቀር አሉታዊ ተጽእኖ ያመጣል::

እንግዲህ እነዚህንና የመሳሰሉትን ድካሞች በተሸከመ ሕብረተሰብ ውስጥ ኖረንና የክህደትን ጽዋ ጠጥተን ነው ወደ እግዚአብሔር መንግስት የመጣነው:: ጌታ ማንነታችንን በመለወጥ እውነተኛ ቃል ኪዳን ማለት ምን ማለት እንደሆነ እስከሚመሰክርልን ድረስ ከብዙ አሮጌ አመለካከቶች ጋር እንታገላለን:: ስለዚህ የእግዚአብሔር መንገድ ከለመድነውና ከደከምንበት ከሰው መንገድ ለየት እንደሚል እንድንገነዘብና ካለንበት አበሳ እንድንፈታ የጥሪውን መንገድ እንወቅ:: እግዚአብሔር እንዴት ነው ጥሪውን ለማከናወን የሚሰራው? መንገዱስ ምንድን ነው? እንዴት ነው እግዚአብሔር ወደ እኛ የሚመጣው?

1. ስማችንን በመለወጥ ይመጣል

«እንግዲህ ስምህ አብራም ተብሎ አይጠራ፣ ነገር ግን ስምህ አብርሃም ይሆናል»

- ዘፍጥረት 17:5

የአብርሃም ስም አብራም በነበረበት ጊዜ እግዚአብሔር ወደ እርሱ የመብዛትን ራእይ ሲሰጠው መጀመሪያ ስሙን ነበር የቀየረው:: ሰዎች እሱን የሚጠሩበትን ስም ቀየረው:: አብርሃምም ራሱም የሚጠራበት ስም ተቀየረ፣ እይታውም አብሮ! አብርሃም ተራ ነገርን እያየና እየተናገረ የከበረ ነገርን መውረስ ስለማይችል፤ ጥቂትን ነገር እያወጀና እያየ መብዛትን መውረስ ስለማይችል፤ ስሙ መለወጥ ነበረበት::

ስማችን እኛነታችንን የሚያንጸባርቅ መጠሪያችን ነው:: ስማችን ሁል ጊዜ ማንነታችንን ወይም እኛ እንዲህ ነን ብለን ያመንንበትን አመለካከት ያንጸባርቃል:: ይህም ስም ሲጠራ እኛ እንደዚያ እንደሆንን አምነንበት አቤት በማለት ምላሽን እንሰጣለን:: ስለዚህም ራሳችንን የምንጠራበትን ስም ጌታ ሊቀይር ይፈልጋል:: ከዚያም ባሻገር ስማችን ሰዎች እንደዚህ ነው ብለው ስለ እኛ የሚያስቡትን ነገር ያስታውሰናል:: ሰዎች ስለ እኛ ባለቡ ቁጥር በዚያ ስም ነው የሚያስታውሱን:: ስለዚህም ሰዎች የሰጡንን ስም ጌታ ሊቀይር ይፈልጋል::

እኛም ሆንን ሰዎች ስምን የምናወጣው እንደ እይታችን ነው:: ስማችን መለወጡ አመለካከታችንን ይለውጠዋል:: አመለካከታችን ሲለወጥ ደግሞ

ማንነታችን ይለወጣል። ስማችን ያለፈውን ታሪካችንን ያመለክታል። ሰዎች፣ «እሱ እኮ እንዲህ አይነት ሰው ነው» ብለው ያስቀመጡብን ስም አለ። ይህም ስም የተሰጠን ከታሪካችን፣ ከሰራነው ስህተትና እንደዚህ አይነት ሰው ነው ተብለን ከተሰጠን ግምት ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ግን ያንን ስም ለውጦ እንድንሆን ወደ ተሰጠን ስም ሊያሸጋግረን ይፈልጋል።

2. በቃል ኪዳን ይመጣል

«ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም አቆማለሁ»

- ዘፍጥረት 17:7

አብርሃምን ወደ ዓላማው እግዚአብሔር ሲጠራው በማይለወጠው ማንነቱ ላይ የተመሰረተ ኪዳን ገብቶ ነው የጠራው። አብርሃም ያለውን ነገር ሁሉ ጥሎ እግዚአብሔርን በመታዘዝ ሲወጣ ዛሬ ተጀምሮ ነገ የሚቆም ነገር ውስጥ አልነበረም የገባው። ለእርሱና ለዘሩ ሳይቀር የሚተርፍን ቃል ኪዳን ከጌታ ተቀብሎ ጌታን አምኖ ነው የወጣው።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የአብርሃምን ዋጋ የመክፈል መንገድ ስንከተል አንድ ልናስታውሰና ልባችንን ልናሳርፍበት የሚገባን እውነት አለ። እግዚአብሔር ወደእኛ ሲመጣ በቃል ኪዳን ነው የሚመጣው። ጌታ በፍጹም ቃል ኪዳን ሳይገባ አያሰማራንም። እግዚአብሔር እንዲሁ በድንገትና እግረመንገዱን ወደ ሕይወታችን ገብቶ እንዲሁ በሆነው ባልሆነው ምክንያት ከሕይወታችን አይወጣም። እግዚአብሔር የገባውን ኪዳን በፍጹም በቀላሉ አይሽርም። ቃሉ ከሚያልፍ ሰማይና ምድር ቢያልፉ ይቀልላል።

ይህ እግዚአብሔር የሚገባልን በቀላሉ የማይሻር ቃል ኪዳን ከዘር ወደ ዘር የመውረድና ትውልድን የሚያቅፍ ጉልበት አለው። በእኛ እግዚአብሔርን መታዘዝ ምክንያት ቤተሰባችንና ዘራችን ሁሉ የበረከት ዝናብ እንዲዘንብላቸው የማድረግ ጥሪ ደርሶናል። ስለዚህም እግዚአብሔር የሚናገረንን የውሳኔ ጥሪ ከግል ሕይወታችን አንጻር ብቻ አይተን ምላሽ መስጠቱ ጠባብነትንና ምስጢሩ እንዳልበራልን ያመላክታል። የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን ምስጢር ሲበራልንና በሚገባ ስንገነዘበው ከእንግድነት ስሜት የሚያወጣና የሚያደላድል ኪዳን እንደሆነ እንረዳለን። እኛ፣ ቤተሰባችንና ዘራችን የሚያርፍበትና ከመቅበዝበዝ

ስሜትና እርግማን የሚወጣበት ቃል ኪዳን የአብርሃምን ጥሪ በመከተል ውስጥ ይገኛል።

3. ከእኛም ቃል ኪዳንን በመጠበቅ ይመጣል

«አንተ ደግሞ ቃል ኪዳኔን ትጠብቃለህ»

- ዘፍጥረት 17:9

አብርሃም ቃል ኪዳንን ከእግዚአብሔር ከተቀበለ በኋላ ሃላፊነቱን በእግዚአብሔር ላይ ጥሎ እንዳሻው ለመመላለስ አልተጠራም። ከእግዚአብሔር የማይለወጥን ኪዳን የተቀበለው አብርሃም ከእርሱም የሚጠበቅበትን የኪዳን ጥሪ ከእግዚአብሔር አንደበት ሰምቶ ነበር የሄደው። እሱ የሚጠበቅበትን ሳያውቅ ወይም ደግሞ እያወቀ በግድየለሽነት በመመላለስ እግዚአብሔር ሃላፊነቱን የመወጣቱን ሁኔታ ላይ ብቻ እንዲያተኩር አልተፈቀደለትም። እሱም በመገረዝ ውስጥ ያለን ኪዳን የመጠበቅን ሃላፊነት ተቀብሎ ነበር።

የአብርሃምን ጥሪና በረከት ለመውረስ አብርሃም በሄደበት ጎዳና ከመሄድ ውጪ ሌላ አማራጭ መንገድ የለንም። የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የእኛን ታማኝነት ይጠይቃል። እግዚአብሔር ቃል ኪዳንን ከገባ በኋላ እኛም የምንጠብቀውን ቃል ኪዳን ይሰጠናል። በሌላ አባባል፣ እንዳሻችንና እንደፈለግነው እየኖርን በመከራ ጊዜ ብቻ፣ «ምነው ጌታ ተወኝ» ማለት የእግአብሔርን የቃል ኪዳን አሰራር ያለመገንዘብ ምልክት ነው።

ለጌታ የምንገባው ቃል ኪዳን መገረዝን ይጠይቃል። ይህ የመገረዝ ኪዳን የጌታን መንገድ ለመከተል ሲሉ የመጎዳትንና ዋጋ የመክፈልን ሁኔታ ያመላክታል። ይህ የመገረዝ ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር መቀበል ማለት ትርፍ የሆነውንና የማይጠቅመውን ነገር ሁሉ የማስወገድን ቃል ኪዳን ያመላክታል። ይህ ለጌታ የምንገባው ቃል ኪዳን ዘላቂና ለቤተሰብ የሚተላለፍ እንጂ ጊዜያዊና ወጣ ገባ የምንልበት አይነት ኪዳን መሆን የለበትም። እግዚአብሔር ከሚሰጠን ቃል ኪዳኖች አብዛኛዎቹ ሁኔታዊ ቃል ኪዳኖች ናቸው። ማለትም እነዚህ ጌታ የሚገባቸው ኪዳኖች የእኛን መታዘዝና የራሳችንን ድርሻና ኪዳን በመጠበቃችን ላይ የተመሰረቱ ናቸው።

4. የትዳር ጓደኛችንንም በራእዩ በመጠቅለል ይመጣል

«ያሚስትህ የሶራን ስም ሶራ ብለህ አትጥራ፣ ስምዋ ሳራ ይሆናል እንጂ። እባርካታለሁ፣ ደግሞም ከእርሷ ልጅ እሰጥሃለሁ፣ እባርካትማለሁ፣ የአህዛብም እናት ትሆናለች፣ የአህዛብ ነገስታት ከእርሷ ይወጣሉ»

- ዘፍጥረት 17:15-16

አብርሃም ያደገበትና የኖረበት ሕብረተሰብ በሴቶች ላይ ያለው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ተጽእኖ በግልጽ ባይጻፍም፣ እግዚአብሔር ግን ወደ አብርሃም በጥሪ ሲመጣ በሳራ ላይ ያለውንም ዓላማ መግለጥ አስፈላጊ ሆኖ አገኘው። የእግዚአብሔር ጥሪና በረከት ለአብርሃም ብቻ የተሰጠ ጥሪና በረከት አይደለም። ሚስቱን ሳራን የሚያጠቃልል በረከት ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ኪዳን ከሚስቱ ከሳራ ውጪ በፍጹም ወደ መሆን ሊመጣ የማይችል ጉዳይ ነው። ስለዚህ የአብርሃም ስም እንደተቀየረ የሶራም ስም ወደ ሳራ መቀየር ነበረበት። አብርሃም ትባረካለህ፣ ትበዛለህ፣ የአሕዛብም አባት ትሆናለህ እንደተባለ ለእሷም እንዲሁ ተባለላት።

ለባል የመጣ በረከት ለሚስትም መጥቶአል። ለሚስትም የመጣ በረከት ለባልም ጭምር መጥቶአል። እግዚአብሔር ትዳርን ያከብራል። እግዚአብሔር አብሮ ሊባርከን ካላሰበ በስተቀር በትዳር አያጣምረንምና። ይህ እውነት ግን በዘመናችን ሲንጸባረቅ አይታይም። እግዚአብሔር ጠራኝ ያለ ሰው የትዳር ጓደኛውን ችላ ብሎ ወደፊት ሲገሰግስና ባለው ትርፍ ጊዜ ብቻ ለትዳሩ ጊዜ ሲሰጥ ሲታይ ልብን ለጥያቄ ይዳርጋል። አብሮ መኖር፣ አብሮ ለእግዚአብሔር ጥሪ ምላሽ መስጠትና አብሮ መባረክ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው።

እግዚአብሔር የእኛን ስም ሲቀይር የትዳር ጓደኛችንንም፣ ከዚም አልፎ የትዳራችንን ስም ይቀይራል። በማንኛውም የጌታ ጉብኝትም ሆነ የእድገት እርምጃ ከትዳር ጓደኛችን ጋር ሰፊ ክፍተት እንዲኖረን የጌታ ፈቃድ አይደለም። ስማችንን፣ አመለካከታችንንና ማንነታችንን በቤተሰብ ደረጃ አብሮ ካልቀየረ አብረን መራመድ አንችልም። አለዚያ አገልግሎት፣ የግል ዓላማና ከቤተሰብ ውጪ የምናደርጋቸው ተግባሮች እያማረባቸውና ለጊዜው እየተሳኩ፣ የቤተሰብ ሁኔታ ግን እያዘቀጠ ይሄዳል። ሁኔታውም በጊዜው ምላሽ ካልተሰጠው በግላችን የከመርነው «በረከት» ቤተሰባችን ሲፈርስ አብሮ ይፈርሳል።

5. በጠባብነታችን ሳይወሰን ይመጣል

«አብርሃምም በማንባሩ ወደቀ፣ ሳቀም፣ በልቡም አለ፦ የመቶ አመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመት የሆናትም ሳራ ትወልዳለችን?»

- ዘፍጥረት 17:16-19

አብርሃም ከእግዚአብሔር የሰማው ቃል ካለበት እድሜ፣ ቦጊዜው ካለው አመለካከቱና፣ በዙሪያው ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ስላልተጣጣመለት ግራ የገባው ይመስላል። ለእግዚአብሔር በመስገድ አክብሮቱን ቢገልጥም እንኳ ስሜቱ ግን እንዲስቅ ግድ አለው። ሳቅና ጸሎት እስኪደባለቅበት ድረስ የተደናገጠና ጠበብ ያለ አመለካከት ቢኖረውም እንኳ፣ ጌታን ከመስራት አልመለሰውም። አብርሃም በዚህ መልኩ ምላሽ እንደሚሰጠው እግዚአብሔር ቀድሞውንም ያውቀዋል። የመጣለትን መልእክት ባለችው ሰዋዊ አእምሮ ለማስተናገድ አስቸጋሪ ስለሆነ።

እግዚአብሔር የአብርሃምን በረከት እንድንወርስ ሲጠራን በዚህ በተሸከምነው ጊዜአዊ «ድንኳን» ምክንያት ስንጎተት ችግራችንን ይገነዘባል። እግዚአብሔር የሚገልጥለትን እውነታና የሚሰጠውን የበረከት ጥሪ በቀላሉና ምንም ሳይከብደው የሚቀበል ሰው ይገኛል ተብሎ አይታሰብም። ይህም የሚሆንበት ምክንያት እግዚአብሔር ከእኛነታችን ጋር የሚመጥን ሳይሆን እሱ ሊያደርግ ከሚፈልገውና ከሚያስበው ነገር ጋር የሚመጥን ጥሪ ስለሚሰጠን ነው። ጥሪው ትልቅ፣ ማንነታችን ግን ትንሽ፣ የውርሱ ባለጠግነት የከበረ የእኛ ልምምድ ግን የተዋረደ ሆኖ ስናየው አእምሮአችን መሸከም ያስቸግረውና «እንስቃለን»።

እግዚአብሔር ቃል እንዲገባልን ፍጽምናችንን ቢጠብቅ ኖሮ ተስፋ አይኖረንም ነበር። ንስር ጫጩቶችዋን ተሸክማ እንደምትወስድ እግዚአብሔር እንዲሸከመንና ወደ ተናገረልን ፍጻሜአችን እንዲወስደን የሚያደርገው ችግራችንን አሸንፈንና ካለምንም ድካም አምነነው ማለፋችን ሳይሆን የልባችንን ንጽህና በማየት ነው። እግዚአብሔርን ከልባችን ስንወደውና የሚናገረው ነገር ቢከብደንም እንኳ በየዋህነት ስንከተለው አለማመናችንንና ድካማችንን ያግዛል።

6. በሁለተኛ እድል ይመጣል

«ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፤ እነሆ ባርኬዋለሁ፤ ፍሬአምም አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዛዋለሁ፤ አሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፤ ታላቅ ሀዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ»

- ዘፍጥረት 17:20

አብርሃም የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃል እውን ለማድረግ በስጋው ለመራመድ የሳራን ድምጽ ከሰማ በኋላ እስማኤል በመወለዱ በቀላሉ የማይረሳ ጸጸትን ወደ ሕይወቱ አምጥቶአል። አሁን እስማኤል መጥቶአል፣ ምን ያድርገው? ምንም እንኳ የእስማኤል መወለድ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ቢሆንምና የእግዚአብሔር ፈቃድ በእሱ እንደማይፈጸም ቢወሰንም፣ ወደ መኖር የመጣው የእስማኤልም ፍጻሜ ግን መታወቅ አለበት። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር በአብርሃም ስህተትና በኃጢአት ውጤት የመጣውን እስማኤልን እንደሚባርክና ለአብርሃምም ሁለተኛ እድል እንደሚሰጠው ተናገረ።

አንዳንድ ጊዜ በስጋችን የምንንዛቸው ጎዳናዎችና በእግዚአብሔር አሰራር ላይ ያለን ጣልቃ ገብነት የራሳቸውን መዘዞች ይዘው ይመጣሉ። አንዳንዶቹ ስህተቶቻችን ከንስሃ በኋላ በመዘዝ የማይከተሉን አይነት ስህተቶች ሲሆኑ፣ አንዳንዶቹ ግን ከእኛ ጋር እስከ መጨረሻው የሚዘልቁ የስህተት ፍሬዎችን ያስከትላሉ። ለዚህ ነው በስህተታችን ስላመጣነው «እስማኤል» መጸለይ ያለብን። እግዚአብሔር የሁለተኛ እድል አምላክ ነውና፣ በስህተታችን ተጸጽተን በፊቱ ስንቀርብ በምህረት ወደ እኛ ፊቱን ይመልሳል፣ ራሳችንንም በማዋረድ የምንጸልየውን ጸሎት ጌታ ይሰማል።

እግዚአብሔር ክፉውን ወደ መልካም የመለወጫ መንገድ አለው፤ ለእርግማን አላልፎ ከሰጠን ሁኔታ ውስጥ በረከትን የማውጣት ችሎታውም ፈቃደኝነቱም አለው። ልባችንን ቅን ካደረግንና በፊቱ በቅንነት ለመመላለስ ጎዳናችንን ከቀየርን እኛን ከመባረክ ሊከለክለው የሚችልና ይቅር የማይባል ኃጢአትና ድካም የለም። የጠላት ሃሳብ አንድ ጊዜ በሰራነው የስህተት መዘዝ ምክንያት ተተብትበን እድሜአችንን በጸጸት እንድንኖር ነው። የእግዚአብሔር ሃሳብ ግን ከስህተታችን ተመልሰን እንድንባረክ፣ ያንንም ስህተት ደግመን እንዳንሰራና ክፉው ወደ መልካም እንዲለወጥ ነው።

7. ፈቃዱን አድርገን ሌሎችን እንድናስደርግ በመጠበቅ ይመጣል

«አብርሃምን ልጅን እስማኤልን፣ በቤቱም የተወለዱትን ሁሉ፣ በብሩም የገዛቸውን ሁሉ፣ ከአብርሃም ቤተሰብ ወንዶቹን ሁሉ ወሰደ፣ የቁልፈታቸውንም ሰጋ እግዚአብሔር እንዳለው በዚያው ቀን ገረዘ»

- ዘፍጥረት 17:22-23

አብርሃም ምንም እንኳ በእድሜ እጅግ የገፋ ቢሆንም እግዚአብሔርን በመታዘዝ የግርዛትን ኪዳን ፈጸመ። የጌታን ትእዛዝ ግን ራሱ ብቻ በመፈጸም አልተወሰነም። ልጁንና በቤቱ የነበሩቱን ሁሉ ወደዚህ የቃል ኪዳን ሕይወት ለማምጣት ተጽእኖን አሳድሮባቸው ነበር። አብርሃም በግሉ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መፈጸሙ ብቻውን በቂ እንዳልሆነ የተገነዘበ ሰው ነበር። የጌታ ኪዳን እርሱንም ሆነ ቤተሰቡን፣ ከዚም አልፎ በእሱ ጥላ ስር ያሉትን ሁሉ እንደሚጠቀልል ገብቶት ነበር። በቤቱ ከኪዳን ውጪ የሚኖር ሰው መኖሩ ሊያስከትልበት የሚችለውን መዘዝ አውቆ ኪዳንን በቤተሰብ ደረጃ ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ እሱ እንዳደረገው ኪዳኑን በሚገባ መፈጸም አለብን። ከትልቅነታችን፣ ከልምምዳችንና ከማወቃችን የተነሳ ከመታዘዝ ልናመልጠው የምንችለው የእግዚአብሔር ትእዛዝ የለም። እኛ ታዝዘን ሌሎችም እንዲታዘዙ ተጽእኖን ልናሳድር ተጠርተናል። እግዚአብሔር ተናግሮ ሲጨርስ የእኛ ስራ መጀመር አለበት። የእኛ ስራ ደግሞ ቤተሰባችንንና ለተጽእኖ በአካባቢያችን እግዚአብሔር ያስቀመጣቸውን ሰዎች ሁሉ የሚመለከት ጉዳይ ነው።

እግዚአብሔር ለመጨረሻ ጊዜ ወደ እኛ መጥቶ የተናገረንን ነገር እስክንፈጽመውና እስከምንታዘዘው ድረስ ሌላ አዲስ ትእዛዝና መገለጥ ይዞ ወደ እኛ ሊመጣ አይችልም። ይህም የመታዘዝ ሁኔታ ሌላው ሰው እንዲያደርገው የምንፈልገውን ነገር ሁሉ በመጀመሪያ እኛ በማድረግ ምሳሌን በመጣል መጀመር እንዳለብን አብርሃም ትምህርትን ሰጥቶን አልፎአል። ጌታ የተናገረንን በመታዘዝ መፈጸም በአካባቢያችን ባሉት ሰዎች ላይ ይህ ነው የማይባል የመታዘዝ ተጽእኖ ያመጣል። «የምላችሁን አድርጉ» ከማለት ይልቅ «የማደርገውን አድርጉ» ማለቱ ነገሩን ያቀልለዋልና።

ምዕራፍ ስድስት

የአብርሃም ጥሪና መለኮታዊ ጉብኝት (ዘፍጥረት 18-19)

«መጎብኘትህም መንፈሴን ጠበቀች» (ኢዮብ 10:12)::

ከእግዚአብሔር አስገራሚ መለኮታዊ አሰራሮች አንዱ የመጎብኘት ጊዜ ነው:: ጌታ አንድን ነገር ለመስራት በሚፈልግበት ጊዜ ሰዎችን ይጎበኛል:: የጉብኝት ቀን ሁለት አላማዎች አሉት:: አንደኛው አላማ በፊቱ በጽድቅና ራስን በማስገዛት ሲራመዱ የቆዩትን ህዝቡን፣ «የመጠበቂያ ጊዜ አበቃ፣ ዘመኑ የጉብኝት ዘመን ነው!» ብሎ ለማወጅ ሲመጣ፣ በሌላ ጎኑ ደግሞ በአመጽ የጸኑትን ሰዎች፣ «የትእግስት ዘመን አለቀ፣ ዘመኑ የቅጣት ዘመን ነው!» በማለት ይገለጣል:: በአጭሩ፣ መለኮታዊ ጉብኝት የሚመጣው የጌታን ተስፋ በመጠበቅ የጸኑትን ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ ለመካስ፣ በአመጻቸው የጸኑትን ደግሞ ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ ለመቅጣት ነው::

በዘፍጥረት ምእራፍ 18 እና 19 ውስጥ እንደምናጠናው፣ በአብርሃም ዘመን የሆነውም ይህ ነው:: ለብዙ ዘመን ጌታን በመጠበቅ የዛሉትን እነ አብርሃምን ቁርጠኛ ቀን ቀጠሮ ለመስጠት ጌታ ለጉብኝት መጣ! «የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ»:: አለቀ! ቀን ተወሰነ! ወይ ቀኑን አልነገረን፣ ወይም ደግሞ ተስፋ እንዳንቆርጥ በቶሎ አላከናወነውም የሚለው የሃሳብ መገላላት አበቃለት:: ቀድሞ መቼ እንደሆነ ባልተወሰነለት የጌታ የተስፋ ቃል እነ አብርሃም ነበሩ የሚፈተኑት:: አሁን ደግሞ ቀን ቀጥሮ «በእውነት» ብሎ በስሙ ቃለ መሃላን የገባው ጌታ የሚፈተንበት ጊዜ መጣ:: መለኮታዊ ጉብኝት ማለት ይህ ነው::

በእነዚሁ ምእራፎች ውስጥ እንደምንመለከተው፣ የጌታ ጉብኝት በአመጸ የጸኑትን ለመቅጣትም ይመጣል:: የግብረ ሰዶም ፈላስፎች የነገሱባት፣ የርኩሰትን መገለጥ ለማባዛት ራሳቸውን ለዲያቢሎስ ያስገዙ ኃጢአን የተንሰራፋባት ሰዶም ቀኗ ደረሰ:: ይህም ቀን የጌታ የጉብኝት ቀን ነው:: «እግዚአብሔር የለም ወይ? ካለስ ለምን እነዚህ ሰዎች እንዳሻቸው ሲሆኑ ዝም አለ» የሚለው አባባል የሚያቆምበት ቀን፣ የጉብኝት ቀን ይባላል:: አለቀ! ቀን ተወሰነ! እግዚአብሔር በቁጣ ተነሳ:: ቀድሞ፣ «ተመለሱ» ብሎ ሲለምን የነበረ እግዚአብሔር፣ «አባክህ ድረስልኝ፣ ከእንግዲህ አይለምደኝም» ተብሎ የሚለመንበት ዘመን መጣ!

ራሳችንን ከየትኛው ወገን አገኘነው? የጌታ የጉብኝት አዋጅ በሚታወጅበት በዚህ ዘመን ጌታ እያንዳንዱን እንደስራው ለመክፈል በመንፈሱ ይገለጣል:: የሚወሰንብን ውሳኔ ምን ይሆን? ትእግስታችን እስኪያልቅ ጌታን በማስከበር የጠበቅን ነን ወይስ ትእግስቱ እስኪያልቅ ጌታን በማሳዘን የጸናን?

ይህ ዘመን መለኮት በጉብኝት ወደ ህዝቡ የሚመጣበት ዘመን ነውና ምን እንደምናደርግ እንወቅ:: አብርሃምን ጌታ ሲጎበኘው ከተከናወኑት ሁኔታዎችና አብርሃም ከስጣቸው ምላሾች በመነሳት፣ መለኮት ሲጎበኘን ሊኖረን ስለሚገባ ምላሽ እናጢን::

1. መለኮት ሲጎበኝህ ለመሰዋት ሩጥ እንጂ ልመናን ለማቅረብ አትሩጥ

«በቀትር ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአደባባር ዛፍ ተገለጠለት . . . ወደ ምድርም ሰገደ ወደ ድንኳኑም ወደ ሳራ ዘንድ ፈጥኖ ገባና . . . ያዘጋጀውንም ጥጃ አመጣ ፣ በፊታቸውም አቀረበው»

- ዘፍጥረት 18:1-8

አብርሃም በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ ነበር ጌታ የጎበኘው:: እግዚአብሔር እንዲጎበኘው የማረፍና የመቀመጥ ሕይወት ነበረው:: ይህም ብቻ አይደለም፣ አብርሃም የጌታን ጉብኝት ለማስተናገድ ተነስቶ ሲሮጥ እንመለከታለን:: አብርሃም የጌታን ጉብኝት እንደተመለከተ የሮጠው ከጉብኝቱ የሚገኘውን ነገር ለመቃረም ሳይሆን ለጎበኘው ለእግዚአብሔር መስዋእትን

ለማቅረብ ነበር። በግንባሩ ተደፍቶ ከሰገደና አምልኮውን ካቀረበ በኋላ ይህም አልበቃ ስላለው ወደ ድንኳኑ ሮጦ መስዋእትን ይዞ ሲመጣ ይታያል።

እግዚአብሔር ሊሰራ የሚመጣበት ጊዜ የጉብኝት ዘመን ይባላል። ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ለጉብኝት ሲመጣ የሚባረክውን ለመባረክና የሚቀጣውን ደግሞ ለመቅጣት ነው የሚመጣው። ስለዚህም ጌታ ሲጎበኝን ጊዜ ሳናባክንና የመጣልን ጉብኝት ሳያልፈን ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምላሽ መስጠት አለብን። የምላሽ ሁሉ ምላሽ ደግሞ መስዋእትን በፊቱ ማቅረብ ነው። ለጎበኘን እግዚአብሔር የምናቀርበው ነገር ምን አለን?

አብርሃም ለጎበኘው እግዚአብሔር በምድር ሰገደ። ጌታ ሲጎበኘህ ሊቀድም የሚገባው አምልኮ እንጂ ልመና አይደለም። አብርሃም ለጎበኘው ለእግዚአብሔር መስዋእትን አቀረበ። ጌታ ሲጎበኝን ለመሰዋት እንዘጋጅ እንጂ ለልመና አንዘጋጅ። አብርሃም ለጎበኘው ለእግዚአብሔር እጅግ የሰባውን መስዋእት አቀረበ። ጌታ ሲጎበኝን ተራ መስዋእት አናቅርብ፤ ተራ ውሳኔን አንወስን፤ ተራ አመለካከት አንያዝ፤ ተራ ስጦታ አንስጠው። ሰፊ፣ የከበረና ታላቅ አምላክ ስላለን ለዚያ የሚመጥን መስዋእትነትና መሰጠት ከእኛ ይጠበቃል።

2. መለኮት ሲጎበኝህ ተፈጥሮ ሁሉ ለመታዘዝ እንደሚቆም አስታውስ

«አብርሃምና ሳራ በእድሜአቸው ሸምግለው ፈጽመው አርጅተው ነበር . . . እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፦ ካረጀሁ በኋላ በውኑ እወልዳለሁን? ስትል ሳራ ለምን ሳቀች? በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን?»

- ዘፍጥረት 18፡9-15

አብርሃምና ሳራ እግዚአብሔር የገባላቸውን ቃል ከወቅቱ ሁኔታቸው ጋር ማጣጣም ስላቃታቸውና መሸከም ስላልቻሉ ነበር በየተራ የሳቁት። አምላካዊው መልስ ግን «በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን» የሚል ነበር። እግዚአብሔር የተፈጥሮ አምላክ ስለሆነና የተፈጥሮን ህግ የደነገገ አምላክ ስለሆነ ያንኑ እሱው የደነገገውን ሕግ የመሻር፣ የመለወጥም ሆነ የማሻሻል መብቱ የተጠበቀ ነው። የእግዚአብሔር ጉብኝት ለአብርሃም ያበሰረለት የምስራች ይህ ነበር፦ ከተፈጥሮ ውስንነት የሚወጣን ታላቅ ስራ እግዚአብሔር መስራት ይችላል።

የእግዚአብሔር ጉብኝት የተፈጥሮን ሰዓት የሚያስቆም ትእዛዝ ይዞ ይመጣል። በተፈጥሮአዊው ውስንነታችን ችለን ያለፍናቸውን ጎዳናዎች አልፈን ወደማይቻለው ክልል ውስጥ ስንገባ እንቆማለን። ያን ጊዜ ነው ማንም የማያግደው እግዚአብሔር በጉብኝት መጥቶ የማይቻለውን ወደሚቻል የሚያመጣው። ይህም ማለት፣ ወደተገባልን ኪዳን እንዳንገባ የሚገዳደረን ነገር ሁሉ እድሜው እስከ ጉብኝት ቀን ድረስ ነው ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ጉብኝት የጤና መዛባት፣ የእድሜ ገደብና የአካባቢ ውስንነት ሁሉ ሳይቀሩ ይታዘዙታል። የእግዚአብሔርን ጉብኝት የተፈጥሮ ሕግ ይታዘዘዋል። መስራት ካለበትና እኛን መባረክ ካለበት ጸሐይን ያስቆማል፣ ስጋን እንደ ህጻን ልጅ ትኩስ ያደርጋል፣ ሙታንን ያስነሳል፣ አለቀ የተባለለትንም ጉዳይ ይቀጥላል። የእግዚአብሔርን ጉብኝት እየተመላለሰ በመምጣት የታወቀ የልምምድ አዙሪት ይታዘዘዋል። የእግዚአብሔር ጉብኝት ይዞ የሚመጣውን ትእዛዝ ለማስተናገድ የማይንበረከክ ነገር የለም። ይህንን ማመን ወደ አብርሃም በረከት ወራሽነት ያሻግረናል።

3. መለኮት ሲጎበኝህ ወሳኙ ችሎታህ ሳይሆን የባህሪይ ጥራት ነው

«እግዚአብሔርም አለ፦ እኔ የማደርገውን ከአብርሃም እሰውራለሁን? . . . ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ ልጆቹንና ከእሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝ አውቃለሁና»

- ዘፍጥረት 18፡16-19

አብርሃም በእግዚአብሔር ሲጎበኝ የመጣለትን የመገለጥ ጥልቀት የወሰነው ባለው ነገር ወይም በብቃቱ ሳይሆን በባህሪው ጥራት ነበር። እግዚአብሔር ከአብርሃም መገለጥን የማይከለክልበትን ምክንያት ሲናገር የጠቀሰው የአብርሃምን የባህሪይ ጥራት ነበር።

«በእውነት ታላቅና ብርቱ ሕዝብ ይሆናልና»፦ ለታላቅነትና ለብርቱነት ራስን መስጠት መገለጥን ያሰፋል። በዚህ፣ ታላቅ ከመሆን ተራ መሆን በሚቀልልበት ዘመን ታላቅና ብርቱ ለመሆን ራስን መስጠት ጠንካራ የባህሪይና የማንነት ጽንአትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው።

«የምድርም አሕዛብ ሁሉ በእርሱ ይባረካሉና»፦ ለብዙዎች በረከት ራስን መስጠት መገለጥን ያሰፋል። በዚህ፣ ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ከማደር

ማለፍ በተሳናቸው ዘመን ለሌሎች በረከት የመሆንን ማንነት ማዳበር ታላቅ የባህሪን ጨዋነት ያመላክታል።

«ጽድቅንና ፍርድን በማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ይጠብቁ ዘንድ»፦ ለጽድቅ፣ ለፍርድና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በተሰጠንበት መሰጠት መጠን መገለጣችን ይሰፋል። በዚህ፣ እውነተኛ ፍርድ በጠፋበት ትውልድ መካከል እየኖሩ ይህንን መገለጥ ይዞ መቆየት አስገራሚ ማንነት ነው።

«ልጆቹንና ከእርሱ በኋላ ቤቱን እንዲያዝዝ አውቃለሁና»፦ በስራችን መልካም ተጽእኖ በማምጣት የያዝንካቸው ሰዎች በበዙ መጠን መገለጣችን የጠለቀ ይሆናል። በዚህ፣ ማዘዝና መታዘዝ የሚባሉት እውነታዎች በጠፉበት አመጸኛ ትውልድ ውስጥ እየኖሩ ሌሎችን የማዘዝ ብቃት መያዝ ጨዋነት ነው።

«ይህም እግዚአብሔር በአብርሃም ላይ የተናገረውን ነገር ሁሉ ያመጣ ዘንድ ነው»፦ ቀድሞ ጌታ ስለእኛ የተናገረው ነገር መኖሩና ለዚያም ድምጽ ራሳችንን የመስጠታችን ሁኔታ መገለጥን ያሰፋል። በዚህ፣ ጌታን ለመስማትና ለመታዘዝ ራስን መስጠት በጠፋበት ዘመን ያንን ማድረግ ጌታን ይፈታዋል።

4. መለኮት ሲጎበኝህ ካለምንም አላማ አይመጣም

«እግዚአብሔርም አለ፦ የሰዶምና ገሞራ ጩኸት እጅግ በዝቶአልና፣ ኃጢአታቸውም እጅግ ከብዶአችና፣ እንግዲህ ወደ እኔ እንደመጣች እንደጩኸትዋ አድርገው እንደሆነ ወርጄ አያለሁ፣ እንዲሁም ባይሆን አውቃለሁ»

- ዘፍጥረት 18:20-21

አብርሃምን እግዚአብሔር ሊጎበኘው ሲመጣ ለእሱና ለሳራ የምስራችን ይዞ ከመምጣት ባሻገር፣ ኃጢአት ለበዛባቸው ለሰዶምና ለገሞራ የጎስቁላ አለዚያ የመቀጣት ምርጫን ይዞ ነበር የመጣው። አብርሃም የእግዚአብሔርን ጉብኝት ሲያስተናግድ የመጀመሪያው አይደለም። በድምጽና በራእይ ከዚህ በፊት በተለያየ መልኩ ወደ እሱ መጥቶ ነበር። በእያንዳንዱ እግዚአብሔር ወደ አብርሃም በመጣባቸው ሁኔታዎች ውስጥ መልእክትንና መመሪያን ይዞ ነው የመጣው።

እግዚአብሔር ሊጎበኝንና ሊናገረን ሲመጣ ለጨዋታና እንዲሁ ጊዜን ለማሳለፍ አይመጣም። ጌታ ከጎበኘን በኋላ በሕይወታችን የተሰራ ስራ ከሌለ፣

ጎበኘን ብለን የተናገርነው ነገር ከስሜት ያላለፈና የትም የማያደርስ ሆኖ እንዳይቀር ያሰጋናል።

ጌታ ጎበኘን፣ መገኘቱ በመካከላችን በኃይል ነበረ፣ እና እነዚህን የመሳሰሉትን የተለመዱ አባባሎቻችንን ከተናገርን በኋላ በግላጭ የሚታይ የሕይወት ለውጥና የአመለካከት ስፋት ካልተከሰተ የእግዚአብሔር ጉብኝት ትርጉም አልገባንም ማለት ነው።

ጌታ ሲጎበኘን ራሳችንን እንደመስታወት የሚያሳየንን እውነት ይዞ በመምጣት በጉልበት የሚያስኬድን የትህትና መንፈስ ይሞላብናል። ይህን መንፈስ ስናስተናግድ ብቻ እግዚአብሔር ሊናገረንና ሊያሳየን ይዞ የመጣውን መለኮታዊ እውነት መገንዘብ እንችላለን።

ጌታ ሲጎበኝ የበረከትንም ሆነ የፍርድን መልእክት ሚዛናዊ አድርጎ ነው የሚመጣው። እግዚአብሔር የበረከትን መልእክት ይዞ ሲመጣ እንኳ፣ እሱ ፍጹምና እንከን የማይወጣለት አምላክ በመሆኑ «የምነቅፍብህ አንድ ነገር አለኝ» በሚል መልእክት ለንስሃ እየጠራን ይመጣል። እናስተውል!

5. መለኮት ሲጎበኝህ ለሚሰጥህ መገለጥ አስተውለህ ምላሽ ስጥ

«አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር። አብርሃምም ቀረበ አለም፦ በውኑ ጻድቁን ከኃጢአተኛ ጋር ታጠፋለህን?»

- ዘፍጥረት 18:22-23

አብርሃም ከእግዚአብሔር የመጣለትን ሰዶምና ገሞራን የመቅጣት መልእክት እንደለማ ምን አይነት ምላሽ መስጠት እንደሚገባው አውቆ ነበር። የመጣለትን የቅጣት መልእክት ይዞ ሄዶ ለሰዎቹ የመናገር ወይም ደግሞ ጉዳዩን በዝምታ ማለፍ ሳይሆን ምልጃ እንደሚያስፈልገው አወቀ።

እግዚአብሔር አንድን ሁኔታ ሲገልጥልን ማድረግ የሚገባንን ማወቅ የመጀመሪያው እርምጃችን ሊሆን ይገባዋል። የእግዚአብሔር ጉብኝት መገለጥን ይዞ ይመጣል። ከጉብኝቱ በፊት ያላየነውን ነገር አሳይቶን ይሄዳል። በዚያን ጊዜ ለተገለጠልን እውነት ምን አይነት ምላሽ እንደሚጠበቅብን ማወቅ አስፈላጊ ነው።

አብርሃም በተገለጠለት ጉዳይ ላይ ጌታን ሲለምንና የምህረቱን ደጃፍ ሲያንኳኳ እንዳደረገው ለረጅም ጊዜ ከጌታ ጋር ተነጋግሮ አያውቅም።

እግዚአብሔርን ብዙ ከመለመኑ የተነሳ ይቆጣኛል ብሎ እስኪያስብ ድረስ በቀላሉ አልለቀቀውም ነበር።

በጉብኝት ወቅት በሰማነው ጉዳይ ላይ የእኛ ምላሽ ለውጥን የሚያመጣ ከሆነ እግዚአብሔርን በቀላሉ ልንለቀው አይገባንም። ምህረት ለሚያስፈልገው ምህረትን፣ ፈውስ ለሚገባው ፈውስን፣ እንዲሁም ጉብኝት ለሚሻ ጉብኝትን እስኪያደርግ ድረስ መለመን አለብን።

አብርሃም በእግዚአብሔር ፊት በቅንነት በመሄድ ብቻ በሚከናወነውና ከዚያም አልፎ የግድ በምልጃ ልንወድቅለት በሚገባው ነገር መካከል ለይቶ አውቆ ነበር። ይህንን እውነታ መገንዘብ ለእግዚአብሔር ለምንሰጠው ምላሽ አስፈላጊ መረዳት ነው። እግዚአብሔር ሲናገረን በአንድ ጎኑ «እሱ እግዚአብሔር ነው፣ የወደደውን ያድርግ» ብለን የምንተውለት ጉዳይ ሲኖር፣ በሌላ ጎኑ ደግሞ እግዚአብሔር ምላሽን እስኪሰጥ ድረስ በምልጃ የምንወድቅበት ጉዳይ አለ። በእነዚህ ሁኔታዎች መካከል መለየትና ምላሻችንን ማስተካከል አስፈላጊ ነው።

6. መለኮት ሲጎበኝህ ሳያስጨርስህ አይሄድምና ሳትጨርስ አትልቀቀው

«እግዚአብሔርም ከአብርሃም ጋር ንግግሩን በጨረሰ ጊዜ ሄደ፤ አብርሃምም ወደ ስፍራው ተመለሰ»

- ዘፍጥረት 18:32

አብርሃም የራሱን ሃሳብ ተናግሮ ብቻ አልነበረም የሄደው። እግዚአብሔር የእርሱን ነገር አስጨርሶት መሄዱን ከተመለከተ በኋላ ነበር የሄደው። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የጀመረውን ነገር ሳይጨርስ በፍጹም አይሄድምና በቀላሉ ልንለቀው አይገባም። «አንኳኩ» ብሎ የመከረን ጌታ ካለማቋረጥ ደጆቹን እንድናንኳኳ ይፈልጋል። ንጉስ ነውና ደጅ ሊጠና ይገባዋል።

አብርሃም የእግዚአብሔርን ምህረት የለመነበትን የምልጃውን ቁጥር በአስር ጸድቃን ላይ ባያቆመው ኖሮ ምናልባት የሰዶም ታሪክ ይለወጥ ይሆን? አስር ቁጥር ላይ ያቆመው አብርሃም ነው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም። እግዚአብሔር በመንፈሱ ወደ ልባችን በመፍሰስ አንድን ሃሳብ ሲመጣና እንድንጸልይ ሲያነሳሳን የምንለምነውን ለመስማትና ለማድረግ ነውና በቀላሉ መሄድ የለብንም።

አብርሃም ምልጃውን የገታው ጌታን እንዳስቸገረው ተሰምቶት ይመስላል (ዘፍ. 18:27፣ 31 እና 32)። ይህንን እውነት እናስታውስ፦ ጌታን ምንም ነገር ብንጠይቀውና ደጁን ጠንተን ብንወተውተው እናስደስተዋለን እንጂ በፍጹም አናደክመውም። ጥቂት ስለጸለይን የማናገኛቸውን ነገሮች በብዙ ጌታን ስለለመንነውና ስለማለድን አናገኛቸዋለን።

አብርሃም ምልጃውን ያቆመው የምህረትን ሁኔታ በሰው እይታ ተመልክቶት ይመስላል። የሚታይህን ነገር እግዚአብሔር በእንዴት አይነት ሁኔታ እንደሚያየው አታውቅምና አስፍተህ እይ፣ አስፍተህም ጠይቅ።

እግዚአብሔር ንግግሩን ሲጨርስ መሄዱና አብርሃምም ሲጨርስ ወደ ስፍራው መመለሱ አብርሃም እግዚአብሔርን የሚገናኝበት ስፍራ እንደነበረው ያሳያል። ጌታን የምትገናኝበት መደበኛ ስፍራህ የት ነው?

7. መለኮት ሲጎበኝህ የሚሰጥህ መገለጥ አይሳሳትምና ችላ አትበለው

«እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ላይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ እሳትና ዲን አዘነበ፤ እነዚያንም ከተሞች፣ በዙሪያቸውም ያለውን ሁሉ፣ በከተሞቹም የሚኖሩትን ሁሉ፣ የምድሩንም ቡቃያ ሁሉ ገለበጠ»

- ዘፍጥረት 19:24-28

እግዚአብሔር ስለ ሰዶም ታላቅ ጥፋት ለማወጅ ታላቅ ጉባኤንና ታላላቅ ነገስታቶችን አልጠራም። እግዚአብሔር ይፈልግ የነበረው አንድን ነገር ነበር - ትልቅ ልብ ያለውን ሰው። አንድን ትልቅ ልብ ያለውን አብርሃምን አግኝቶ ጠራውና የልቡን አካፈለው። ጌታ ትልቅ ልብ ካገኘ ትልቅን ጉባኤና ታላላቅ ሰዎችን አይጠበቅም። ልቡን ባዘጋጀለት ሰው ውስጥ ሆኖ መስራት የሚፈልገውን ሁሉ ይሰራል።

እግዚአብሔር ስለ ሰዶም ታላቅ ጥፋት ለማወጅ ታላቅና አስፈሪ ድምጽ አላንጎደጎደም። ጌታ በረጋ ሁኔታ የሚያሰማትን ድምጹን በተረጋጋ መንፈስ ሰምቶ የሚታዘዘው ሰው ካገኘ «ትልቅ» ድምጽ ማውጣት አያሻውም። እግዚአብሔር የሚሰማውንና የሚታዘዘውን ሰው ይፈልጋል። እግዚአብሔር እውነተኛና የተዘጋጀ ልብ ያለውን ሰው ይፈልጋልና እንገኝለት።

እግዚአብሔር ስለ ሰዶም ታላቅ ጥፋት ለማወጅ ረጅም ሕልምና ትንቢትን አላመጣም። ጌታ ትኩረቱ ያለው መልእክቱ መተላለፉ ላይ፣ ናፍቆቱ

ደግሞ የሚታዘዘው ሰው ማግኘቱ ላይ ነው እንጂ እኛን በራእይ ጥልቀትና ስፋት ማስገረም አይደለም። ራእይ፣ ድምጽ፣ ትንቢትና መገለጥ ከመጣና ከሄደ በኋላ ጌታ አንድን ነገር ይጠባበቃል፦ የመጣውን እውነት የሚታዘዝና የሚተገብር ሰው!

እግዚአብሔር በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ፣ በለመድነውም ሆነ ባልለመድነው መልክ ሲመጣና ሲናገረን ልንታዘዝ ይገባናል። እግዚአብሔር ቀድሞ ባልተለማመድነው መንገድ ስለመጣና ስለተናገረን ውጤቱን የተሰየ አያደርገውም። መመለስ ያለበት ጥያቄ፦ ጌታ ተናግሮአል ወይ? የሚለው ነው። የተናገረን እግዚአብሔር ከሆነ፣ ሁኔታው የማይመስል ቢሆን እንኳ፣ «ጌታ ተናገረ እኔም ይህንን ብቻ ሰማሁ፣ ኃይል የእግዚአብሔር ነው» በማለት መታዘዝ ከእኛ ይጠበቃል።

ምዕራፍ ሰባት

የአብርሃም ጥሪና የጠሪው ስጦታ (ዘፍጥረት 20-22)

«በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፣ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃን አባት ይወርዳሉ» (ያዕ. 1:17)።

የእኔ ነው ብለን ያመንነውን ነገር ሰው ሲነካብን ያለመውደዳችንን የእኛ ን የሰው ልጆች ባህሪይ እንስሳትም ሳይቀሩ ይጋሩናል። ሰው ከልጅነቱ ጀምሮ በእጁ የደረሰበትን ነገር አጥብቆ በመያዝ የታወቀ ፍጥረት ነው። ሕጻናት እንኳ ገና በእንጭጭነታቸው ከሚታይባቸው ባህሪይ አንዱ በእጃቸው የያዙትን በቀላሉ ያለመልቀቅ ዝንባሌ ነው።

የእኛ ነው ብለን ባመንንበት ነገር ዙሪያ ቅጥርን እንሰራና፣ ማንም ያንን ቅጥር ቢተላለፍ አጸፋውን ለመመለስ ዝግጁ መሆናችንን እናሳያለን። ለምሳሌ፣ ሰውም ሆነ ማንኛውም የእንስሳ ዘር የእኔ ነው ብሎ ከሚያምንባቸው ነገሮች ሁሉ አስበልጦ የሚያየው ነገር ቢኖር የገዛ ልጁን ነው። ይህም አመለካከቱ ልጁን ለማንም አሳልፎ ላለመስጠት በሚከፍለው ዋጋ በገሃድ ይታያል። ለብቻቸው ቢሆኑ ሮጠው ማምለጥን የሚመርጡ ሰዎች፣ ልጃቸው አጠገባቸው ስላለ ብቻ እስከሞት ድረስ ለመፋለም ሊያሸንፉት እንደማይችሉት ከሚያውቁት አውሬ ጋር ሳይቀር እንኳ ሲጋፈጡ ማየት አስገራሚ ነው።

ባጠቃላይ እኛ የሰው ልጆች የእኛ የሆነውን ነገር ሌላው ሲነካብን አንወድም። እንደውም የእኛ የሆነውን ነገር የመውሰድ አዝማሚያ ያየንባቸውን ሰዎች ከወዲሁ ለማሳወቅ ስናገልላቸው ሁሉ እንታያለን።

አንድ ልንክደው የማንችለው እውነት ግን አለ። ይህም እውነት፣ የእኛ የሆነውን ነገር ከእኛ ለመንጠቅ ያደባው ሰው፣ እንስሳ፣ አጋንንትም ሆነ ልዩ ፍጥረት በብርታት ወይም በጥበብ ከእኛ ከበለጠ ምንም ያህል እንጣር፣ የእኛ ነው ያልነውን ነገር ማጣታችን ነው። ለዚህ አስደንጋጭ ሁኔታ መፍትሄው፣ የምንችለውን ሁሉ ካደረግን በኋላ፣ ከስልጣን ሁሉ በላይ ስልጣን ባለውና፣ ከኃያላንም ሁሉ በላይ ኃያል በሆነው በእግዚአብሔር መታመን ነው።

እንግዲህ ይህንን የራሳችንን የሆነውን ነገር የመጠበቅ ዝንባሌ ያብላላነው ሁኔታውን ከተፈጥሮአዊው አይታ አንጻር በማገናዘብ ነው። በተፈጥሮአዊው አይን ስናየው አንድ ሰው የእሱ የሆነውን አሳልፎ ላለመስጠት የተለያዩ ምርጫዎችን ሊጠቀም ይታያል።

አንዳንዶቻችን የእኛ ነው ብለን በምናምነው ነገር አካባቢ ሰዎች ያንገበግቡ እንደመሰለን አደኑን ሊነጠቅ እንደቀረበ አንበሳ አስደንጋጭ ድምጽን እናሰማለን። ሌሎቻችን ደግሞ የዚህ አይነቱ ሰው ተቃራኒ ነን። አንድ ሰው ወይም ሁኔታ ገፍቶ አይምጣ እንጂ፣ ከመጣ ግን ካለምንም ተግዳሮት የምንነጠቅ ሰዎች ነን። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት አይነት አቀራረቦች ከመስመር የወጡ ናቸው።

የእኛ ነው ብለን ከጌታ የተቀበልነውን ማንኛውም ነገር በእንዴት አይነት ሁኔታ ነው ልንጠብቀው የምንችለው? አንድ ነገር ሙሉ በሙሉ ከጌታ የተቀበልነው ነገር መሆኑን ካመንን በኋላ የእኛ ሃላፊነት ምን ድረስ ነው? የጌታስ ሃላፊነት የቱ ድረስ ይመጣል? ተፈትኖ ከወጣው የእምነት አባታችን ከአብርሃም ሕይወት የምንማራቸው እውነታዎች ከብዙ ጥፋት ያድኑናልና እናጢናቸው።

1. ጌታ የሰጠህ ነገር የአንተ ነው

«እነሆ፣ አንተ ስለወሰድካት ሴት ምውት ነህ፤ እርስዋ ባለ ባል ናትና»

- ዘፍጥረት 20:3

አብርሃም ሳራን እጅግ አድርጎ እንደሚወዳትና ውበቷንም በሚገባ እንደሚያደንቅ ግልጽ የሆነበት ክፍል ቢኖር ይህ ክፍል ነው። ውበቷን ያየ ሰው ልቡን ወደ እሷ እንደሚያዘነብል የተገነዘበው አብርሃም በአቤሜሌክ ፊት ሲቀርብ በእሷ ምክንያት ችግር ይገጥመኛል ብሎ ሰጋ። እውነቱ ግን እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለሳራ የገባላቸውን ኪዳን ሳይፈጽም ምንም

እንደማይሆን ነው። በአጭሩ፣ ሣራ የአብርሃም እንጂ የአቢሜሌክ ሚስት ስላልሆነች ለአቤሜሌክ ሣራን መውሰድ አልተፈቀደለትም።

ከአብርሃም እንደምንማረው፣ ጌታ ለእኛ ብሎ የሰጠን ማንኛውም ስጦታ የእኛ እንደሆነና ማንም ሊወስደው እንዳልተፈቀደለትም፣ እንደማይችልም ነው። ጌታ ለእኛ ብሎ የሰጠንን ነገር ማንም ሰው በተንኮል ቢወስድ፣ አቤሜሌክ የአብርሃምን ስጦታ ሳራን ሲወስድ እንደሆነ፣ ከዚያው ጋር አብሮ መርገምንም ጭምር ይወስዳልና ስለሁኔታው ጌታን ማሳሰብ እንጂ ከሁኔታው የተነሳ እንቅልፍ ልናጣና ልንረበሽ አይገባንም።

ጌታ የሰጠንን ስጦታ እንድንንከባከበው፣ እንድንጠብቀውና እንድንደሰትበት እንጂ ከእሱ የተነሳ ከእጁ ይወጣ ይሆን እያልን እንቅልፍ አጥተን እንድናድርና የስጋት ህይወት ውስጥ እንድንገባ የጌታ ሃሳብ አይደለም። ቃሉ እንደሚል ሁሉን ነገር ጌታ የሚሰጠን በእሱ ደስ እንዲለንና ስሙንም እንድናከብርበት፣ በዚያም ውስጥ ለበረከት እንድንውል እንጂ ለመርገም አይደለም።

ጌታ የሰጠን ነገር ከእጃችን በቀላሉ ሊወሰድ የሚችለው በሚገባ በማንይዝበት ጊዜ ብቻ ነው። የእግዚአብሔር ስጦታ በሚገባ ሊያዝና እግዚአብሔር ላቀደለት ዓላማ ልንጠቀምበት ይገባናል። ይህ በማይሆንበት ጊዜ ጠላት በቀላሉ መጥቶ ሊያጠቃንና ስጦታችንን ሊወስድብን ይችላል።

2. ጌታ የሰጠህ ነገር ጊዜውን ጠብቆ ይመጣል

«እግዚአብሔርም እንደተናገረው ሳራን አሰበ፤ እግዚአብሔርም እንደተናገረው ለሳራ አደረገላት። ሳራም ጸነሰች፣ እግዚአብሔርም በተናገረው ወራት ለአብርሃም በእርጅናው ወንድ ልጅን ወለደችለት»

- ዘፍጥረት 21:1-2

አብርሃም ይስሃቅን ከእግዚአብሔር ከመቀበሉ በፊት የተሰፋ ቃልን ነበር የተቀበለው። በይስሃቅ በኩል እንደሚባርከውና የብዙ አሕዛብ አባት እንደሚያደርገው የተሰፋ ቃልን ከተቀበለ በኋላ ግን ብዙ ተፈትኗል። ይህም የተሰፋ ቃል ፈተና አብርሃም ከሚስቱ ከሳራ ጋር መክሮ የስጋን መንገድ ለመከተል እስኪወስኑና እስማኤልን ለማትረፍ እስኪበቁ ድረስ ተገዳድሮአቸው ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በገባው ቃል መሰረት ይስሃቅን ለአብርሃም አሳቀፈው።

አንድን ነገር እናስታውስ፡- ጌታ የገባልን ቃል ምንም ያህል ረጅም ዘመን የቆየ ቢመስለንም እንኳ ጊዜውን ጠብቆ መምጣቱ አይቀርም። እንዳንድ ጊዜ የተስፋ ቃሉን ስንቀበል የነበረን የውስጥ ግለት ሁኔታውን በአጭር ጊዜ የምንቀበል እስኪመስለን ድረስ የራሳችንን ጊዜ ገደብ እንሰፍርና መጠበቅ እንጀምራለን። ብዙም ሳንቆይ ግን የጊዜው ጉዳይ በእኛ ሳይሆን በእግዚአብሔር እጅ እንደሆነ እንገነዘባለን።

ጌታ ያንተ ነው ብሎ የገባልን ኪዳን ከፍጻሜአችንና ጌታ በሕይወታችን ካለው ዓላማ ጋር የተያያዘ ስለሆነ ያንን ነገር ላለመስጠት አይችልም - ቃሉን መሻር ስለማይችል። ይልቁንም ጌታ የገባልንን ቃል ለመፈጸም ስጦታውን ይዞ ሲመጣ ኪዳኑን በመጠበቅ ዝለን በስጋችን ለመሙላት ስንሯሯጥ ከስፍራችን እንዳያጣን ጥንቃቄ ልንወስድ ይገባናል።

የእድሜ መግፋት፣ የጤንነት መቀየር፣ የፖለቲካ መለዋወጥ፣ የኢኮኖሚ ዝቅጠትና፣ የሰው ወረተኛነት ጌታ ለእኛ በገባው የተስፋ ቃል ኪዳን ላይ ቅንጣት ለውጥ ሊያመጣ እንደማይችል በማመን ጽኑ ልንሆን ይገባናል። የተስፋውን ቃል አቅፈን በጤናማ ሁኔታ ጌታን ከጠበቅነው በሕይወታችን የሚመጡ ሁኔታዎች ሁሉ መሸጋገሪያ ድልድይ ይሆኑናል እንጂ እንቅፋት ሊሆኑን አይችሉም።

3. ጌታ የሰጠህ ነገር አንተ በስጋህ ካመጣኸው ነገር ጋር አብሮ መኖር አይችልም

«ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድድ፤ የዚህች ባሪ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አይወርስምና»

- ዘፍጥረት 21:10)

አብርሃም ጌታን በመጠበቅ ብዙ የቆየ ሲመስለውና መጠበቅ ሲታክተው የተስፋ ቃሉን ለጣጥፎ በስጋው ፈጠረው። ጌታ የገባለትን ያንን የልቡን ናፍቆት የሚያሟላለትን የተስፋ ቃል ይስሃቅን ጠብቆ ያላገኘ ሲመስለው ወደ አጋር በመግባት እግዚአብሔርን ለማገዝ ሞከረ። እስማኤል በአብርሃም ቤት በሰላም የኖረው እውነተኛውን የእግዚአብሔርን ተስፋ የተሸከመው ይስሃቅ እስኪመጣ ድረስ ብቻ ነበር። ይስሃቅ ከተወለደ በኋላ በስጋ በተወለደውና በኪዳን በተወለደው መካከል ውጥረት መፈጠር ጀመረ። በስጋ የመጣው በመንፈስ ከመጣው ጋር ሊወርስ አይችልምና አንዱ መውጣት ነበረበት።

እግዚአብሔር የገባልንን የተስፋ ቃል ይዘን በስጋችን ወዲህና ወዲያ ብለን አንድን ነገር ልናቅፍ እንችላለን። ችግሩ ግን ያለው እዚህ ጋር ነው፣ በስጋችን ጎትተን ያመጣነውን ሁኔታ ጉያችን ካስገባን በኋላ የእግዚአብሔር እውነተኛው ነገር ሲመጣ አብረው መኖር አይችሉም። በስጋችን ያመጣነውን ፍሬ አውጥተን እስክንጥል ድረስ በእውነተኛውና ጌታ በሰጠን ስጦታ መደሰትና መባረክ አንችልም።

የተስፋው ቃል እስኪመጣ ድረስ ዮሴፍን እንደፈተነው እኛንም እንደሚፈትነን ጥርጥር የሌለው እውነት ነው። ሆኖም፣ ምንም ያህል ፈተና ቢበዛ ጌታን ጠብቀን የተገባልንን ተስፋ መቀበል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ጌታን መጠበቅ ተስኖን በስጋችን ያመጣነው ነገር አብሮን እስካለ ድረስ በሕይወታችን ሰላም አይኖርምና ነው።

ጌታ ያልሰጠንንና በስጋችን ያመጣነውን ነገር ከሕይወታችን ማስወጣት አለብን። ከጌታ ያልተቀበልነውን ነገር ስንለየው ውስጣችን ብቻ በሚያውቀው ቀጠሮ ነገ ልንመለስበት እንደምንችል እያሰብንና ለመመለስ እንዲመቸን አድርገን በሩን ገርበብ አድርገን ከማለፍ መጠበቅ አለብን። በፍጹም ንክኪ ሊኖርህ እስከማይገባን ድረስ ልንለያቸው የሚገቡን ነገሮች እንዳሉ አንዘንጋ።

4. ያንተን ነገር የተሻሙ የጌታ ከአንተ ጋር አብሮነት በግላጭ ያያሉ

«በዚያም ዘመን አቢሜሌክ . . . አብርሃምን አለው፡- በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው»

- ዘፍጥረት 21:22

አቤሜሌክ ከዚህ በፊት የአብርሃም ሚስት የሆነችውን ሳራን ለመውሰድ የቃጣውና እስኪቀጣም ድረስ የደረሰ ሰው ነበር። አሁን ግን የእግዚአብሔርን ክንድ ከተመለከተ በኋላ አብርሃምን የሚያግዝ መለኮታዊ ኃይል እንዳለ ገባው። አብርሃም ቀድሞ ሚስቱን ከወሰደበት ከአቤሜሌክ አንደበት ለጌታ ክብር የሚሆንን ምስክርነት ሰማ። አቤሜሌክ ወደ አብርሃም መጥቶ ክብርን ለአብርሃም አምላክ ሰጠ እንጂ አብርሃም ወደ አቤሜሌክ አልሄደም።

በጌታ ከታመንን ከጌታ የተስጠንን መልካም ነገር በኃይሉ ተመክቶ የቀማንን፣ በሽንገላ ያታለለንንና የእኛ የሆነውን ነገር ሁሉ የተመኘውን ሰው ለጌታ ክብር ሲንበረከክ እናየዋለን። ከእኛ በላይ እንደሆነ ራሱን ያገነነና

የፈለገውን ነገር በፈለገው ጊዜና ሁኔታ ማድረግ እንደሚችል የተሰማውን ሰው እግዚአብሔር መጥቶ በእኛ ላይ ብቸኛ ስልጣን ያለው እሱ ብቻ መሆኑን ያሳያል።

በጌታ ከታመንን በክፉ የሚነሳብንን ሁሉ በመልካም እናሸንፋለን። በእኛ ያለው በዚያ ካለው ስለሚበልጥ ከማንኛውም ሁኔታና ተግዳሮት በላይ መኖር የሚያስችልን አቅም ይሰጠናል። ክፉው በእኛ ላይ በሚያመጣው ክፋትና ትኩረታችንን ከጌታ እንድናነሳ ለማድረግ በሚያስማን ዛቻ ሳንረበሽ የጠራን ጌታ ላይ ልቦናችንንና እምነታችንን ብንጥል በመጨረሻ ድል የእኛ ነው።

በእግዚአብሔር ከታመንን ከእጁ የተቀበልነውን መልካም ስጦታ ሁሉ እንዳስከበርን እንኖራለን። በጌታ ጠባቂነትና ጋሻነት ከታመንን ጠላቶቻችን ሳይቀሩ ጌታ ከእኛ ጋር እንደሆነ እስኪመሰክሩ ድረስ እንጸናለን። ስልፉ የእግዚአብሔር እንደሆነና የእኛ ስራ በእርሱ በመታመንና እሱን በመታዘዝ መኖር ብቻ እንደሆነ ወደ ማወቅ መረዳት ስንመጣ የክብሩ እሳት ቅጥራችን ይሆንልናል።

5. ጌታ የሰጠህን «የአንተን» ነገር እንድትሰዋለት ይጠይቅሃል

«ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው፣ እንዲህም አለው፦ አብርሃም ሆይ። አብርሃምም፦ እነሆ አለሁ አለ። የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሃቅን ይዘህ ወደ ሞሪያም ምድር ሂድ፣ እኔም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መስዋእት አድርገህ ሰዋው አለ»

- ዘፍጥረት 22:1-2

አብርሃም ይስሃቅን የተቀበለው ከብዙ ምጥና እንባ በኋላ ነበር። ይህንን በመከራ የወለደውን አንድያ ልጁን ከምንም ነገር አብልጦ እንደሚወደው ግልጽ ነው። እንግዲህ ይህንን እግዚአብሔር የአንተ ነው ብሎ የሰጠውን ብቸኛ የሆነውን ልጁን ነበር ለመስዋእትነት የተጠየቀው። ይህንን ጥያቄ እግዚአብሔር ሲያቀርብለት በአብርሃም ጭንቅላት ውስጥ ምን አይነት ሃሳብ ሊያልፍ እንደሚችል መገመት አያስቸግርም። እግዚአብሔር ይዋሻል ማለት ነው? ይህ ጥያቄ የመጣው በእርግጥ ከእግዚአብሔር ነው? ለምን እግዚአብሔር ከሰጠኝ በኋላ መልሶ ለመውሰድ ፈለገ? ይህ ሁሉ ጥያቄ ቢኖርም ለእግዚአብሔር ምላሽ መሰጠት ነበረበትና አብርሃም እሺ አለ።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ በምናደርገው ጉዞአችን ጌታ የምንወደውን የእኛ ነው የምንለውን ነገር እንድንተውለትና እንድንሰዋለት ይጠይቀናል። በእጃችን የገባውንና በመግባቱም ደስ ብሎን ጌታን ያመሰገንንበትን ነገር ጌታ መጥቶ «ይህንን ነገር ልቀቀው» ሲለን ጉዳዩ ለታላት ፈተና እንደሚሆንብን ጥርጥር የለውም።

ጌታ የምንወደውንና የእኔ ነው ያልነውን ነገር የሚጠይቀን በልባችን ሙሉነት እሱን መከተላችንንና አለመከተላችንን ያውቅ ዘንድ እኛን ለመፈተንና የውስጣችንን ለማወቅ ነው። ከሰጪውና ከስጦታው የቱን እንደምናስበልጥና ልባችንን የሚረከው የትኛው እንደሆነ ዋናው መመዘኛው ይህ ብቻ ነው። «ውድ» የሆነውን ነገራችንን ስንጠየቅ የምንሰጠው ምላሽ ወሳኝ ነው።

ጌታ፣ አንድን ነገር «ሰዋልኝ፣ ለእኔ ስትል ተወው» ሲለን ብንታዘዘው፣ ነገሩን ከሞት እንኳን አስነስቶ መልሶ ሊሰጠን እንደሚችል ልናምነው ይገባል። አብርሃም ይስሃቅን ሊሰዋ ሲዘጋጅ እግዚአብሔርን ያመነው በእንዲህ አይነት እምነት ነውና።

6. የአንተ የሆነውን ስትጠየቅ ተግባራዊ ምላሽህ የልብህን ቅንነት ያሳያል

«አብርሃምም በማለዳ ተነስቶ አህያውን ጫነ፣ ሁለቱንም ሎሌዎቹንና ልጁን ይስሃቅን ከእርሱ ጋር ወሰደ፣ እንጨትንም ለመስዋእት ሰነጠቀ፣ ተነስቶም እግዚአብሔር ወዳለው ቦታ ሄደ»

- ዘፍጥረት 22:3

አብርሃም ይስሐቅን እንዲሰዋ ከተናገረው በኋላ ግራና ቀኝ ሳይል ወደ ተግባር ሊሄድ እንጂ ንግግር ሲያበዛ በፍጹም አይታይም። አብርሃም የገባው አንድ እውነት አለ፦ እምነትና መታዘዝ የአንደበት ጉዳይ ሳይሆን በተግባር የሚገለጥ ምላሽ ነው። ለአብርሃም እግዚአብሔርን መታዘዝ ማለት የተነገረውን ካለምንም ጥያቄ ወደተግባር መለወጥ እንጂ በአንደበት ብዙ ቃል መግባት ብቻ አይደለም።

ጌታ አንድን ነገር ለእርሱ ክብር እንድንሰዋለት ሲጠይቀን፣ ከሁሉ በፊት ጥያቄው በትክክል ከጌታ መምጣቱንና ከስሜታችን የመነጨ ጉዳይ እንዳልሆነ ማረጋገጥ አለብን። ያንን በሚገባ ካረጋገጥን በኋላ ጌታ ስላዘዘን የመስዋእትነት ነገር ለምክር ወደ «ተቀቡ» ሰዎች ብንሄድ፣ «ነቢያትን»

ብናማክር፣ ወይም ደግሞ ይህንና ያንን ብናደርግ አንዱም ነገር የጌታን ትእዛዝ አይለውጠውም።

ጌታ የመስዋእትን ነገር ሲናገረን፣ የትእዛዙ እውንነት ከሰጠን የልብ ግለት ሳንበርድ ልንተገብረው ይገባል። ጌታ እንደተናገረን ያረጋገጥነውን ነገር በአእምሮአችን ስናወጣና ስናወርድ፣ ከሰዎች ጋር ጉዳዩን በዚህና በዚያ መልኩ ስንወያየው፣ የማመቻመች መንገዶችን ስናስላስል ብዙ ከሰነበትን በኋላ እንታዘዘዋለን ማለት ዘበት ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሁኔታዎች የጌታ ድምጽ በልባችን የሰጠንን፣ ለመታዘዝ የሚረዳንን ግለት ስለሚያበርዱት ነው።

ጌታን ባዘዘን ጊዜ በውስጣችን ከሚመጣ የመንፈስ እገዛና ግለት የተነሳ አለመታዘዝን እንደ እብደት እንቆጥረዋለን። ጌታ ያዘዘንን ሳንታዘዘው ጊዜው ካለፈ በኋላ ግን «ታዝገፎው ቢሆን ኖሮ» የሚለውን ነገር ስናስበው የመታዘዙን ነገር እንደ እብደት ልናየው እንችላለን። በጊዜው ምላሽ ያልሰጠንለትን ትእዛዝ ከጊዜ በኋላ ስናስበው እንደቅዠት የመቁጠር ዝንባሌ አለን። ጌታ አንድን ነገር ሲያዘን ነገሩን ሳናውጠነጥንና የስጋ ለባሽን ሃሳብ ሳናስገባ የሰጠነው ምላሽ ትክክለኛው ምላሽ ነው።

7. ለመስዋእትነትህ አምላካዊ መልስ የሚመጣው በመጨረሻው ሰዓት ላይ ነው

«በብሳቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት»

- ዘፍጥረት 22:9-24

አብርሃም ለታዘዘው ነገር ምላሽን ሲሰጥ፣ ጌታ ጣልቃ እንደሚገባ ውስጡ ያውቀዋል። እግዚአብሔር ጣልቃ ባይገባና ባያስቆመው እንኳ የሰዋውን ልጁን ከሞትም ቢሆን አስነስቶ ሊሰጠው እንደሚችል ያምን ነበር። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር ቶሎ አልመጣም ነበር። አብርሃም እስኪፈተንና በልቡ ያለው ምን እንደሆነ እስኪታወቅ ድረስ ነበር ጌታ ዘግይቶ የመጣው። ይስሐቅን በቢላዋ እስከሚሰዋው ድረስ እግዚአብሔር ዝም ቢለው ኖሮ አብርሃም በርግጥ ያደርገው ነበር? ቃሉ እንደሚመሰክርለት አብርሃም ያንን ከማድረግ የሚከለክለው ነገር እንዳልነበረ እናስተውላለን።

አንድን መስዋእት እውነተኛ መስዋእት የሚያሰኘው እስኪፈትነን ድረስ መገዳደሩ ነው። እግዚአብሔር የእኛ ነው የምንለውን ነገር ለእርሱ ክብር እንድንተውለት ሲናገረን ነገሩን ከመውደዳችን የተነሳ ከእኛ እንዲለይ

እንደማንፈልግ ያውቀዋል። ለዚህም ነው ጥያቄውን የሚያቀርብልን። ለቀረበልን የመስዋእትነት ጥያቄ የምንሰጠው መልስ በኃይማኖታዊ ቋንቋ ስለተሞላንና ሌላ መልስ ስለማይቀናን ከሆነ ጌታ መርምሮ ያውቀዋል፣ ፈተናውንም እንወድቃለን። ሁኔታው የሚታወቀው ግን ጌታ እስክ መጨረሻው ዝም ሲለን ነው።

ለመክፈል ፈቃደኛ ለምንሆንበት ለማንኛውም መስዋእትነት አምላካዊ መልስ እንዳለ ማወቅና መረዳት አስፈላጊ ነው። መልሱ የሚመጣው ግን የውስጣችን ሁኔታ በውጫዊ ተግባራችን ታይቶና ፈተናውን አልፈን እውነተኛ መሆናችን ሲረጋገጥ። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር የጠየቀንን ብንሰጠው አንጠቅመውም፣ ባንሰጠውም አንጎዳውም። በሁኔታው ተሰርተንበትና ተባርከንበት የምናልፈው እኛው ነን። ስለዚህ፣ እግዚአብሔር እንድንሰጠው ወይም እንድንሰዋለት ለጠየቀን ነገር አሁኑኑ ምላሽ ልንሰጠው ይገባል።

ይህንን አንዘንጋ፣ እግዚአብሔር የሰጠን ነገር ሁሉ የእርሱ ስለሆነ መልሶ የመጠየቅ መብት አለው። የሚጠይቀን ደግሞ የምንወደውን ነገር ነው፣ ምክንያቱም የምንጠላውንና የማንፈልገውን ነገር ብንተው መስዋእትነት አይደለምና ነው። ስለዚህ፣ ትክክለኛ መስዋእት ከራሳችን ጋር ሳይቀር ያጣላናል፡- አእምሮአችን ስለማይፈልገው ያዝናል፣ ልባችን ግን ጌታን ስለታዘዘ ይደሰትበታል። የውስጥ ትግል የማይቀር ነው።

የትክክለኛ መስዋእት ግፊትና ውሳኔ ከውስጥ ፈንቅሎ መውጣት አለበት። ሰዎች በጌታ ስም ተናግረውና በመናገር ችሎታ አሳምነውን ለወሰንነው የመስዋእትነት ውሳኔ ጌታ ተጠያቂ አይደለም። ትክክለኛ ዋጋ አከፋፈል ሁለት ነገሮችን ያካትታል፣ ጌታ ተው ያለውን ነገር ዋጋ በመክፈል መተው እና ጌታ አድርግልኝ ወይም ስጠኝ ያለንን ነገር ዋጋ በመክፈል ማድረግና መስጠት። «መታዘዝ ከመስዋእት ይበልጣል» (1ሳሙ. 15:22)! ጌታ መታዘዝህ እንጂ የከፈልከው የዋጋ አይነትና ብዛት አያረካውም!

ምዕራፍ ስምንት

በአብርሃም ጥሪ መብሰል
(ዘፍጥረት 23-25)

«ወራሹ ሕጻን ሆኖ ባለበት ዘመን ሁሉ፣ ምንም የሁሉ ጌታ ቢሆን ከቶ ከባሪያ አይለይም፣ ነገር ግን አባቱ እስከቀጠረለት ቀን ድረስ ከጠባቂዎችና ከመጋቢዎች በታች ነው» (ገላትያ 4፡1-2)።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ ከሕጻንነት ባህሪይ በመውጣት በአብርሃም ጥሪ መብሰል የግድ ነው። በዚህ እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል ለእኛ ባስተላለፈው ጥሪ የበሰለ ሰው ባህሪያቶች ምንድን ናቸው? ለዚህ አስፈላጊ ጥያቄ መልስ ለማግኘት የአብርሃምን ሕይወት የመጨረሻ ዘመን ታሪክ ያዘሉትን ምእራፎች እናጠናለን። ወደዚያ ጥናት ከመግባታችን በፊት ግን መብሰል የሚባለውን እውነት ለመንደርደሪያ ያህል በሁለት መልኩ ተመልክተን እንለፍ።

በመጀመሪያ ደረጃ አንድን ነገር ለማብሰል በእሳት እንለበልበዋለን ወይም ደግሞ እንቀቅለዋለን። በሌላ አባባል አንድ ነገር በሚገባ ለመብሰል በእሳት ላይ በቂ ጊዜ መቆየት አለበት። ይህ የአበሳሰል ሁኔታ የሚያሳየን በእግዚአብሔር ጥሪ ከምንበሰልባቸው መንገዶች አንደኛው በመከራና በአስቸጋሪ የልምምድ እሳት ውስጥ ተፈትኖ በማለፍ መሆኑን ነው። ለዚህ አይነቱ የአበሳሰል ሁኔታ ጠንቅ ሊሆኑ ከሚችሉት ሁኔታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ፈጽሞ ለእሳት ያለመጋለጥ። እንድንበስል የግድ በመከራ ማለፍ ያስፈልጋል። የክርስትናና የጥሪ ሕይወት ማለት የምኞት፣ የድሎትና ምንም ችግር የሌለበት ሕይወት ብቻ ነው ብለን ካሰብን ተሳስተናል።
- የሰብ ለብ ሁኔታ። አንዳንድ ጊዜ በሚገባ እሳቱ ሳይነካን ነው የምናልፈው። ይህም የሚሆነው ችግር ሲመጣ ወጣ፣ ሁሉ ደህና ሲሆን ደግሞ ገባ እያልን «ለብ ለብ» ብለን ስለምናልፍ የበሰለ ነገር አይታይብንም።
- የመቃጠል ዝንባሌ። ችግርና ፈተና ውስጣችንን እንዲጎዳውና ዘልቆ ገብቶ እንዲያቃጥለን ከፈቀድንለት ከመብሰል እናልፍና ወደማረር ደረጃ እንደርሳለን። መራራነትና ለዛ ቢስነት ከዚህ ሁኔታ ይመነጫሉ።

በሁለተኛ ደረጃ፣ የመብሰልን ሁኔታ ከፍሬ ጋር በማገናኘት መመልከት እንችላለን። አንድ ፍሬ ለመብሰል ከበቀለበት ዛፍ ሳይለይ ለበቂ ጊዜ ሲቆይ ይገባዋል። አንድ ፍሬ ከዛፉ ሳይለይና ከተለያዩ ከመብሰል ከሚቀጩ ሁኔታዎች ተጠብቆ ከቆየ መብሰሉ አይቀርም። ከዚህም እውነት የምናስተውለው፣ ከጠራን ከእግዚአብሔርና ከተጠራንበት ሁኔታ ሳንለይ በምንቆይበት ጊዜ በጥሪ የመብሰላችንን ጉዳይ እውንና ፈጣን እንደምናደርገው ነው። ለዚህ አይነቱ የአበሳሰል ሁኔታ ጠንቅ ሊሆኑ ከሚችሉት ሁኔታዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ከጠሪያችን ወይም ከጥሪያችን መለየት። ከጠራን ጌታ በተለየን ቁጥር የመብሰላችንን ሁኔታ እናራዝማለን። በሌላ ጎኑ ደግሞ በአንድ የጥሪ መስመር ካልጸናንና ስፍራን ከቀያየርን በፍጹም አንበስልም።
- ለጤና ቢስ ሰዎች መጋለጥ። እኛን ለመርዳትና ለመጥቀም ሳይሆን ለጥቅማቸው የሚጠቀሙን ሰዎች በስለን እንዳንቀጠፍና ለመልካም ነገር እንዳንውል ሊያደርጉን ይችላሉና ታላቅ ጥንቃቄ ያሻል።
- በጊዜው «ለመብል» እና ለጥቅም አለመዋል። በጥሪያችን በቆየንበት ዘመን ያህል ለጥቅም በጊዜው ካልዋልን ዘመናችን ያልፍና ወደ መበስበስ እናልፋለን። ሁሉ ነገር ጌታ ባቀደለት ጊዜ ሲሆን ያምራል።

እንግዲህ የአብርሃም ሕይወት ከላይ ከጠቀስናቸው ሁኔታዎች የተጠበቀ ሕይወት ነበር። አብርሃም በሕይወት ዘመኑ በተለያየ የፈተና እሳት አልፎና በስሎ የወጣ ሰው ነበር። በተጨማሪም፣ አብርሃም በነገር ሁሉ ከጠራው ከእግዚአብሔር ሳይለይ በስሎ የወጣ ሰው ነበር። ይህ በሚገባ በስሎ የወጣ

የእምነት አርበኛ ብለለቱ ከታየባቸው እውነቶች መካከል የሚከተሉት ይገኝ ብታል።

1. ለተፈጥሮአዊ ክስተቶች ሚዛናዊ ምላሽ መስጠት

«አብርሃምም ለሳራ ሊያዝንላትና ሊያለቅስላት ተነሳ»

- ዘፍጥረት 23:2

አብርሃም የእምነት አባታችን ነው። በእምነቱ የተመሰከረለትና ከዚያም የተነሳ የእግዚአብሔር ወዳጅ የተባለ ታላቅ ሰው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስመ ጥር የሆነ አብርሃም በሕይወት ዘመኑ ለሚደርሰው የሃዘንና የደስታ መፈራረቅ ተፈጥሮአዊ ምላሽ መስጠትን የተማረ ሰው ነበር። ይህም እውነት ለረጅም ጊዜ አብራው የኖረች ሚስቱ ሳራ በሞት ስትለየው ባሳየው ሁኔታ በግልጽ ይታያል። የእምነት ሰው መሆኑ ለሚስቱ እንዳያዝንላት አላገደውም። በእምነት ሽፋፍኖና ያላዘነ መስሎ ለማለፍ አልፈለገም። የእምነትንና የተፈጥሮ ሂደትን ግንኙነትና ልዩነት በሚገባ ያውቅ ነበር።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው የእምነት ሰው መሆን ማለት ከተፈጥሮ ውጪ መሆን ማለት እንዳልሆነ ያውቃል። በእግዚአብሔር ማመን ማለት እሱ ራሱ ከሰጠን የኃዘን፣ የደስታና የመሳሰሉት ስሜቶች ውጪ መኖር ማለት አይደለም። በእግዚአብሔር እውነት የበሰለ ሰው ለስጋ ኃጢአት አሳልፎ ከሚሰጥ ስሜት ራሱን እየጠበቀ ተፈጥሮአዊ ክስተቶች ለሚያመጡበት ሁኔታ ትክክለኛ ስሜትን መግለጽ የሚችል ሰው ነው።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው «መንፈሳዊ» ሰው መሆን ማለት «መንፈስ» መሆን ማለት እንዳልሆነ ያውቃል። አንዳንድ ጊዜ «በእምነት መርከብ» ስንወሰድና እንደባለ አእምሮ ማሰብ ሲሳነን፣ ችግር፣ መከራና የሕይወት ውጣ ውረድ በፍጹም የማይነካንና ሁል ጊዜ ከፍ ያለ ስፍራ ላይ ሆነን መመላለስ እንደሚገባን እናስባለን። ስለዚህም ያልሆንነውን ሆነን ለመገኘት ስንታገል አላስፈላጊ ውጥረት ውስጥ ራሳችንን እንጨምራለን።።።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው መንፈሳዊ መሆንና የእምነት ሰው መሆን ማለት ስሜት የለሽና ግድ የለሽ መሆን ማለት እንዳልሆነም ያውቃል። በአብርሃም ጥሪ የበሰልን ስንሆን፣ ምንም አይነት የእምነት ሰዎች ብንሆንም እንኳ በሰው ላይ የሚደርስ ተፈጥሮአዊ ሂደት ሁሉ እንደሚደርስብን በማወቅና በሚዛናዊነት እንመላለሳለን።

2. በሕብረተሰቡ መካከል ቀኝ እጅን የሚያሰጥ ምስክርነት መገንባት

«የኬጢ ልጆችም ለአብርሃም መለሱ፣ አሉትም፦ ጌታ ሆይ፣ ስማን፤ አንተ በእኛ መካከል ከእግዚአብሔር አለቃ ነህ»

- ዘፍጥረት 23:3-6

አብርሃም ብዙ ዘመን ከኖረ በኋላ ሣራን በሞት እንዳጣት እንመለከታለን። በዚያን ጊዜ ነበር ለእሷ መቀበሪያ ስፍራን በመፈለግ ወደለምኞት የተጠጋው። በዚህም ገዛው በሕብረተሰቡ መካከል ከነበረው ጤናማ ምስክርነት የተነሳ የፈለገውን ነገር ለማግኘት አላስቸገረውም ነበር። ቃሉ «የሰው አካሄድ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንደሆነ በእሱና በጠላቶቹ መካከል ሰንኳ ሰላምን ያደርጋል» (ምሳ. 16:7) እንደሚል አብርሃም በእምነት አርምጃው እግዚአብሔርን ደስ በማሰኘቱ ምክንያት በኖረበት ህብረተሰብ ውስጥ ተቀባይነቱ እጅግ የላቀ ነበር።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው የእግዚአብሔር ሰው መሆን ማለት ከሕብረተሰቡ መካከል ራስን ማግለል ማለት እንዳልሆነ በሚገባ ያውቃል። በክርስቶስ በመሆናችን ምክንያት ዓለም ልትጠላን እንደምትችል ቃሉ ቢነግረንም፣ ይህ ጥላቻ የፍርሃት ጥላቻ እንጂ የንቀት ጥላቻ እንዳልሆነ ልናውቅ ይገባናል። የአብርሃምን የጥሪ ሕይወት በሚገባ የሚኖር ሰው በሚኖርበት ሕብረተሰብ ውስጥ ታላቅ የሆነን ተጽእኖ እንደሚያመጣ እመን ነው።

የጥሪ ሰው ስለሆንክ ከጥሪዬና መንፈሳዊ ነው ብዬ ከማስበው ጉዳይ ውጪ ከሕብረተሰቡ ጋር አልገናኝም የሚለው ሃሳብ ያልበሰለ ሃሳብ ነው። የአብርሃም ጥሪ አሕዛብን የሚነካ፣ የሚባርክና፣ ለብዙዎች አባት የመሆን ጥሪ መሆኑን ሳንዘነጋ ማምጣት የምንችለውን ተጽእኖ ሁሉ በሕብረተሰባችን ውስጥ ለማምጣት ልንዘረጋ ይገባናል።

ተፈጥሮአዊው በሆነው በሰው አይን የማይታየው የጥሪያችን ሁኔታ የሚገለጠው በተፈጥሮ አይን በሚታየው በባህሪያችን ነውና በህብረተሰቡ መካከል በመልካም ባህሪ መገለጥ የግድ ይሆናል።

3. ነገርን ሁሉ በእምነት ዋጋ ከፍሎ ማግኘትን መለማመድ

«በእርሻው ዳር ያለችውን ድርብ ክፍል ያላትን ዋሻውን በሙሉ ዋጋ በመካከላችሁ ይሰጠኝ»

- ዘፍጥረት 23:9

አብርሃም በሕብረተሰቡ መካከል ከነበረው መልካም ምስክርነት የተነሳ ለቀብር የሚሆንን ስፍራ በነጻ እንዲወስድ ግብግ ሲቀርብለት እናነባለን። ይህንን ሊሰጠው ያለውን ቁራሽ መሬት በነጻ መቀበልን ሊችል እሱ ግን አልፈለገም ነበር። አብርሃም ለሚያገኘው ነገር ሁሉ ዋጋ ከፍሎ በማግኘት ለእግዚአብሔር ክብርን የመስጠት ምስጢር የገባው ሰው ነበር። አብርሃም ይህንን የገባውን ነገሮችን ዋጋ ከፍሎ የመውሰድ ምስጢር ለህዝቡ ሲገልጥ በትህትናና ዝቅ በማለት እንጂ በእግዚአብሔር ስም በመታበይ አልነበረም።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው እግዚአብሔርን የሚከተለው በእምነት መሆኑን ቢያውቅም፣ በላቡ ማደርንና በእምነት መስራትን የተለማመደ ሰው ነው። የእምነት ሰው መሆን ማለት ሰርቶ መባረክ እንጂ በድንግ የሚመጣን «በረከት» እንደ እግዚአብሔር ስጦታ እየቆጠሩ መኖር ማለት አይደለም። እምነት ማለት ስራ ማለት ነው። ማመንና መስራትን ልንለያያቸው የማንችላቸው እውነቶች ናቸው።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው በጌታ ፊት በመቅረብና ራእይንና ምሪትን በመቀበል «የእጆቹን ስራ ይባርክልኛል» በማለት ይወጣል። የእምነት ሰው መሆን ማለት በጸሎት ለስራ ጸጋን መቀበል ማለት ነው እንጂ በፍጹም ሳይሰሩ በጸሎት ብቻ ተአምራትን ከሰውና ከሰማይ መጠበቅ ማለት አይደለም። የበሰለ ሰው ያምናል፣ ይጸልያል፣ ይሰራል፣ ይቀበላላ፣ ለጌታም ክብርን ይሰጣል።

የእምነት ሰው መሆን ማለት ራስን መቻል እንጂ የሕብረተሰብ ሸክምና ጥገኛ መሆን ማለት አይደለም። በነጻ ወደ እጃችን የሚመጣልንን ነገር ቁጭ ብለን በመጠበቅ፣ «ጌታ ይህንን አደረገልኝ» ለማለት መዘጋጀት ጠላት ውጥመድ ውስጥ እንድንወድቅ የማድረግ አደገኛነት እንዳለው ግልጽ ነው።

4. በሚሰራው ስራ ሁሉ የሚባረክ

«አብርሃምም ሸመገለ በዘመኑም አረጀ፤ እግዚአብሔርም አብርሃምን በስራው ሁሉ ባረከው»

- ዘፍጥረት 24:1

አብርሃም ለሞት በቀረበበት ዘመን ስራው ሲመዘን የመጣው አምላካዊ ሪፖርት፡- «በስራው ሁሉ ተባረከ» የሚል ነበር። በግል ሕይወቱ፣ በቤተሰብ ህይወቱ፣ ከሕብረተሰቡ ጋር በነበረው ሕብረትና በማንኛውም ነገር አብርሃም የተባረከ ነበር። አብርሃም በሁሉ ነገር እንደተባረከ የተመሰከረለት ገና የበረከትን ጎዳና እንደጀመረና ጌታ እንደተናገረው አልነበረም። ያንን የጀመረውን ጉዞ ሲጨርስና ጌታም የተናገረውን ወርሶና አስመስክሮ ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ ሲደርስ ነበር የተመሰከረለት።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው በብዙ ልምምድ ያለፈና የሚያደርገውን የሚያውቅ ሰው ስለሆነ በሁሉ ነገር የተባረከ ሰው ነው። የአብርሃም ጥሪና በረከት በአንድ የሕይወት አቅጣጫችን ተባርከን በሌላኛው ግን እንድንረገም የሚያደርግ ጎዳና አይደለም። ለምሳሌ፣ አገልግሎት እየተባረከ ቤተሰብ እንዲያሽቆለቁል የጌታ ፈቃድ አይደለም። በእግዚአብሔር ቃል እውቀት እየተባረክን በተፈጥሮአዊው እውቀት ወደ ኋላ እንድንቀር የጌታ ሃሳብ አይደለም።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው የሚነካውን ነገር ሁሉ የሚነካው በስጦታው ብቻ ሳይሆን በባህሪውም ጭምር ስለሆነ ይባረክለታል። ስጦታ ስኬታማ የሚሆነው መልካም ባህሪይና ምስክርነት ሲኖረን ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ የሚያግዘንና ከተግባራችን ጀርባ ሆኖ ስኬትን የሚጨምርልን ስለመረጠንና ሊባርከን ስለወደደ ብቻ ሳይሆን ባህሪያችን ለእሱ ሲመቸውም ጭምር ነው።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው በአንድ ነገር ላይ ፍሬ እስኪያገኝና እግዚአብሔር የተናገረውን እስኪወርስ ድረስ በታማኝነት የሚቆይ ስለሆነ መባረኩ አይቀርም። በዚያም ጌታ ባሰማራው ስፍራ ሲቆይ በመስራትና በመተግበር ስለሚቆይ መባረኩ ጥርጥር የለውም። ጌታ ራሱን ያስገዛለትንና በዘመኑ ሁሉ የተከተለውን ሰው ላለመባረክ ያስቸግረዋል።

5. ለተተኪው ትውልድ መሰረታዊ መመሪያን ትቶ የሚያልፍ

«አብርሃምም ሎሌውን የቤቱን ሽማግሌ የከብቱን ሁሉ አዛዥ አለው፡- እጅህን ከጭኔ በታች አድርግ፣ እኔም አብሬ ከምኖራቸው ከከነዓን ሴቶች ልጆች ለልጄ ሚስት እንዳትወስድለት በሰማይና በምድር አምላክ

በእግዚአብሔር አምልሃለሁ፤ ነገር ግን ወደአገሬና ወደተወለድኩ ትሄዳለህ፣ ለልጄ ለይስሃቅም ሚስትን ትወስድለታለህ»

- ዘፍጥረት 24:2-67

አብርሃም ከመሞቱ በፊት ጌታ በገባለትን የመብዛት ቃል ኪዳን ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያመጣ በሚችል ዋነኛ ሁኔታ ላይ መመሪያን ሲሰጥ ይታያል። እግዚአብሔር የገባለት ኪዳን እንዳይሰናከል ልጁ ይስሐቅ ከሌሎች አማልክት ጋር ሊያስተዋውቁት ከሚችሉ ሴቶች ጋር እንዳይጋባ መጠንቀቅ ነበረበት። ይህንንም እውነት በግልጽ ሊያስተምርና ትእዛዝን ሊያስተላልፍ እናነባለን። ከመሞቱ በፊት በግልጽ አስተምሮና ትእዛዝን አስተላልፎ ያላሰፈው ነገር ሁሉ ነገ በዘሩ ላይ ታላቅ አሉታዊ ተጽእኖ እንደሚያስከትልበት እመን ነበር።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው ጌታ የሰጠውንና ያሳየው እውነት በግልጥነት የሚያስተምርና ዘላለማዊ መርሀን ለተተኪው ትውልድ አስተላልፎ የሚያልፍ ሰው ነው። የእሱ ዘመን ጊዜው ሲመጣ እንደሚያልፍና ከእሱ በኋላ የሚተካው ትውልድ የእሱን ምሪት እንደሚሻ ጠንቅቆ ማወቅና ያንንም ማድረግ ታላቅ መብሰል ነው። ስለዚህም በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው እሱ ሲያልፍ ለተተኪው ትውልድ ተጽእኖን ጥሎ የሚያልፍ ሰው ነው።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው ከሁሉ በፊት የግሉን ሕይወት ከሚያምንበት መርህ አንጻር ይቃኛል። ያንን የሚያደርግበት ምክንያት እሱ ያላመነበትንና ያልተለማመደውን እውነት ለሌላው ለማስተላለፍ መከራ ቢያደርግም እንኳ ያ እውነት ጉልበት እንደሌለው ስለሚያውቅ ነው። የመርህ ሰው ያመነበትንና የተለማመደውን እውነት የነገን ትውልድ በማየት ያስተምራል፣ ሁኔታዎችንም ሁሉ መስመር ያስይዛል እንጂ ለተተኪው ትውልድ የችግር ምንጭ የሚሆን መስመር ቀድዶ አያልፍም። ይህንንም እውነት ለመለማመድ እግዚአብሔር በሰጠው መንፈሳዊ መርህ ላይ ማመቻመች እንደማይገባው ያውቃል።

6. ቅርስን ለበታቹ አስተላልፎና መስመር አስይዞ የሚያልፍ

«አብርሃምም የነበረውን ሁሉ ለይስሃቅ ሰጠው»

- ዘፍጥረት 25:5

አብርሃም በሕይወቱ መጨረሻ ላይ የበሰለ ሰው ብቻ ሊያደርገው የሚችለውን አንድን ነገር አደረገ። የእሱ ዘመን ወደ መፈጸም እንደደረሰ በማስተዋል በዘመናት ደክሞ የገነባውንና ያፈራውን ሃብትና ንብረት ሁሉ ለልጁ ለይስሃቅ ሰጠው። እሱ አምኖበትና አስቦበት ለልጁ ያላስተላለፈው ነገር ነገ የጸብና የመከፋፈል ምንጭ እንደሚሆን በበሰለ አእምሮው ተገንዝቦ ይህንን አደረገ። ይህ ከራስ ወዳድነትና ከሃብት ፍቅር ነጻ የሆነ አርበኛ፣ የእሱ የሆነውን ሁሉ ጌታ የሰጠው ለተተኪው ትውልድ እንዲስተላልፍ እንደሆነ በሚገባ የበራለት ሰው ነበር።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው ጌታ የሰጠው የተጽእኖ ዘመን ወደ ማብቃቱ መቃረቡን የሚያውቅና በማስተዋል ማድረግ የሚገባውን ነገር የሚያውቅ ሰው ነው። እግዚአብሔር ለሁሉ ሰው በዘመኑ ተባርኮ፣ ጌታውን አስክብሮና እሱም ደስ ተሰኝቶ እንዲያልፍ ፈቃዱ ነው። ሆኖም የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚያገለግልበት ዘመን ሲያበቃ ደግሞ በእጁ ያለውን ሁሉ ለተተኪው ወራሽ ትውልድ በደስታ መስጠትን ሊማር ይገባዋል።

በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው ጌታ «ዘመንህ ነው» ብሎ እሱን አስነስቶት እንደነበረ፣ ሌላውንም በጊዜው እንደዚያ ሊያስነሳው እንደሚችል ስለሚያውቅ ሁኔታውን በደስታ የሚቀበል ሰው ነው እንጂ የሌላውን ታናሽነት የሚንቅ ሰው አይደለም። ይህ በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው ክብሩ ያለው ከኋላው ለተነሱ ሰዎች ሁሉን ነገር አሳልፎ በመስጠት እንጂ እስከ ሞት በመያዝ እንዳልሆነ ያውቃል። ስለዚህም ይህ በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው እሱ ካለፈ በኋላ አሁን በእጁ ያለው ነገር ወደ ማን ሊሄድ እንደሚችል ስለማያውቅና ሊነሳ የሚችለውን ማለቂያ የሌለው ችግር አስቀድሞ ስለሚያይ አስተካክሎ እንጂ አዝረክርኮ አያልፍም።

7. ሁሉን ጨርሶና እድሜ ጠግቦ እንደሚያልፍ በማወቅ የተደላደለ

«አብርሃምም ነፍሱን ሰጠ፣ በመልካም ሽምግልናም ሞተ፣ ሸመገለም፣ ብዙ ዘመንም ጠገበ፣ ወደወገኖቹም ተከማቸ»

- ዘፍጥረት 25:8

አብርሃም የሞተው በእጭር ተቀጭቶ ላይሆን እድሜን ጠግቦ ነበር። እግዚአብሔር ለሰጠው ጥሪ ተገቢውን ምላሽ ሰጥቶ፣ በፊቱ የተዘረጋለትን

መንገድ ተከትሎና፣ የተገባለትን ኪዳን በአይኑ አይቶ በመልካም ሽምግልና ነበር የሞተው። በጠራው በእግዚአብሔር ላይ እምነቱን ስለጣለና መንገዱንም ለመከተል በፍጹም ልቡ ስለሄደ ከተወሰነለት እድሜ በፊት እንደማይቀጭና ሩጫውን ሳይጨርስ እንደማይገታ እሙን ነበር። የጠራው ጌታ የሰጠው ምሪት ወደ እውነታ እስኪመጣ ድረስ የሚሰፈልገውን እድሜ ያህል መኖር ነበረበት።

የአብርሃምን ጥሪ የተቀበለና በልቡ ቅንነትን የተከተለ ሰው በጠራው በእምላኩ የተደላደለ ሰው ነው። ስለዚህም፣ ከሞት ፍርሃትና ከጭንገፋ አሰራር በላይ ነው። የአባቱን የአብርሃምን እምነት ስለተጎናጸፈ፣ ይህ የእምነት ሰው በሕይወቱ የተነገረለትን ሳያይ ለሞትና ለጭንገፋ መንፈስ አይንበረከክም። ጀምሮ አለመጨረስ፣ በሆነ ባልሆነው መሰናከል፣ ከመንገድ መገታት፣ ሞትና መቀጨት በእሱም ሆነ እሱ በነካው ነገር ሁሉ ላይ ስልጣን እንዳናራቸው ለአንዱና ለመጨረሻ ጊዜ የቆረጠ ሰው ነው።

የጨዋው የእምነት ሰው የአብርሃም ጥሪ የበራለት ወገን ክብሩን ጠብቆ የቆየ፣ እግዚአብሔርን መምሰልና መንገዱንም መከተል ማትረፊያ እንደሆነ የገባው ሰው ስለሆነ ሽምግልናውና የመጨረሻው አመቶቹ መልካም ናቸው። በመጨረሻው ዘመኑ በፍጹም ተጥሎ አይቀርም። በአብርሃም ጥሪ የበሰለ ሰው የመጨረሻዎቹን አመታቱን ሁኔታ የሚወስኑት የመጀመሪያዎቹ አመታት ውሳኔዎቹና እርምጃዎቹ እንደሆኑ ስለሚያውቅ መንገዱን በእግዚአብሔር ፊት ያስተካከለ ሰው ነው፤ ስለዚህም በበረከት ጀምሮ በበረከት ይፈጽማል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

የአብርሃም ዘር ነህ ወይስ የሎጥ? (ዘፍጥረት 12)

«የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ስራ ባደረጋችሁ ነበር» (ዮሐ. 8:39-40)።

ሎጥ የሚለው ስም ቀጥተኛ ትርጓሜው «ስውር ወይም ምስጢር የተሞላ» ማለት ነው። እንደሚታወቀው ሁሉ በብሉይ ኪዳን ዘመን የአንድ ሰው ስምና የኑሮ አቅጣጫ የተራራቁ አይደሉም። ለዚህም ነው እግዚአብሔር የሰዎችን ታሪክና አቅጣጫ መቀየር ሲፈልግ፣ ወደ አብርሃም መጥቶ እንዳደረገው፣ በቅድሚያ ስማቸውን የሚለውጠው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ የስም ለውጥ ማለት የኑሮ፣ የአቅጣጫና የፍጻሜ ለውጥ ማለት ነው።

ሎጥም እንደ ስሙ የሆነ ኑሮን የኖረ ይመስላል። ሎጥ ማለት አቋመ፣ አመለካከቱ፣ ራእዩና ማንነቱ ያልተለየ ሰው ነበረ። ከየት ተነስቶ ወደ የት ሊሄድ እንደፈለገ፣ እንኳን ለሌላው ለእርሱ ለራሱ እንኳን ግልጽ አልነበረም። አብርሃም ከኖረው ኑሮና ከተጓዘው ጉዞ አንጻር ሲታይ የሎጥ ጎዳና ለበረከት የማይመች፣ ጠማማና ቅጡ የማይታወቅ እንደሆነ ማስተዋል ከባድ አይደለም። ለዚህም ነው የሎጥን ኑሮ እየኖርን የአብርሃምን በረከት መውረስ የማይቻለው።

ቃሉ ይህንን እውነት ሲያጸናልን እንዲህ ይለናል፦ «የአብርሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ስራ ባደረጋችሁ ነበር» (ዮሐ. 8:39-40)። ትርጓሜ፦ «የአብርሃምን በረከት መውረስ ከፈለጋችሁ እንደ ብርሃን መመላለስ አለባችሁ»። የአብርሃምን መንገድ መከተል፣ የአብርሃምን ህይወት መኖርና የአብርሃምን እምነት መለማመድ የአብርሃምን በረከት እንድንወርስ መንገዱን ይከፍትልናል።

«ክርስቶስን በማመናችን የአብርሃም ልጆች ነን፣ ስለዚህም በረከቱን እንወርሳለን» በሚለው ስህተት የማይወጣለት አባባል ብቻ ተይዘን ኑሮአችን ግን እንደሎጥ ከሆነ ውርስ የሕልም እንጀራ ነው። የአብርሃምን ህይወት ካላከበርነውና ካልኖርነው የአብርሃም በረከት ከእኛ እንደሚወሰድ ቃሉ ያሳስበናል፡- «አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና፡- ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሳለት እግዚአብሔር ይችላል» (ማቴ. 3:9)። «እላችኋለሁ፣ ብዙዎች ከምስራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሃቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግስተ ሰማያት ይቀመጣሉ፤ የመንግስት ልጆች ግን በውጪ ወዳለው ጨለማ ይጣላሉ» (ማቴ. 8:11)።

የአብርሃም ልጆች ሆነን በጠላት እስራት ውስጥም ልንቀመጥ እንደምንችል ቃሉ ያስታውሰናል፡- «ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአስራ ስምንት አመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እስራት ልትፈታ አይገባምን» (ሉቃ. 13:16)? አርነትና ነጻነት የእኔ ነው ብለን የአብርሃምን አምላክ አምነን ካልተጠጋን ጠላት የአብርሃም ልጅ ነው ብሎ እንደማይተወን ልናስታውስ ያስፈልጋል።

አብርሃም የተለያዩ ልጆች እንዳሉትም ቃሉ ያመላክተናል፡- «አንዱ ከባሪያይቱ አንዱም ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደነበሩት ተጽፎአልና» (ገላ. 4:22)። በሚቀጥለው ምእራፋችን እንደምንመለከተው የአብርሃም ልጅ ሆነን የባሪያ ወይም የእስራት ልጅ ልንሆን እንችላለን።

አንባቢዬ ሁሉ እንዲያስተውል የምመኘውን ከላይ የጠቀስኩትን እውነት ማጉላት እፈልጋለሁ። የሎጥን ሕይወት እየኖርን የአብርሃምን በረከት መውረስ በፍጹም የማይቻል ጉዳይ ነው። የአብርሃምና የሎጥ መንገድ ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ የራቀ ነው። ስለዚህም፣ ምናልባት አካሄዳችን በረከት ከራቀው ከሎጥ ጋር የሚመሳሰል ከሆነና የውስጣችን ምኞት ግን የአብርሃምን በረከት መውረስ ከሆነ የአቅጣጫ ለውጥ ማድረግ የግድ ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው በአብርሃምና በሎጥ መካከል ያለውን መሰረታዊ ልዩነቶች ለማወቅ የስነ-መለኮት ትምህርት ምሁራን መሆን የለብንም። በግልጽ ተጽፎአል! ማድረግ የሚገባን ይህ ነው፡- ማንበብ፣ ለመገንዘብ ልቦናን መክፈትና ለተገለጠልን እውነት የመታዘዝን እርምጃ መውሰድ! እንደ አብርሃም ለመበርታት፣ ከሎጥ ድካም ነጻ መውጣት አስፈላጊ ነው። እንደ አብርሃም

ለመባረክ ከሎጥ እርግማን መዋጀት የግድ ነው። እንደ አብርሃም ለመውረስ ከወረሰን ከሎጥ የሕይወት ዘይቤ መገላገል አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

በሚከተሉት ገጾች ውስጥ የምንመለከታቸውን የሎጥን አስከፊ ባህሪያቶች በማስተዋል ልቦናችንን ወደ አብርሃም አምላክ ወደ እግዚአብሔር እንድንመልስና ከበረከቱ ተካፋዮች እንድንሆን አንባቢዬን አበረታታለሁ። የአብርሃምን በረከት እንዳንወርስ የሚያደርጉን የሎጥ ባህሪያት ምንድን ናቸው?

1. በሌሎች ብርታትና የተስፋ ቃል ተከልሎ መኖር

«አብራምም እግዚአብሔር እንደ ነገረው ሄደ፣ ሎጥም ከእርሱ ጋር ሄደ»

- ዘፍጥረት 12:4

«አብራምም ከግብጽ ወጣ፣ እርሱና ሚስቱ ለእርሱም የነበረውም ሁሉ ሎጥም ከእርሱ ጋር ወደ አዜብ ወጡ»

- ዘፍጥረት 13:1

ሎጥ በአብርሃም የተስፋ ቃል ተከልሎ ተመላለሰ፤ አብርሃም ግን በግሉ የተሰጠውን «ተስፋ ይዞ አመነ» (ሮሜ 4:18)።

ከታሪኩ መነሻ ጀምሮ ሎጥ ከአብርሃም ጋር ተጣብቆ የሚገባና የሚወጣ ሰው ነበር እንጂ የራሱ ብርታት፣ ዓላማና መርህ የነበረው ሰው ያልነበረ ሰው ነው። ሎጥ በአብርሃም ብርታትና የተስፋ ቃል ተከልሎ በረከትን ለመውረስ የቆረጠ ሰው ነበር። ስለዚህም አብርሃም ሲወጣ ይወጣ፣ አብርሃም ሲገባ ደግሞ ይገባ ነበር። አብርሃም በሰፈረበት ስፍራ ሎጥ አይጠፋም ነበር። በመካከላቸው አለመስማማት እስኪከሰት ድረስ ከአብርሃም ጋር ተጣብቆ ነበር። ከአብርሃም እስኪለይ ድረስ ሎጥ ሰላም ነበር። ከአብርሃም ከተለየ በኋላ ነበር በችግርና በመከራ መመታት የጀመረው።

እግዚአብሔርን በግላችን ፈልገን ሳናገኘውና በሕይወታችን ያለውን ዓላማ ሳናውቅ፣ ዘወትር በሌሎች በእሱ መንገድ በበረቱ ሰዎች ጥላ ስር ጥገኛ ሆነን በመኖር የአብርሃምን በረከት እንወርሳለን ማለት የማይሆን ነው። ከልመናና ከጥገኝነት ያላለፈ ሕይወት ይዘንና የእግዚአብሔርን የመባረክ ጉልበት ሳንለማመድ የአብርሃምን በረከት መጠባበቅ ጊዜን ማባከን ነው። የአብርሃም በረከት የሚመጣው በእግዚአብሔር በማመንና እርሱንም በፍጹም ልብ በመከተል ነው።

2. የቀረበለትን በረከት መጠቀም አለመቻል

«ከአብራም ጋር የሄደው ሎጥ ደግሞ የላምና የበግ መንጋ ድንኳንም ነበረው»

- ዘፍጥረት 13:5

ሎጥ ብዙ ኃብት ነበረው፣ መጨረሻው ግን ከንቱ ነበር፤ አብርሃም ግን ከነበረው መንጋና ሃብት ያለፈ በረከት ውስጥ የገባ ሰው ነበር፦ «በዚችም የእግር ጫማ ስንኳ የሚያህል ርስት አልሰጠውም፤ ነገር ግን ልጅ ሳይኖረው ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጎ ይሰጠው ዘንድ ተስፋ ሰጠው» (የሐዋ. 7:5)።

ሎጥ ምንም እንኳ በግሉ ከእግዚአብሔር ተቀበልኩት የሚለው የተስፋ ቃልም ሆነ በረከት ባይኖረውም፣ ከአብርሃም ጋር በመሆኑ ምክንያት ተባርኮ ነበር። ያንን በረከት ግን አያያዙን አላወቀበትም ነበር። ይህ የሚያሳየን እግዚአብሔር በግሉ ለሎጥ የሰጠው የተስፋ ቃልም ሆነ የውርስ ኪዳን ባይኖረውም እንኳ በአብርሃም ምክንያት የገባውን ሌሎችን የመባረክ ኪዳን በሎጥ ሕይወት ለመፈጸም መፈለጉን ነው። ሎጥ ግን ይህንን እውነት ያስተዋለና የተጠቀመበት አይመስልም።

እግዚአብሔር በእጃችን ያስገባውን በረኩት፣ የገባልንን የተስፋ ቃልና በፊታችን ያስቀመጠውን እድል ተጠቅመን ወደሚቀጥለው ደረጃ ማደግ ካልቻልን የምስኪኖች ሁሉ ምስኪኖች ነን። እግዚአብሔር ማንኛውንም የበረኩት እድል በእጃችን የሚያስቀጣው ሊባርከንና ካሰንበት አውጥቶ ልንገባበት ወደሚገባን ስፍራ ሊወስደን ነው። ይህንን እውነት ተገንዝበን በእጃችን የገባውን በረከት መጠቀም ካልቻልን ግን የአብርሃም በረከት በሙላት ወደ እኛ ይመጣል ማለት የማይሞላ ተስፋ ነው።

3. መልካም መስሎ በሚታይ ሁኔታ መታለል

«ሎጥም አይኑን አነሳ፣ በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውንም አገር ሁሉ ውኃ የሞላበት መሆኑን አየ . . . በዮርዳኖስ ዙሪያ ያለውን አገር ሁሉ መረጠ»

- ዘፍጥረት 13:10-11

ሎጥ አይኖቹን አንስቶ መልካም ወደ መሰለው ሄደ፣ በዚያም ሰፈረ፤ አብርሃም ግን ለጊዜው የማይመስለውን ሁኔታ «በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ» (ሮሜ 4:19)።

አብርሃም ለሎጥ ወደ ፈለገበትና ወደ መረጠው መንገድ እንዲሄድ ምርጫን ሲሰጠው፣ ሎጥ ውስጡን አድምጦና አምላኩን አማክሮ ሳይሆን ለአይኑ ያማረውን ነበር የመረጠው። ይህ የሆነበት ምክንያት፣ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ ሎጥ የዓላማ መልህቅ ያልነበረውና ወደቀናውና በረከት አገኝበታለሁ ብሎ ወዳሰበበት አቅጣጫ የሚቀዝፍ ሰው በመሆኑ ነው። ሎጥ በሚያየውና በሚሰማው የሚነዳና በቀላሉ የሚታለል ሰው ነበር። ምርጫን ሲመርጥ መለኮታዊውን ሃሳብ አድምጦ ሳይሆን በአይኑ አይቶና መልካም የሚመስለውንና ያማረውን መርጦ ነበር የመመላለሰው፣ በዚህም አካሄዱ ከሰረ እንጂ አላተረፈም።

ከሎጥ ሕይወት እንደምንማረው በውስጣችን ከተተከለው ጤናማ መርህ ወይም ከመለኮታዊ ምሪት አንጻር ሳይሆን ለአይናችን ስላማረንና ለስሜታችን ጥሩ ስለመሰለን ብቻ ተነሳስቶ አንድን ውሳኔ መወሰን አደገኛ ጉዳይ ነው። ለአይን የሚያምርና ለስሜት የተመቸ ብዙ አሳሳች ነገር የበዛባት አለም ውስጥ እንኖራለን። እነዚህ የስሜት ሕዋሳት በውሳኔአችን ላይ ተጽእኖ ማምጣት ከጀመሩና እኛም መታዘዝ ከጀመርን ከተወሰነልን የአብርሃም በረከት እንደምንወጣ እሙን ነው። የአብርሃም መንገድ የእምነት መንገድ ነውና።

4. ጤና ቢስ ሰዎች ሊያመጡበት የሚችሉትን ክፉ ተጽእኖ አለመገንዘብ

«ሎጥም በአገሩ ሜዳ ባሉት ከተሞች ተቀመጠ፣ እስከ ሰዶምም ድረስ ድንኳኑን አዘዋወረ። የሰዶም ሰዎች ግን ክፉዎችና በእግዚአብሔር ፊት እጅግ ኃጢአተኞች ነበሩ»

- ዘፍጥረት 13:12-13

ሎጥ ከአመጸኞች መካከል የኖረ ሰው ነበር፤ አብርሃም ግን «ከአገርህና ከዘመዶችህም ወጥተህ ወደማሳይህ ወደማንኛውም ምድር ና» (የሐዋ. 7:3) ሊባል የታዘዘ ሰው ነበር።

ሎጥ ከክፉዎችና ለርኩሰት ራሳቸውን ከሰጡ ሰዎች ጋር ድንኳኑን ሲተክልና ተዳብሎ ሊኖር ምን አይነት አደገኛ ተጽእኖ ሊያድርበት እንደሚችል ያልገባው ሰው ነበር፣ አብርሃም ግን እንኳን ከክፉዎች አይደለም ከሚወዳቸውና ለበረከት ሊሆኑለት ከሚችሉ ቤተሰቦቹ እንኳን ተለይ ሲባል ካልተለየ ሊመጣበት የሚችለውን ቀውስ ስለሚያውቅ ፈጥኖ በእምነት የታዘዘ ሰው ነበር።

ሎጥ ከክፉዎች ጋር ሲኖር ሳለ ጻድቅ ነፍሱን ያስጨንቅ እንደነበር ቅዱስ ጴጥሮስ በግልጽ ያስቀመጠው እውነት ነው (2ጴጥ. 2:7)። ሎጥ ጤና ቢስ ሰዎች በሕይወቱ ሊያስከትሉት የሚችሉትን ክፉ ተጽእኖ በፍጹም ያልተመለከተ ሰው ነበር። ነፍሱ እየተጨነቀችና ግራ ተጋብቶ ሳለ እንኳን አሁንም ድንኳኑን በሰዶም የተከለ ሰው ነበር።

ብዙ ጊዜአችንን አብረን የምናሳልፋቸው ሰዎች በእኛ ላይ ብዙ ተጽእኖ አላቸው። መልካሞቹ ለመልካም ነገር፣ ክፉዎቹ ደግሞ ለክፉ! ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን ባህሪይ እንደሚያጠፋ ቃሉ ያስታውሰናል (1ቆሮ15:33)። የአብርሃምን በረከት ለመውረስ ከአብርሃም ልጆች ጋር መዳበል የግድ ነው።

5. ለሌሎች መንፈሳዊ እርምጃ እንቅፋት መሆን

«ሎጥ ከተለየው በኋላም እግዚአብሔርም አብራምን አለው»

- ዘፍጥረት 13:14

ሎጥ እንኳን ለራሱ በረከትን አግኝቶ ለሌሎች ሊተርፍ፣ እንደውም ለአብርሃም እንቅፋት የነበረ ሰው ነበር፣ ስለ አብርሃም ግን ቃሉ ሲመሰክር እርሱ እንደተባረከ «እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም ጋር ይባረካሉ» (ገላ. 3:9)።

ሎጥ እስኪለየው ድረስ የእግዚአብሔር ድምጽ ወደ አብርሃም አልመጣም ነበር። ሎጥ እንደተለየው ግን አብርሃም ከእግዚአብሔር ለመስማት የተከፈተ ሰማይ ነበረው። ይህ እውነት እንደሚጠቁመን የሎጥ በአጠገቡ መሆን ለአብርሃም የበረከት ምንጭ ሳይሆን እንቅፋት እንደሆነበት ነው። አብርሃም ከሎጥ ጋር በነበረበት ጊዜ ብዙ የጸብ ሁኔታዎችም እንደነበሩ ግልጽ ነው (ዘፍ. 13:6)። ስለዚህም አብርሃም ከእግዚአብሔር ለመስማትም ሆነ ሰላም ለማግኘት ከሎጥ መለየት ነበረበት።

በእኛ ምክንያት የሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ሲቆምና ሲደርቅ እንደማየት ሊያሳስበን የሚገባ ጉዳይ የለም። የአብርሃም በረከት በሕይወታችን በመላት ሲመጣና የእርሱን በረከት ወደ መውረሻው መስመር ውስጥ ስንገባ በእኛ ምክንያት ሰዎች ይባረካሉ እንጂ አይረገሙም። ከእምነት የሆኑት የእምነት አባት ከሆነው ከአብርሃም ጋር እንደሚባረኩ እኛም የበረከትና የመልካም ነገር ፈር ቀዳጆች እንሆናለን። ከእኛ ጋር የሆነ እንዲያርፍ፣ እንዲባረክና፣ ወደተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ይህ የአብርሃም የበረከት መንገድ ነው።

6. ለምርኮ ቀላል የሆነ ህይወት

«እንዲህ ሁሉ በሲዳም ሸለቆ በእነርሱ ላይ ለሰልፍ ወጡ . . . በሰዶም ይኖር የነበረውን የአብራምን የወንድም ልጅ ሎጥን ደግሞ ከብቱንም ወስደው ሄዱ»

- ዘፍጥረት 14:8-12

ሎጥ ወደ እርሱ አቅጣጫ የመጣው የመጀመሪያው ጠላት የማረከው ደካማ ሰው ነበር፣ ስለ አብርሃም ቃሉ እንደሚመሰክር፦ «የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አስራት» (ዕብ. 7:1) ያወጣ ሰውና ለምርኮ የበረታ ሰው ነበር።

ሎጥ የመጣ ጠላት በቀላሉ ማርኮት የሚሄድ ሰው ነበር። ሎጥ ብዙ ሃብትና ብዙ ባሪያዎች ቢኖሩትም እንኳ አብርሃም እንዳደረገ በቤቱ የተወለዱትን ሰዎች ለሰልፍ አላሰለጠነም ነበር። እርሱ የሰልፍ ሰው ስላልነበረ እነሱም እንደዚያ ነበሩ። ሰልፈኛ ሆኖ በቤቱ ያሉትንም እንደዚያ ለማድረግ ሊያነሳሳው የሚገባ ዋነኛ ነገር የነበረው የኃብት ብዛት ነበር። ይህንን በረከቱን የሚፈልጉ ጠላቶች በዙሪያው እንዳሉ እሙን ሆኖ ሳለ እርሱ ግን ለጠላት ተጋልጦ የተቀመጠ የማያስተውል ሰው ነበር።

አንዳንድ ጊዜ እኛን ለመማረክ የመጣ መንፈስ ሁሉ በቀላሉ የሚያጠቃን ሰዎች ሆነን እንገኛለን። ይህም ዝንባሌ እጅግ አስጊና በእኛ ላይ ያለውን የአብርሃምን በረከት የመውረስ ጸጋ የሚገፍፍ ጉዳይ ነው። የተጠራነው ተባርከን ትውልድንም ለመባረክ ሆኖ ሳለ፣ ወደ እኛ የመጣ ተራ መንፈስ ሁሉ ለማይረባ ነገር ማርኮ ሲያስቀረን ያሳዝናል። የወሬው፣ የዝሙቱ፣ ዓለምን የመውደዱና የመሳሰሉት የመንደር መናፍስት መልእክተኞች ብዙዎችን ከአብርሃም በረከት አጉድለዋቸው ሲታይ ልብን ያሳዝናል። የአብርሃም መንገድ እንዲህ አይደለም።

7. ዘወትር በሰው ብርታት አርነት መውጣት

«አብራምም ወንድሙ እንደተማረከ በሰማ ጊዜ . . . ፍለጋቸውን ተከትሎ እስከዳን ድረስ ሄደ . . . ከብቱንም ሁሉ አስመለሰ፣ ደግሞም ወንድሙን ሎጥንና ከብቶቹን ሴቶችንና ሕዝቡን ደግሞ መለሰ»

- ዘፍጥረት 14:14-16

ሎጥ ከተማረከ በኋላ ከዚያ ምርኮ ለመውጣት የግድ የሌላ ሰው ድጋፍ አስፈልጎት ነበር። አብርሃም ግን «በእምነት በረታ እንጂ ባለማመን ምክንያት» ወደምርኮ ሲወርድ አይታይም (ሮሜ 4:20)።

ሎጥ ከገባበት ምርኮ አብርሃም እስኪያወጣው ድረስ የመውጫ ምንም መንገድ አልነበረውም። ቀድሞውኑ ከጠላት የሚጠበቅበት እቅድ ያልነበረው ሎጥ፣ ከተማረከ በኋላ አብርሃም መጥቶ ባያስጥለው ኖሮ መጨረሻና ፍጻሜው ምን ይመስል ነበር? ከአብርሃም ጋር በመጠጋቱ ምክንያት የመጣለትን በረከት የመጠበቂያና፣ ምናልባትም ምርኮ ቢመጣ እንኳ ከዚያ ሁኔታ ነጻ የሚወጣበት መንፈሱም ሆነ እቅዱ አልነበረውም።

የአብርሃምን በረከት ለመውረስ የተጠራ ወገን ይህንን በረከት ሊሰርቅ በሚመጣ ጠላት ላይ የመነሳት ብርታትና ጸጋ ከሌለው ተስፋ ቢስና መጨረሻው የማያምር ሆኖ እንደሚቀር ጥርጥር የሌለው እውነት ነው። በላያችን ላይ መጥቶ ቀድሞ የነበረንን «የአብርሃም» መንፈስ በወሰደብን ጠላት ላይ ለመነሳት እኛው ካልወሰንንና ካልተዋጋን፣ በሌላ ሰው ብርታት ነጻ ብንወጣ እንኳ ተመልሰን ወደ ምርኮ መውረዳችን የጊዜ ጉዳይ ነው። አብርሃም የጠላትን ፍለጋ ተከትሎ እንደመታቸው በእኛም ይህ የአርበኝነት መንፈስ ካላንሰራራ ዘወትር ከምርኮ አናልፍም።

8. በእምነት ከማሸነፍ ይልቅ በእንግድነት መንፈስ መኖር

«ይህ ሰው በእንግድነት ለመኖር መጣ፣ ፍርዱንም ይፈርድ ዘንድ ይፈልጋል»

- ዘፍጥረት 19:1-11

ሎጥ ምንም እንኳን በሰዶም ለረጅም ጊዜ የተቀመጠ ሰው ቢሆን፣ ከእንግድነት መንፈስ አልወጣም ነበር፣ «አብርሃም (ግን) . . . እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ» (ዕብ. 11:8-9)።

የሰዶም ህዝብ ወደ እርሱ የመጡትን እንግዶቹን ሊደፍሩበት በመጡ ጊዜ ያንን ክፉ ነገር የመቋቋም ማንነትና እምነት ስላላዳበረ ሁኔታውን ከመቃወም ይልቅ ልጆቹን ነበር አሳልፎ ለመስጠት ያቀረበው። አብርሃምም ቢሆን በእንግድነት አገር የተቀመጠ ሰው ነበር። ነገር ግን በእንግድነት ሃገር በተቀመጠበት ዘመን በእምነት እንደተቀመጠ ቃሉ መስክሮለታል። እንደ

መጻተኛ ሲቀመጥ ሳለ በዚያ ባለው መንፈስ ላይ በእምነት ተነሳ እንጂ ባለማመን አልተገዛም።

እንደ አብርሃም ልጆች በምንኖርበት ስፍራ ሁሉ በእኛ ያለውን መልካም ነገር የሚቃወም የዚህ አለም ገገር እንደሚኖር ልንጠባበቀው የሚገባን እውነት ነው። ሆኖም ይህ መንፈስ እንደ እንግዳ እንዲገዛንና እንዲያንበረክከን የጌታ ፈቃድ አይደለም። መጻተኝነት እንዲሰማንና አንገታችንን አቀርቅረን እንድንመላለስ በሚፈልገን ጠላት ላይ በመነሳት በጌታ ያሰንን እምነት የምናሳይበትን መንፈስ መቀበል አለብን። በቤት ውስጥ፣ በስራ ቦታ፣ በትምህርት ቤትም ሆነ በተለያዩ ስፍራዎች፣ «አካባቢው የእኔ ነው» የሚል ድምጽን የሚያስተጋባውን ጠላት ሳንፈራ በጌታ ስም የገኘነትን መንፈስ በውስጣችን በጸሎት መቀስቀስ አለብን።

9. በተራ ነገርና በፈዘዝ መሞላት

«ሎጥም ወጣ፣ ልጆቹን ለሚያገቡት ለአማቾቹም ነገራቸው፣ አሳቸውም፦ ተነሱ፣ ከዚህ ስፍራ ውጡ፣ እግዚአብሔር ይህችን ከተማ ያጠፋታልና። ለአማቾቹ ግን የሚያፈዝባቸው መሰላቸው»

- ዘፍጥረት 19:14

ሎጥ በሰዶም በኖረበት ዘመን በስራ ያስመሰከረው ቁም ነገረኝነት እንዳልነበረውና የሚናገረው ነገር እንደፈዘ ይቆጠር እንደነበረ፣ «አባታችን አብርሃም . . . እምነት ከስራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ በስራም እምነት እንደተፈጸመ ትመለከታለህን» (ያዕ. 2:21-22)?

እግዚአብሔር ሰዶምን ሊያጠፋ በሚያስፈራ ሁኔታ መጥቶ ሳለ፣ በዚህ አስደንጋጭ መንፈስ ውስጥ ሆኖ ነበር ለአማቾቹ መልእክቱን ያስተላለፈላቸው። አማቾቹ ሎጥን በቁም ነገር መውሰድ እስኪሳናቸው ድረስ ከዚህ በፊት መልካም ነገር እንዳላገኙበት እናያለን። እግዚአብሔር ሰዶምን ሊያጠፋት ነው የሚለውን መልእክቱን እንደወትሮው ፈዝ ቆጠሩበት። ሎጥ ምን አይነት ቁም ነገር የለሽ ሰው ቢሆን ነው? ምን ቢላቸው ይሆን መልእክቱን የሚያምኑት? አንድ ነገር ግልጽ ነው፦ ሎጥን እንደ ፈዘኛ የቆጠሩት ከአነጋገር ዘይቤው ወይም ከአቀራረቡ ሳይሆን ቀድሞ ካዳበረው ምስክርነቱ ነው።

ከአብርሃም የወራሽነት ሕይወት ወደ ሎጥ የተወራሽነት ሕይወት እንድንዘቅጥ ከሚያደርጉን አደገኛ የህይወት ዘይቤዎች መካከል አንዱ የፈዘኝነት

ሕይወት ነው። በሕይወታችን ስርተን የምናውቀው ቁም ነገር ከሌለና ዘወትር ፈዘኞች ከሆንን የምንወርስ ሳንሆን የምንወረስ እንሆናለን። በእግዚአብሔር ስም የሰራናቸው ቁም ነገሮች ከሌሉንና ከዚህ በፊት በጸሎታችንና ጌታን ሰምተን በመታዘዛችን ካልታወቅን በድንገት ተነስተን እንዲህና እንዲያ ብንል ማን ነው የሚያምነን? እኛም ተወርሰን ሌሎችንም እናስወርሳለን እንጂ!

10. ቀላሉንና ዋጋ የሚያስከፍለውን መምረጥ

«መላእክት ሎጥን፦ . . . እንዳትጠፋም ወደተራራው ጠፍተህ አምልጥ . . . ሎጥም አላቸው፦ . . . ወደተራራ ሸሽቼ አመልጥ ዘንድ አልችልም፤ እነሆ ይህች ከተማ ወደ አርስዋ ሸሽቶ ለማምለጥ ቅርብ ናት፥ አርስዋም ትንሽ ናት፤ ነፍሴን ለማዳን ወደ አርስዋ ሸሽቼ ላምልጥ፤ አርስዋ ትንሽ ከተማ አይደለችምን?»

- ዘፍጥረት 19:15-20

ሎጥ የታዘዘውንና ከባድ የሚመስለውን ነገር በእሺታ መንፈስ ከማድረግ ይልቅ ቀላል ሆኖ የሚታየውን ነበር የሚያደርገው፤ ስለ አብርሃም በእምነት ታዛዥ የመሆን ባህሪይ ቃሉ ሲመሰክርለት፣ «አብርሃም . . . በእምነት ታዘዘ» (ዕብ. 11:8) ይለናል።

ሎጥ ወደ ተራራ ሸሽ ሲባል ወደ ቀላሏ መንደር ሸሸ። (ወደ ተራራ ሄዶ ቢሆን ኖሮ ሚስቱ ትድን ይሆን)? ያንን ምርጫ የወሰደበት ምክንያቱ ግልጽ ነው፦ ወደ ተራራው በመሸሽ ዋጋ የሚያስከፍልን ምርጫ ከመምረጥ ይልቅ ቀላል መስሎ የሚታየውን ወደ መንደር የመሸሽ ምርጫ መውሰድ ለእርሱ የሚያጓጓ ነበር። ሎጥ ትእግስት የሚጠይቅን ምርጫ የሚደፍር አይመስልም። አብርሃም ግን «ከታገሰ በኋላ ተስፋውን አገኘ» (ዕብ. 6:15) የሚል ምስክርነት የተሰጠው ታላቅ ሰው ነው።

ይህ መርህ በግልጽ እንደሚያሳየን፣ ቀላል ምርጫ ስንመርጥ ፍጻሜአችንም ቀላል፣ ተራ ውሳኔን ስንወስን ኑሮአችንም እንዲሁ ተራ፣ ርካሹንና ዝቅ ያለውን ስንመርጥ ህይወታችንም ርካሽና ዝቅ ያለ እንደሚሆን ጥርጥር የለውም። የአንድን ሰው ነገ የሚወስነው የዛሬ ውሳኔው ነው። የትናንት ውሳኔአችንን ፍሬ ዛሬ እየበላን እንደሆን፣ የዛሬው ውሳኔአችን ደግሞ ነገ የምንበላውን ፍሬ ያበቅልልናል። ስለዚህ የአብርሃምን በረከት ወራሽ ሆኖ

ለመገኘት እንደ እሱ ከባዱን ምርጫ ለመምረጥ በእምነት የምንታዘዝ ልንሆን የግድ ነው።

11. ስለእኛ ሳይሆን ስለሌሎች ሲባል መዳን

«እግዚአብሔርም እነዚያን የአገር ከተሞች ባጠፋ ጊዜ አብርሃምን አሰበው፤ ሎጥ ተቀምጦባት የነበረውንም ከተማ ባጠፋ ጊዜ ከዚያ ጥፋት መካከል ሎጥን አወጣው»

- ዘፍጥረት 19:29

ሎጥን እግዚአብሔር ያዳነበት ምክንያት አንድና አንድ ነው፤ አብርሃምን ስላሰበ! የአብርሃምን ህይወት በንጽጽር ስንመለከት ግን በእሱ ምክንያት ሰዎች ሌሎች ተቀባይነት እንደሚያገኙና እንደሚድኑ ነው፦ «እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ» (ገላ 3:7)።

እግዚአብሔር ሎጥን ለማዳን የሚያበቃውን መልካምነት በሎጥ ውስጥ ስላላገኘ እሱን ለማዳን ሌላ ማላጅና ጻድቅ ሰው ማግኘት ነበረበት፣ እሱም አብርሃም ነው። በሌላ አባባል ጌታ ሎጥን ያዳነው የአብርሃምን ጽድቅና ምልጃ ስላሰበ እንጂ ሎጥን እንዲያስብ የሚያደርገውን መልካም ነገር ስላገኘ አልነበረም።

ጌታ እንዲያስበንና እንዲጎበኘን የሚያደርገውን መልካም ነገር ከእኛ ካላገኘ ወደ አብርሃም በረከት የመግባታችን ጉዳይ አጠራጣሪ ይሆናል። ቃሉ፣ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች ናቸው እንደሚል፣ በውስጣችን እግዚአብሔር እንዲታደገን የሚያደርግ እምነት እንዲገኝብንና ድነን ሌሎችን የማዳን ተስፋዎች እንድንሆን ልንተጋ ይገባል። አለዚያ ዘወትር ሰዎች ካልጸለዩልን፣ ካልማለዱልንና፣ እጃቸውን ጭነው ዘይትን ካልቀቡን በስተቀር በእስራት የምንመላለስ ሰዎች እንሆናለን። ይህ በሚሆንበት ጊዜ እኳን የአብርሃምን በረከት ልንወርስ ቀርቶ፣ እኛ ራሳችን በጠላት ከመወረስ የማምለጣችን ጉዳይ አጠራጣሪ ይሆናል።

12. ለሚቀጥለው ትውልድ ራእይ የለሽ ህይወት

«ታላቂቱም (የሎጥ ልጅ) ታናሺቱን አለቻት፦ . . . አባታችንንም የወይን ጠጅ እናጠጣውና ከእርሱ ጋር እንተኛ፣ ከአባታችንም ዘር እናስቀር»

- ዘፍጥረት 19:30-38

ሎጥ ከጥፋት ከዳነ በኋላ ለሚቀጥለው ትውልድ በማሰብ ዘርን ለራሱ የማስቀረት ጉዳይ ሲያሳስበው አይታይም፣ ስለ አብርሃም ግን፣ «ለብዙ አሕዛብ አባት አደረግሁህ» (ሮሜ 4:17) ሲል ቃሉ ይመሰክርለታል።

ሎጥ ትውልድን ለመተካት ያሰበ ሰው አልነበረም። ይልቁንስ በጊዜአዊ ደስታ በመወሰድ ሲሰክርና ይህንና ያንን ሲያደርግ ነበር ዘመኑን በማሳለፍ ላይ የነበረው። ምንም እንኳ በስህተት ጎዳና ቢሄዱም፣ ልጆቹ ከእሱ የተሻለ ሲያስቡና ዘርን ለአባታቸው የማስቀረት ጉዳይ ሲያሳስባቸው ይታያሉ። የአብርሃም በረከት ወደ ትውልድ የሚያልፍና ዘርን ሁሉ የሚነካ በረከት ስለሆነ በሎጥ ሁኔታ የአብርሃምን በረከት መውረስ የማይቻል ነው።

ራእያችን፣ ተግባራችን፣ ውሳኔአችንና የዛሬው እርምጃችን መጪውን ትውልድ ያካተተ ካልሆነ ከአብርሃም የበረከት መንፈስ ሊያስወጣን እንደሚችል በማሰብ እርማትን ልንወስድ ይገባል። የአብርሃም በረከት ከግል ደስታና ለጊዜው ረክቶ ከመኖር ያለፈና ወደ ፊት ለሚተካው ትውልድ በረከትንና ቅርስን ትቶ የማለፍ ሁኔታ ያካተተ በመሆኑ የሕይወታችንን መርህ ከዚህ አንጻር ልንቃኝ ይገባናል። ለዛሬ ከመኖርና ከማደር አልፈን፣ ነገንና የሚቀጥለውን ትውልድ በአይታችን ውስጥ አካትተን በእቅድ መመላለስ የአብርሃም የበረከት መንገድ ነው።

ምዕራፍ አስር

የባሪያ ልጅ ነህ ወይስ የጨዋ?
(ዘፍጥረት 12)

«አንዱ ከባሪያይቱ አንዱም ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደነበሩት ተጽፏልና» (ገላ. 4:22)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ክባርነት ሕይወት ነጻ የመውጫውን መንገድ በሚያሳይበት በገላትያ መልእክቱ ውስጥ ከአብርሃም ጉልበት የወጡትን የሁለት ትውልድ ሁኔታ በማነጻጸር የእነዚህን ትውልድ ልዩነቶችና በእምነት በኩል የአብርሃምን በረከት የመውረሻውን መንገድ ይጠቁመናል። የአብርሃም መንገድ የእምነት መንገድ እንጂ የህግ መንገድ አይደለም። የሚጸድቁ፣ አብርሃም እግዚአብሔርን አምኖ ጽድቅም ሆኖ እንደተቆጠረለት እንዲሁ ማድረግ አለባቸው። የአብርሃምን በረከት ለመውረስ አብርሃም ከተሳሳተው ስህተት መቆጠብና እግዚአብሔር አብርሃምን በወሰደው ጎዳና መራመድ የግድ ነው።

አብርሃም ሁለት ልጆች ነበሩት፡- አንድ ክባሪያ፣ ማለትም በእስራት ካለች፣ አንድ ደግሞ ከጨዋ፣ ማለትም በተስፋ ቃል ነጻነት ውስጥ ካለች። የእነዚህ ዘሮች ልዩነት እጅግ አስገራሚና የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት ያለው ነው። እነዚህ ሁለት ልጆች የራሳቸው የሆነ ባህሪ አላቸው። ቃል ኪዳን የሌላትና መጽሐፉም «ባሪያ» የሚላት አጋር ስትሆን፣ አብርሃም የስጋውን ውጥን በመከተል ከእሷ እስማኤልን አገኘ። እስማኤል የባሪያ ልጅ ስለሆነ የአብርሃምን በረከት እንዲወርስ አልተፈቀደለትም። ቃል ኪዳኑን አብራ የተቀበለችውና መጽሐፉም ጨዋ የሚላት ሳራ ስትሆን፣ አብርሃም ተስፋውን ከጠበቀ በኋላ ከእሷ ይስሃቅን አገኘ። ይስሃቅ የጨዋ ወይም የተስፋ ቃል ልጅ ስለ ነበረ የአብርሃምን በረከት እንዲወርስ ተብሎለታል።

የባሪያ ልጅ የሆነው እስማኤል ያለው በእስራት ሲሆን፤ የጨዋ ልጅ የሆነው ይስሃቅ ደግሞ ያለው በነጻነት ነው። የባሪያውን ልጅ በእስራት እንዲሆን ያደረገው ካለተስፋ ቃል በመወለዱና የስጋ ስራ ስለታከለበት ሲሆን፤ የጨዋውን ልጅ ጨዋ ያሰኘው ደግሞ በእግዚአብሔር ተስፋ በመወለድና የመንፈስ ቅዱስ ሃሳብ ስላለበት ነው።

በዚሁ በገላትያ መልእክቱ ውስጥ ጳውሎስ፤ እኛን አማኞችን በክርስቶስ በማመናችን ምክንያት የአብርሃም ልጆች መሆናችንን ያስታውሰናል፦ «እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም ልጆች እንደሆኑ ይህንን እወቁ (ገላ. 3:7)። ጳውሎስ ይህንን ንጽጽር ያመጣበት ዋነኛ ምክንያቱ በዚያ ዘመን አብርሃም ሁለት አይነት ልጆች እንደ ነበሩት ሁሉ፤ በአሁን ዘመን ያለንስ የአብርሃም ልጆች በሁለት የመከፈላችንን ሁኔታ ለማሳየት ነው። በአንድ ጎኑ፤ ራሳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመስጠትና የተስፋ ቃሉን በመጠበቅ በጨዋነት የምንመላለስ ስንኖር፤ በሌላ ጎኑ ደግሞ የስጋችንን መንገድ የምንከተልና ከተስፋ ቃሉ የተቃረነ የባርነት ህይወት የምንመራ ሰዎች እንገኛለን።

እነዚህ የአብርሃም ልጆች በዚያ መልክ የመወለዳቸውን ሁኔታ እነሱ አልወሰኑትም ነበር። ዛሬ ግን እኛ የጨዋነትን (የነጻነት) ወይም የባርነትን (የእስራት) መንገድ የመከተልና በሕይወታችን የሚመጣውን ውጤት የመወሰን መብቱን፤ ምርጫውንና መገለጡን ጌታ ሰጥቶናል። ስለዚህ፤ በአንድ ጎኑ በእምነት በመሆናችን ምክንያት ለእኛ የቀረበውን የአብርሃምን በረከት የመቀበልም ሆነ በእሱ በመመላለስ የመባረክ መብቱ ሲኖረን፤ በሌላ ጎኑ ደግሞ የስጋ ስራ ውስጥ በመግባትና ከተስፋው ውጪ በመመላለስ የባሪያ ልጅ የመሆን ምርጫው የእኛ ነው።

ከዚህ በታች የምንመለከተው የጨዋ ወይም የተስፋ ልጅ ከመሆን ይልቅ የባሪያ ወይም የስጋ ፍሬ ወደ መሆን ስናዘቅጥ የሚታዩብንን ምልክቶች ነው። ከተስፋ ቃሉ ውጪ መኖርና በባርነት መንፈስ መመታት የሚከተሉትን ምልክቶች እንዲገለጹብን ያደርጋል።

1. በቀንበር መገዛትን መውደድ

«እናንተ ከሕግ በታች ልትኖሩ የምትወዱ»

- ገላትያ 4:21

ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች በባርነት ለመኖር የመምረጣቸውን ሁኔታ ለማረም፤ ባርነትን በሕግ በታች ከመኖር ጋር አነጻጽሮ ነው የገለጠላቸው። ከሕግ በታች መኖር ማለት በባርነት መኖር ማለት ነው። አብርሃምን የእምነት አባት ያሰኘውና የተስፋ ቃሉን እንዲወርስ ያደረገው ከሕግ በታች መኖሩ ሳይሆን አምኖ ጽድቅን ማግኘቱና የተቀበለውን የተስፋ ቃል መቀበሉ ነው። ሕግ በቀንበር ገዝቶ እንድንታዘዘው ያስገድዳል፤ እምነት ግን የተስፋ ቃል ተቀብለን በዚያ ነጻነት እንድንመላለስ ይፈታናል።

የባርነት መንፈስ የተጠናወተው ሰው የነጻነት መንገድ አይስማማውም። በባርነት ቀንበር መገዛትን፤ መልፋትንና መድከምን ይወዳል። በነጻ የሚቀርብለትን ነገር እንደርካሽ ስለሚቆጥረው አያከብረውም። በእርሱ የባርነት አመለካከት ምንም ነገር ለማግኘት መድከም፤ መልፋትና በቀንበር መገዛት አለበት። በነጻ የመጣን ነገር ዋጋ እንደሌለው ይቆጥረዋል። ስለዚህም በክርስቶስ ያገኘውን ነጻ ሕይወት እንኳን አክብሮ መመላለስ ይሳነዋል።

የባርነት መንፈስ የመታው ሰው አንድን ስርአት የሚያከብረው፤ ካላከበረ ቅጣት ስለሚከተለው እንጂ ስርአትን የማክበር የጨዋ መንፈስ ስላደረበት አይደለም። ስለዚህ፤ ያንን በፊቱ ያለውን ስርአት በማያከብርበት ጊዜ የግድ መቀጣት፤ መመታትና ልክ መግባት አለበት። አለዚያ ለስርአት አይገዛም። በአጭሩ፤ ይህ አይነቱ የባርነት መንፈስ የለከፈው ሰው አንድን ነገር የሚያከብረው ቅጣት ስላለው እንጂ የመታዘዝና ስርአት የመያዝ እውነቱ ስለገባው አይደለም።

የባርነት መንፈስ የያዘው ሰው በጌታ ቤት አይጸናም። በጌታ ቤት በጨዋ መንፈስ የመኖርን ምስጢር ስላልተገነዘበ፤ በየምክንያቱ ወጣ ገባ ይላል። ወደ ጌታ ቤት የሚመለሰው አንድ ችግር ሲደርስበት ብቻ ነው። አደጋ፤ ክስረት፤ ወይም ደግሞ የተለያዩ የጠላት አለራሮች ሲያገኙት ሮጦ በንስሃ ይመለሳል። ሁሉ ሰላም ሲሆንለት ደግሞ እንደገና ይጠፋል። ይህ የባርነት መንፈስ ነው። አስራት አሰጣጡ፤ ጸሎቱና ማንኛውም እርምጃው ከሚያደረስበት ክፉ ነገር ጋር እንጂ ከመርህ ጋር የተያያዘ አይደለም።

የባርነት ዝንባሌ ያለው ሰው በማስፈራራት፤ በዛቻና በቁጣ ካልሆነ በስተቀር ስርአት አይይዝም። ነጻ ተለቅቆ እንዲመላለስ እድል ሲሰጠው ባርነት የለመደው ውስጡ ያንን የነጻነት መንገድ በፍጹም አይገነዘበውም። ለእርሱ ነጻ መለቀቅ ማለት እንደ ልብ መሆን ማለት ነው። ስለዚህ በየጊዜው የቁጥጥር፤

የህግና የቁጣ ቀንበር በላዩ ላይ ካልተጫነ በስተቀር በመከበሩ፣ በመወደዱና በመታመኑ ምክንያት ሊለቀቅ መስመር የመሳት ዝንባሌ አለው።

2. በተስፋ ቃል ሳይሆን በስጋ መመላለስ

«ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደስጋ ተወልዷል፣ የጨዋይቱ ግን በተስፋው ቃል ተወልዷል»

- ገላትያ 4:23

ሐዋርያው ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች አሁንም ሊያስገነዝባቸው የወደደው፡- በስጋ መመላለስና ስጋዊ መንገድን መከተል የባርነት ምልክት ነው። እውነተኛ ነጻነትና የአብርሃምን በረከት የመውረሻው መንገድ የተስፋ ቃል መቀበልና በዚያ የተስፋ ቃል መሰረት ጌታን መጠበቅ፣ ማመንና ስር መስደድ እንጂ የልብን ምኞት በስጋ ጥረት ለማምጣት መታገል አይደለም። የስጋን ሃሳብና ምኞት ማስተናገድ በስጋ መመላለስን ሲያተርፍ፣ የተስፋ ቃል ማመንና ማሰላሰል በመንፈስ መመላለስን ያተርፍልናል።

የባርነት መንፈስ የመታው ሰው የተስፋ ቃልን ሳይሆን የስጋ ስሌትን ይከተላል። የእግዚአብሔር ሃሳብ ምንድን ነው? ጌታ ምን እንዳደርግ ፈልጓል? አሁን የማስበውና የማደርገው ነገር ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሃሳብ ጋር ይስማማል ወይ? እነዚህና እነዚህን የመሰሉ ጥያቄዎች በባርነት መንፈስ የተመታ ሰው የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች አይደሉም። በስጋው ሃሳብና ምኞት ከመሞላቱ የተነሳ ማታ ሲያውጠነጥን ያደረውን ጠዋት ሊተገብር ይሮጣል እንጂ ጌታን ሲያማክር አይታይም።

የባርነት መንፈስ የተጫነው ሰው ጌታን በማመንና በመስማት እሱን ብቻ ከመታዘዝ ይልቅ ሁኔታዎችን ከብዙ ነገሮች ጋር በማገናኘት የስጋውን መፍትሄ መፈለግ ይቀናዋል። የጌታን ፊት ፈልጎና እግዚአብሔርን ጠብቆ ነገርን በጊዜው ማግኘት የሚባለው ሃሳብ በስጋዊነት ለተሞላው አእምሮው በፍጹም የማይመችና የማይገባ ጉዳይ ነው። ስለዚህም ከሰዎች ጋር ሲታገል፣ ሲጣላና ሲጋጭ ይታያል። ሰው ሊያደርግበት ከሚችለው ክፋት የጌታ ደግነት እንደሚበልጥ በፍጹም አልገባውም።

የባርነት መንፈስ ያጠቃው ሰው የሚያልፍበትን ሁኔታ ዘወትር ከሰው ጋር ነው የሚያገናኘው። ሁል ጊዜ በሰዎች እንደተጠቃ፣ እንደተበዘበዘና ሰዎች ለጥቅማቸው ተጠቅመው እንደጣሉት በመቁጠር ሲቆስል፣ ሲጎዳና ሲያወራ

ይገኛል። የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ከማንኛውም ሁኔታ በላይ ሊያደርገው እንደሚችል በፍጹም አልገባውም። በአሁን ጊዜ ያለበትን ሕይወት እግዚአብሔር ለወደፊቱ በረከት ሊያዘጋጀው እያሳለፈው እንደሆነ ስላልገባው ዘወትር የሰዎች ሰለባ እንደሆነ ይሰማዋል።

የባርነት መንፈስ የቀጠቀጠው ሰው የሚያውቀው የውጊያ ስልት የስጋ ብቻ ነው። ሆነብኝና ደረሰብኝ ላለው ሁኔታ የሚሰጠው ምላሽ ሰዎችን ማማት፣ ስም ማጥፋት፣ መቧደን፣ ማኩረፍና በሰዎች መንገድ ላይ እንቅፋትን ማስቀመጥ ነው። በመንፈስ ስለማይመላለስና ተስፋ ቃሉን ማመንና በተነገረለት የትንቢት ቃል መሰረት በጸሎት መጋደል ሊያመጣለት የሚችለውን ድል ስለማያውቅ ሌሎችን በመጣል የሚበልጥ፣ ሰዎችን ስላሳመነ በር የሚከፈትለት፣ ስለታገለ የሚያሸንፍ ይመስለዋል።

3. ፍሬአችን ሁሉ ለባርነት መሆን

«ከደብረ ሲና የሆነችው አንዲቱ ለባርነት ልጆችን ትወልዳለች፣ እርሷም አጋር ናት»

- ገላትያ 4:24

ሐዋርያው ጳውሎስ የገላትያ ሰዎች እንዲገነዘቡለት የተመኘው ተጨማሪ ጉዳይ ነበር። ከአጋር የተወለደ ሁሉ የእግዚአብሔርን በረከት በአቋራጭ መንገድና በስጋ ስሌት ለማምጣት በተደረገ ጥረት ስለተወለደ መጨረሻው ባርነት ነው። በስጋ የተወለደው እስማኤል የነጻነት መንፈስ የሆነውን የእግዚአብሔርን መንፈስ አስተናግዶ ስላልተወለደ፣ የባርነትን መንፈስ ይዞ ነው ወደ መኖር የመጣው። ስለዚህም ከእርግማን፣ ከዝቅተኝነት መንፈስና በባርነት ከመገዛት አያመልጥም።

ከባርነት መንፈስ ነጻ ካልወጣን ለፍተንና ደክመን የምናፈራው ፍሬ ሁሉ ለባርነት ከመሰጠት አያመልጥም። በተፈጥሮአዊው ኑሮአችንም ሆነ በመንፈሳዊው ጉዞአችን የምንወልዳቸው ልጆች በባርነት መንፈስ የተመቱ ይሆናሉ። በእኛ የሌለውን ለልጆቻችን ማካፈልና ማውረስ አንችልምና፣ እኛ ባሪያዎች ከሆንን በእኛ ስር የሚያድጉ ሁሉ ከዚያ ከባርነት መንፈስ እንደማያመልጡ እሙን ነው። ዘሩ ከተበላሸ ፍሬውም እንዲሁ ከመበላሸት አያመልጥምና።

በባርነት መንፈስ ስር የወደቀ ሰው በንግድ ቢሰማራ ንግዱ ከሌሎች እንግዶቹ በታች፣ ራእይ ቢኖረው ራእዩ አናሳ፣ ስራ ቢኖረው ዘወትር በክፉዎች ስር የሚገዛ ከመሆን አያመልጥም። በላያችን ላይ ያለው የባርነት መንፈስና አመለካከት ለሌሎች ከመገዛት፣ የበታች ሆኖ ከመኖርና ዘወትር ከመታገል እንድናልፍ በፍጹም አይፈቅድልንም። ከእንደዚህ አይነቱ አዙሪት ለመውጣት የግድ ወደ ተስፋ ቃሉ አሰራርና መንፈስ ውስጥ መዝለቅና መግባት አለብን።

የባርነት መንፈስ የገደበው ሰው የሚያፈልቃቸው ሃሳቦች፣ ራእዮችና እቅዶች ሁሉ ዝቅተኛ ሆኖ ላለመታየት፣ ላለመበለጥና የበላይ ሆኖ ለመገኘት የመታገል ዝንባሌ ያላቸው ናቸው እንጂ ከጌታ የተቀበሉትን የተስፋ ቃል ወደ ፍጻሜ ለማምጣት ትኩረት ያላቸው አይደሉም። በባርነት መንፈስ ከተመታና በዝቅተኝነት መንፈስ ከተቀጠቀጠ አመጣጥ ስለሚመጣ ትግሉ ሁሉ ያንን ሆኖ ላለመታየት እንጂ እግዚአብሔር ሁን ያለውን ሆኖ ለመገኘት አይደለም።

ከባርነት መንፈስ ካልወጣንና የተስፋ ቃልን ወደ መቀበልና ወደ መታዘዝ ህይወት ውስጥ ካልገባን ከእኛ የተሻለ ሁኔታ ውስጥ ያሉት ሰዎች ጋር ለመድረስ እነሱን ጎትተን መጣል ያለብን ይመስለናል። የመበለጥ፣ የመጣል፣ የመገፋት፣ የመገለልና ከቁጥር ያለመግባት መንፈስ የሚያጠቃን በላያችን ላይ ከነገሰው የባርነት መንፈስ የተነሳ እንጂ እንደዚያ ስለሆንን አይደለም። መፍትሄው ለእግዚአብሔር ራስን ሙሉ ለሙሉ በመስጠት በተስፋ ቃል መመላለስ እንደሆነ ሊበራልን ይገባል።

4. መሆን ሳይሆን መምሰል

«ይህችም አጋር በአረብ ምድር ያለችው ደብረ ሲና ናት፣ አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌምን ትመስላለች፣ ከልጆችዋ ጋር በባርነት ናትና»

- ገላትያ 4:25

ሐዋርያው ጳውሎስ በሌላ መልኩ ለገላትያ ሰዎች የባርነትንና የጨዋነትን ልዩነት ሊያሳያቸው ይጥራል። የስጋ ሃሳብ ማስፈጸሚያ የሆነችው አጋር ምንም እንኳ ኢየሩሳሌምን የመምሰል ገጽታ ቢኖራትም ኢየሩሳሌም ግን አይደለችም። መምሰልን ትመስላለች፣ መሆንን ግን አይደለችም። የጨዋይቱንና በተስፋ ቃል የታጀበችውን ኢየሩሳሌም ትመስላለች፣ መልክንና ስምን ይዛለች፣

ማንነቷ ሲመረመርና ሲታይ ግን ከውጭ ስትታይ የምትመስለውን አይደለችም።

የባርነት መንፈስ ሲመታን፣ ውስጣችን በባርነት መንፈስ ተይዞ ውጫችንን ግን ነጻ እንደወጣ አስመስለን ወደ መመላለስ እንመጣለን። በውስጣችን እውነተኛ ነጻነት እንደሌለን፣ የመታሰር፣ የመገደብና የመመታት ስሜት እንዳጠቃን እናውቃለን። ነገር ግን በውጪአችን ደህና መስሎ የመታየት ጤናማ መሳይ ገጽታዎችንና የድል ቋንቋዎችን በማዳበር እውነተኛ ማንነታችንን በመሸፋፈን ዘመንን እንፈጃለን። እንመስላለን እንጂ አይደለንም፣ እንናገረዋለን እንጂ አልሆንነውም!

የባርነት መንፈስ ውስጣችንን አፍኖ ሲይዘን፣ ተግባሩ አለን፣ የምንተገብረውን ሆኖ መገኘት ግን ይሳነናል። በውጪ ስንታይ መልኩ አለን መስለን የምንታየውን ግን ሆነን እንዳልተገኘን እናውቀዋለን። መንፈሳዊውን ቋንቋ እናውቀዋለን፣ በመናገር የገለጽነውን እውነት ግን እየኖርነው እንዳልሆነ ውስጣችን ጠንቅቆ ያውቀዋል። እንግዲህ፣ ይህ መስሎ የመታየት ሁኔታ፣ ሆኖ በመገኘት ካልተደገፈ ዘመንን ሁሉ በባርነት መንፈስ ተገዝቶ ከመኖር ያለፈ ታሪክ አይኖረንም።

የባርነትና የዝቅተኝነት መንፈስ ሲታገለን፣ በአንድ ጎኑ ስለችሎታችን፣ ስለልምምዳችንና ስለክንውናችን በመናገርና ያልሆንነውን ነገር እንደሆንን አድርገን ለማቅረብ እንጥራለን። በሌላ ጎኑ ደግሞ የሌሎችን አለመቻልና ዝቅተኛነት በማውራት የበላይነትን ስፍራ ለማግኘት ከመጣጣር ያለፈ ጥረትና ታሪክ አይኖረንም። ይህ ሁሉ የሚሆነው እውነተኛ ማንነት ስለሌለንና ያንንም በማንነት ያልተደገፈ ተግባር መሸፈኛውን መንገድ ለማግኘት በምናደርገው የማያቋርጥ ጥረት ነው።

የባርነት መንፈስ ሲወርሰን፣ ራሳችንን የምንቀበለው ስለቻልንና ስለተሳካልን እንጂ ስለማንነታችን አይደለም። ስለዚህ፣ ሰዎችም እኛን የሚቀበሉን ስለማንነታችን ሳይሆን ስለተሳካልንና ስላከናወንን እንደሆነ ይመስለንና እንስታለን። በዚህ አመለካከት ስንነዳ፣ ሌሎችንም የምንቀበላቸው ስለማንነታቸው መሆኑ ይቀርና ስላላቸው፣ ስለቻሉ ወይም ደግሞ ስላከናወኑ ይሆናል። ይህ በማንነት ላይ ሳይሆን በሁኔታ ላይ የተመሰረተው የተቀባይነት ዝንባሌ ዘወትር አስመሳይነትን እንድናዳብር ካለማቋረጥ ይገፋፋናል።

የባርነት መንፈስ ሲበረታብን፣ ራሳችንንና ሌሎችን ወደመናቅ እናዘቅጣለን። ሆነን ለመታየት የጣርንለት ማንነቱ እንደሌለን ስለምናውቅ ራሳችንን እጅግ አድርገን እንንቀዋለን። የውጪው ታሪካችን ከግል እውነተኛ ማንነታችን ጋር የተራራቀ በመሆኑ ስውር ንቀት በራሳችን ላይ እናዳብራለን። ራሳችን በውጭ አስመስለን በውስጥ ግን ሌላ ሆነን ስለኖርን፣ በሌላውም ሰው የምናየውን መልካም ነገር ማመን ይሳነናል፣ እንደእኛ ያስመሰለ ስለሚመስለን። ስለዚህም ሌላውን እንንቃለን።

5. አሳዳጅነትና ተቃዋሚነት

«ነገር ግን እንደ ስጋ የተወለደው እንደ መንፈስ የተወለደውን በዚያን ጊዜ አንዳሳደደው ዛሬም እንዲሁ ነው»

- ገላትያ 4:29

ጳውሎስ በባሪያውና በጨዋው አብርሃም ልጆች መካከል ያለውን ንጽጽር በመቀጠል፣ የባሪያው ወይም እንደ ስጋ ሃሳብ የተወለደው የጨዋውን ወይም በመንፈስ ሃሳብ የተወለደውን እንደማይመቸው ያሳየናል። አብርሃም በስጋው ውጥንና በራሱ ስሌት የወለደው ልጅ በጌታው አቅድና በመንፈስ የተሰፋ ቃል መሰረት የወለደውን ልጅ ካለማቋረጥ ያሳድደዋል። ወራሽነቱን፣ የእግዚአብሔር ሃሳብ በእርሱ ላይ መሆኑንና መመረጡን ስለማይወድ ቀድሞውም እንደሚያደርግ አሁንም ያሳድደዋል።

ይህ ባህሪይ ዛሬም ሌሎች ሰዎች የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተከትለው በሚባረኩበት ጊዜ የማይወዱትን የስጋ ስራ የሞላባቸውን ሰዎች ያመላክተናል። በመንፈስ መመላለስን ትተን የስጋን ስራ በምናስተናግድበት ጊዜ ሰዎች ሲባረኩ ማየት አንወድም። በውስጣችን ያጠቃን የባርነት መንፈስ የመበለጥን ድምጽ ያሰማናል፦ እነርሱ የበለጸጉት ሰርቀው እንደሆነ፣ እነሱ ከፍ ያሉት እኛን ደፍቀው እንደሆነ፣ እንዲሁም ደግሞ እነሱ የተባረኩት በእኛ ላይ ተረማምደው እንደሆነ ድምጽን ያሰማናል።

«እንደ ስጋ» የሆነ ሰው ባለራእዮችን፣ ጌታ አዲስ ነገር ያስተዋወቃቸውንና ተቀባይነትንም የሰጣቸውን ሰዎች መቃወም ይወድዳል። እንዲህ አይነት ስጋዊ አመለካከት የሰፈረባቸው የባርነት ልጆች አንድን ባለራእይ ሲደግፉ አይታዩም፣ የሚቃወሙት ባለራእይ ግን ብዙ ነው። ምናልባት አንድ ጊዜ አንድን ባለራእይ የሚደግፉ ሆነው ከተገኙ ብቸኛ ዓላማቸው በሌላኛው ላይ

ያላቸውን ተቃውሞ ለማሳየት እንጂ ራእይና የመንፈስ ሃሳብ ገብቶአቸው አይደለም።

እንደ ስጋ የሚመላለሱ ሰዎች ዘወትር ስለ አንድ ሰው የሚናገሩት ጤና ቢስ ነገር አያጡም። ሰዎች ላይ ያለው ጎዶሎው ብቻ ነው የሚታያቸው። እንዲህ አይነት በስጋዊነት የተመሩ አሳዛኝ ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ስርአት አይገዙም። የክርስቶስ አካል የሆነችውን ይህችን የአለም ብቸኛ ተስፋ የሚገለጥባትን ቤተ ክርስቲያንን አይደግፉም። እንደውም ሲቃወሟት፣ ሲያወሩባትና ሲያፈርሷት ይታያሉ። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለው የመንፈስ ሃሳብ አይስማማቸውምና።

ከመንፈስ ሃሳብ የራቁና በስጋቸው ሃሳብ የተሞሉ ሰዎች አብረው ከሚያሳልፉቸው ሌሎች ሰዎች ጋር ያላቸው ጓደኝነት ሁሉ የተመሰረተው የተቃውሞን ነገር በመወያየት ነው። በአንድነት ሆነው የሚቃወሙት ሰው ሲኖራቸው የአሸናፊነት ስሜትንና ስጋዊ እርካታን ያገኛሉ። በመንፈስ ተመላልሶ ሊገኝ የሚችለውን እርካታና ድል ስላልተለማመዱት ብቸኛ የሚያገኙት እርካታና ድል በሌሎች ላይ በመቧደንና በማመጽ፣ እነሱንም በማፍረስ ነው። «ኃይለኞች» እና ታላላቅ ቃላትን የለመዱ ናቸው።

6. በአንድ ስፍራ አለመጽናት

«ነገር ግን መጽሐፍ ምን ይላል? የባሪያይቱ ልጅ ከጨዋይቱ ልጅ ጋር አይወርስምና ባሪያይቱን ከልጅዋ ጋር አውጣት»

- ገላትያ 4:30

በዚህ የባሪያይቱንና የጨዋይቱን ልጆች ልዩነት በሚገልጽበት በመጨረሻው ሃሳብ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የባሪያይሩ ልጅ ላይ ያለውን አንድ አደገኛ እርግማን በግልጽ ያሳየናል። እንደ ስጋ ሃሳብ የተወለደው የባሪያይቱ ልጅ በአንድ ስፍራ መጽናት አይሆንለትም። የተወሰነበት የእርግማን ቃል «አይወርስምና አውጣው» የሚል ነው። ይህ የመጽሐፉ ቃል ነው፣ ማንም ሊሸረው አይችልም! የባሪያይቱ ልጅ ከጨዋይቱ ልጅ ጋር በፍጹም ሊወርስ አይችልም።

በባርነት መንፈስ ስንመታ ወደ አንድ ቦታ የምንነዳው በዚህ በባርነት መንፈስ ተነድተን ስለሆነ ከዚያ ስፍራ የሚያስወጣን ነገር አይጠፋም። ይህ የባርነት መንፈስ በፍጹም እንድንቀይና እንድንረጋጋ አይፈቅድልንም።

ስለዚህም፣ ከአንዱ ጋር እንወጣለን፣ ሌላው ጋር ደግሞ እንገባለን፣ ብዙም ሳንቆይ ከዚም ደግሞ እንወጣለን፤ እንዲሁ እንደተቅበዘበዝን እንኖራለን። ይህ የመቅበዝበዝ መንፈስ በውስጣችን በቂ መሰል ምክንያቶች ስለሚሰጠን ስህተታችንን ማወቅ ይሳነናል።

የባርነት መንፈስ በአንድ ቦታ ቆይተን፣ ሰርተንና ተሰርተን መልካምን በረከት እንድንወርስ በፍጹም አይፈቅድልንም። የገባንበት ስፍራ የምንቆየው በዚያ በገባንበት ስፍራ አንድን የማንቀበለውን ነገር እስከምናገኝ ድረስ ነው። ስለሆነም፣ ከሌላው «ኮብልለን» መጥተን በገባንበት በአዲሱ ስፍራችን ለእኛ የማይስማማ አንድን ነገር እንዳገኘን ፈጥነን እንወጣለን። በአንድ ቦታ ተተክሎ መዝራት፣ ማጨድ፣ ዋጋ ከፍሎና ታግሶ ለበረከት ሆኖ መባረክ ስለማይሆንልን ዘወትር እንደተቅበዘበዝን እንኖራለን።

የባርነት አስራት ካሉበን የቃል ኪዳን ሰዎች መሆን በፍጹም አንችልም። በየምክንያቱ የጀመርነውን ጉዞ እናቋርጣለን። ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ፣ ከአንድ አገር ወደ ሌላኛው አገር፣ ከአንዲት ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላኛይቱ ቤተ ክርስቲያን፣ ከአንድ ፍቅረኛ ወደ ሌላ ፍቅረኛ እንደተቅበዘበዝን ዘመናችንን እንጨርሳለን። ቀድሞ የነበርንበትን ስፍራ «ክፋት» ማውራት የተለመደ ባህሪያችን ሲሆን፣ ያንን አለማልታ ሳንጨርስ ግን ከዚህኛውም የሚያስወጣን ምክንያት እናገኛለን።

ትናንት የነበረንን ጤናማ ጽኑ እምነትና አመለካከት መቼ እንደቀየርነው ሳይታወቅ ተለውጠን እንገኛለን። ወደ ትዳር፣ ወደ ቤተ ክርስቲያንም ሆነ ወደ ማንኛውም ነገር የምንመጣው ከተቻለን በዚያ ያለውን ነገር ለማስቀየር፣ ካልተቻለን ደግሞ በፍጥነት ጥሎ በመሄድ የዚያን ስፍራ ክፉነት ለማውራት እንጂ በመንፈስ ምሪት አይደለም። ከተስፋ ቃል ውጪ መኖር ምንኛ አስከፊ ሕይወት እንደሆነ ሰዎች ከእኛ ብቻ ቢማሩ በቂ ተግሳጽን እስኪያገኙ ድረስ አሳዛኞች ነን።

«በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ» (ገላትያ 5:1)።